ሥርዓተ ቤተክርስቲያን



ደብረ ቁራንዮ መድኃኔዓለም አንቀጻ ተዋሕዶ ሰንበት ት/ቤት

‹‹ሁሉ በአግባብ እና በስርዓት ይሁን››

ቅ ፩ኛቆሮ ፲፬ ፥ ፵

አዘጋጅ፡-ይገዙ ብዙአየሁ

ሰኔ ፳፻፩ዓ.ም



ማውጫ

- መቅድም 3
- መግቢያ-ስርዓተ ቤተክርስቲያን 4

ምዕራፍ 1 7

አንቀፅ 1 ስለቤተክርስቲያንና ስለእርሷ ስለሚገባው ሁሉ 7

- ቤተክርስቲያን ከመሠረት እስከ ጉልላት ያለው ምሳሌና ትርጉም 7
- ለቤተክርስቲያን የሚያስፈልጓት የተግባር ቤቶች 10
- ወደ ቤተ እግዚአብሔር ለመሄድና ለመግባት የሚደረግ ጥንቃቄ 10
- የቤተክርስቲያን አሠራር እና ስሪት 11
- የቤተክርስቲያን ስሪት 12
  - ንዋየ ቅዱሳት 12
- የንዋየ ቅዱሳት ምስጢር 13
- የንዋየ ቅዱሳት ዓይነትና አገልግሎት 13
- ቅዱስ አልባሳት 17
- የዜማ ንዋያት 19
- ቅዱሳን ስዕላት 20

ምዕራፍ 2 25

አንቀፅ 2 ቅዳሴ 25

- የቅዳሴ አገልግሎት 25
- በቅዳሴ አገልግሎት የሚገኙ ስርዓቶችና የአገልግሎት ዓይነቶች 26
- ለመቀደስ ማስቀደስ የሚደረግ ዝግጅት 28
- በስርዓተ ቅዳሴ ጊዜ የሚደረግ ጥንቃቄ 28
- ቅዳሴ በመቀደስ በማስቀደስ የሚገኝ በረከት 29

ምዕራፍ 3 30

አንቀፅ 14 ፀሎት 30

- የፀሎት ስርዓት 30
- ሰባቱ የፀሎት ጊዜያት 31

ምዕራፍ 4 32

አንቀፅ 15 ፆም 32

- የፆም ዓይነቶች 32

ምዕራፍ 5 36

አንቀፅ 19 ስለበዓላት 36

- ዐበይት በዓላት 38
- በዓለ ማርያም 45
- የቅዱሳን መላዕክት በዓላት 45
- የልዩ ልዩ ቅዱሳን በዓላት 45
- ዋቢ መፃሕፍት 46



መቅድም

ይህ የስርዓተ ቤተክርስቲያን ትምህርት ዋናው ዓላማ ምዕመናን ወይም በክርስትና እምነት ውስጥ ያሉ አማኞች የክርስትና ሕይወታቸው እንዲያድግና ይበልጥ እንድናድግ ተደርጎ የተዘጋጀ ነው።

ስርዓተ ቤተክርስቲያን እስከ አሁንም በሲኖዶስ በፍትሐ ነገስት እና በሌሎች የስርዓተ መጻህፍት በሰፊው ተወስኖ ተዕፏል። በዚህም መሰረት ላይ ክርስቲያኖች እምነታቸውን ለማነፅ አካሄዳቸው ለማስተካከል የመንፈሳዊ ምግባራትና ቀኖናዎች ለመተግበር ይጠብቁታል።

ለስርዓተ ቤተክርስቲያን መሰረቱ ደብተራ ኦሪት ነው። ስርዓተ መቅደስ ኦሪት ለስርዓተ መቅደስ ሐዲስ፣ ስርዓተ ካህናት ኦሪት ለስርዓተ ካህናት ሐዲስ መሰረት ሆኗል። ስለዚህም የብሉይ ኪዳን ስርዓት የደብተራ ኦሪት /የመቅደስ ኦሪት/ አሰራር ዛሬ ላለችው የቤተክርስቲያን ህንፃ አሰራር መሰረት ሆኗል። ለምሳሌ ደብተራ ኦሪት በ 3 (ሦስት) ክፍል ይሰራ እንደነበር ሁሉ ቤተክርስቲያን ቅኔማህሌት፣ ቅድስትና መቅደስ በሚል ትሰራለች።

በደብተራ ኦሪት በመቅደስ ታቦተ ሕግ ይቀመጥበት እንደነበረ በቤተክርስቲያን ህግ የተፃፈበት ጽላት ታቦት ለመሰዊያነት ይቀመጥበታል መስዋዕቱ ይቀርብበታል በብሉይ ይሰዋ የነበረው መስዋዕት ቢያልፍም አቀራረቡ ቢለወጥም ዛሬም በቤተክርስቲያናችን አማናዊ መስዋዕት ስጋ ወልደ እግዚአብሔር ይሰዋል። ይህም የሚያስረዳን የብሉይ ኪዳን ስርዓቶች ለሐዲስ ኪዳን መሰረት መሆኑ ነው።

የስርዓተ ቤተክርስቲያን ትምህርት ዓላማ

- ቤተክርስቲያን የምትከተላቸውን ዋና ዋና ቀኖናዎች ለማወቅ
- በስርዓተ ቤተክርስቲያን ትምህርት ብሉያት ሐዲሳት መፃሕፍት በጥልቅና በስራ ስለሚታዩ በመጠኑ ለመማርና ለማስተማር ይረዳል።
- በመንፈሳዊ ሕይወታችን ያሉትን መንፈሳዊ ምግባራት ለመፈፀም ይረዳል
- ያጠፋነውን ጥፋት በምን መልኩ ማስተካከል እንዳለብን ያስረዳናል።
- የቤተክርስቲያን አጥሯ (ቅጥሯ) የቱ እንደሆነ እና ከዛ ድንበር አፈንግጠን እንዳንወጣ ይረዳናል።
- አንድ ሀሳብና አንድ ልብ ለመሆን አንድ አይነት ስርአት ያስፈልጋል። /ፊኛቆሮ ፲፬ ፥ ፵/
- የሃይማኖት ምስጢራትን ለመፈፀም ስርዓት የሃይማኖት መገለጫ ነው። ለምሳሌ ጥምቀት፣ ቁርባን፣ ፆም፣ ፀሎት ወዘተ...የአተገባበር መንገድ /ስርዓት/ መማር ይገባልና።
- የቤተክርስቲያን ንዋያተ ቅዱሳት ከሌሎች ለመለየት እና የሚገባቸውን ክብር ለመስጠት
- የቤተክርስቲያን ንዋያተ ቅዱሳት ትውፊት ተጠብቀው እንዲቆዩ የሚገባውን አስተዋፅኦ ለማበርከት ያስችላልና።



ሥርዓተ-ቤተክርስቲያን

መግቢያ

ስርዓት ማለት ‹‹ ሠርዓ ሠራ ›› ከሚለው የግዕዝ ግስ የወጣ የምዕላድነት ዘር ያለው ስም ነው፡፡ ትርጉሙም ሕግ፣ ደንብ፣ አሠራር፣ መርሐ ግብር ማለት ሲሆን ትርጓሜው እንደ አገባቡ የራሱን ፍቺ ይይዛል፡፡ ቤተክርስቲያን የሚለው ቃል በዘይቤያዊ ፍቺ ሲፈታ እንዲህ ይተረጎማል፡፡

A. ***የፀሎት ቤት /ህንፃ ቤተክርስቲያን/*** ፡- የክርስቲያን መሰብሰቢያ የክርስቲያን መገናኛ ማለት ነው፡፡ ይህም ማለት የሚፀለይበት፣ ስጋ ወደሙ የሚቀበሉበት፣ የሚሰግዱበት ከእግዚአብሔር ጋር የሚገናኙበት ቦታ ማለት ነው፡፡ (ኢሳ 56፥7/ ኤር 7፥10-11/ ሉቃ 19፥46/ ማቴ 18፥20)

E. ***የክርስትያን ወገን*** ፡-ማኅበረ ምዕመናን ተሰብስበው በራሳቸው ቤተክርስቲያን ተብለው ይጠራል፡፡

(1ጴጥ 5፥13/ ሮሜ 16፥16/ የሐዋ 8፥1/ 2ኛቆሮ 8፥1-2)

H. **የግለሰብ ሰውነት ፡-** የአንድ ክርስቲያን ሰውነት የእግዚአብሔር ቤተመቅደስ /ቤተክርስቲያን/ ነው፡፡

(ዮሐ3፥1-10/ ኤፌ2፥19-22/ 1ኛጴጥ 1፥23/ 1ኛቆሮ 3፥16-17)

በአጠቃላይ ስርዓተ ቤተክርስትያን ማለት የቤተክርስቲያን ሕግ፣ የቤተክርስቲያን ቀኖና የቤተክርስቲያን የአሠራር መርሐግብር ማለት ነው፡፡ አንድም በአሚነ ሥላሴ ከመንፈስ ቅዱስ አብራክ ከማኅፀነ ዮርዳኖስ የእግዚአብሔር ልጆች የተባሉ ክርስቲያኖች በመኖሪያቸው በመሰብሰቢያቸው የሚመሩበት የሚተዳደሩበት ደንብ፣ አሠራር፣ ሕግ ማለት ነው፡፡

የስርዓተ ቤተክርስቲያን ምንጮች

የስርዓተ ቤተክስቲያን ትምህርት ጥልቅና ሰፋ ያለ እንደመሆኑ መጠን ከብሉያትና ከሐዲሳት ከመፃሕፍተ ሊቃውንትና ከመፃሕፍተ መነኮሳት ከሌሎችም ልዩ ልዩ የታሪክ ድርሳናት መፃሕፍት በመጥቀስ በመተርጎምና ምስጢሩን በመመርመር ላይ የተሰራ ነው፡፡ ከነዚህም ዋና ዋናዎቹ፡-

፩. መፃሕፍተ ብሉያት

፪. መፃሕፍተ ሐዲሳት

፫. የሐዋርያት ሲኖዶስ

፬. ሥርዐተ ጽዮን

፭. አብጥሊስ

፮. ትዕዛዝ

፯. ዲድስቅልያ

፰. የሦስቱ ጉባኤያት ውሳኔ (የኒቂያ፣ የቁስጥንጥንያ፣ የኤፌሶን)

፱. ከ4ኛው መ/ክ/ዘመን ጀምሮ እስከ አሁን በየጊዜው የተነሱ የቤተክርስቲያን ሊቃውንት የጻፏቸው ልዩ ልዩ የስርዓት መፃሕፍት ናቸው፡፡




በተለየ ሁናቴ ለስርዓተ ቤተክርስትያን ትምህርት ዓቢይ መጋቢ የሚሆነው መፅሐፍ "<u>ፍትሐ ነገስት</u>" በመባል ይጠራል።

በፍትሐ-ነገስት የሚለው ቃል " ፍትሕ እና ነገስት " በሚሉት ሁለት ቃላት የተሰናሰለ ወይም የተያያዘ ቃል ነው። ትርጓሜውም ፍርድ ውሳኔን መስጠት ሕግና ስርዓት ማስፈን ማለት ሲሆን ነገስታቱ ክርስቲያኖች ከመሆናቸው ጋር ስጋዊውም ሆነ መንፈሳዊውን ፍትሕ ይመለከቱ ስለነበር በነገስታቱ ስም " ፍትሐ ነገስት " ተብሎ ተሰይሟል።

ኢትዮጵያ አገራችን በጽሁፍ ከአሉዋት የሕግ መዛሕፍት መካከል ታላቁና የታወቀው " ፍትሐ - ነገስት " የተባለው ነው።

ፍትሐ ነገስት ከዓረብኛ ወደ ግዕዝ ተተርጉሞ በስራ ላይ የዋለው በንጉሠ ነገስቱ አፄ ዘርዐ ያዕቆብ (ከ1444 እስከ 1468) ዓ.ም እንደሆነ ይታወቃል። ይህ ታላቅ መፅሐፍ በጉባዔ እየተረጎመ ከአንዱ ወደ አንዱ እየተላለፈ በኢትዮጵያ የሕግ ቀዋሚ የፍርድ መፅሐፍ ሆኖ አገልግሏል። ዕውቀቱ የሚረድ የሕግ ሊቃውንት ሁሉ ከፍተኛ የሕግ አዋቂነት የመዓረግ ስም ይሰጣቸው ነበር።

ፍትሐ ነገስት በሁለት ዓበይት ክፍሎች ይከፈላል።



ስለዘህ ፍትሐ ነገስት 51 አንቀጽ የሚይዝ ሲሆን 22ቱ ፍትሕ መንፈሳዊ 29ኙ ፍትሕ ስጋዊ በመባል ይጠቃለላሉ።

፩. ***<u>ፍትሕ-መንፈሳዊ</u>*** - ይህ የፍትሐ ነገስት ክፍል ***<u>ቀዳማዊ</u>*** በመባል ይጠራል። በአጠቃላይ በውስጡ የሚያትተው ስለመንፈሳዊ ሀሳብ ነው።

- ከፍትሐ ነገስት 51 አንቀጽ ውስጥ የመጀመሪያዎቹን 22 አንቀጽ የሚይዘው ፍትሕ መንፈሳዊ ነው።

፪. ***<u>ፍትሕ-ስጋዊ</u>*** - ይህ የፍትሐ ነገስት ክፍል ***<u>ዳግማዊ</u>*** በመባል ይጠራል ዓለማውያን ስለሆኑ የአስተዳደር ስርዓቶች ሌሎች ዓለማዊ ሀሳብ ይይዛል።

- ቁጥራቸው 29 አንቀጽ ነው።

በዚህ የትምህርት ወቅት እኛ ትኩረት አድርገን የምንማረው ፍትሕ መንፈሳዊ የሚባለውን ቀዳማዊ ክፍል ሲሆን በተለየ ሁኔታ ከዚህ ክፍል ውስጥ የተወሰኑትን ለመመልከት እንሞክራለን። ከፍትሕ መንፈሳዊ የመጀመሪያ ክፍል ውስጥ የሚከተሉትን አንቀጾች በሰፊው እንመለከታለን።



አንቀጽ ፩. ስለቤተክርስቲያን እና ለእርሷ ስለሚገባው ሁሉ

አንቀጽ ፲፪. ስለ ቅዳሴ

አንቀጽ ፲፬. ስለ ፀሎት

አንቀጽ ፲፭. ስለ ፆም

አንቀጽ ፲፱. ስለ በዓላት



ምዕራፍ አንድ (፩)

አንቀጽ ፩. ስለቤተክርስቲያን እና ለእርሷ ስለሚገባው ሁሉ

ይህን ክፍል በሁለት ዓቢይ ክፍል እንከፍለዋለን፡፡

1.1 ቤተክርስቲያንና ንዋያተ ቅዱሳት
1.2 ለቤተክርስቲያን ስለሚገባው ሁሉ በሚል ይመደባል፡፡

1.1 ቤተክርስቲያንና ንዋያተ ቅዱሳት

ይህን ክፍልም ለመረዳት ያመቸን ዘንድ በሁለት ክፍል እንከፍለዋለን፡፡

1.1.1 ቤተክርስቲያን
1.1.2 ንዋየ ቅድሳት

1.1.1 **ቤተክርስቲያን** ፡- በመግቢያችን ለመመልከት እና ለመረዳት እንደሞከርነው በዘይቤያዊ ፍቺ ሦስት ትርጓሜ ይይዛል፡፡ በሌላ መልኩ ደግሞ በምስጢራዊ ፍቺ ስንፈታው የተለያየ ትርጓሜን ይይዛል፡፡

፡- በቤተክርስቲያናችን ***ምስጢራዊ ፍቺ*** ማለት ከቋንቋ ሰዋሰው ወጭ ነገሩ ካለው ወይም ከሚሰጠው ስራ አንጻር የሚሰጥ ትርጓሜ ነው፡፡ በዚህም ቤተክርስቲያን የሚለው ቃል በብዙ መልኩ ይፈታል፡፡ ከዚህም ውስጥ፡-

A. **ቤተ ፀሎት**፡- ፀሎት ስለሚፀለይበት

E. **ቤተ እግዚአብሔር**፡- ምንም እግዚአብሔር በሁሉ የመላ አምላክ ቢሆንም በተለየ ሁኔታ የሚገኝበት ቤተመቅደስ እንደሚያስፈልገው በመናገሩ ሰሎሞን የመጀመሪያው ቤተመቅደስ ሰርቷል፡፡ ስለዚህ ቤተክርስቲያን ቤተእግዚአብሔር (የእግዚአብሔር ቤት) ትባላለች፡፡

H. **ቤተ ምስዋዕ**፡- መስዋዕተ ሐዲስ አማናዊ ኢየሱስ ክርስቶስ የሚሰዋበት ቦታ ነች፡፡

ስለዚህ ሌሎች እንደዚህ የመሳሰሉ መጠሪያ ስሞች አላት፡፡

በዚህ ክፍል የምንመለከታቸው፡-

- *ቤተክርስቲያን ከመሠረት እስከ ጉልላት ያለው ምሳሌና ትርጉም*
- *ለቤተክርስቲያን የሚያስፈልጓት የተግባር ቤቶች*
- *ወደ ቤተክርስቲያን ለመሄድና ለመግባት መሟላት ያለባቸው ነገሮች*
- *የቤተክርስቲያን አሠራር እና ሰሪት*

፩. ቤተክርስቲያን ከመሠረት እስከ ጉልላት ያለው ምሳሌና ትርጉም

- በአጠቃላይ ሕንፃ ቤተክርስቲያን ***በአዳም*** ትመሰላለች ይኸውም አዳም የሁሉ አስገኝ የፍጥረት ቀዳሚ እንደሆነ ቤተክርስቲያንም የሁሉ ነገር መሠረት ነችና፡፡ አንድም ***በመንግስተ ሰማያት*** ትመሰላለች ቤተክርስቲያን በምድር ያለች የመንግስተ ሰማያት ስርዓት ስብሐተ እግዚአብሔር የሚደርስባት በመሆኗ እንዲሁም ***በኖኅ መርከብም*** ትመሰላለች ያቺ የኖኅ መርከብ በሦስት ክፍል የተከፈለች እንደነበረች ዛሬም በቤተክርስቲያን በእምነት በምግባር ፀንተው ለተከለሉባት ከጥፋት የምታድን በመሆኗ በኖኅ መርከብ ልትመሰል ችላለች፡፡
- ቤተክርስቲያን ***በሥላሴ*** ትመሰላለች፡፡ ይኸውም፡-

➲ መሠረቱ በእግዚአብሔር አብ

➲ሕንፃው በእግዚአብሔር ወልድ

➲ ጣሪያው በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ

❖ የሕንፃ መሠረቱ ከመሬት በታች ስለሆነ የተገለጠ (የታየ) እንደ አይደለ እግዚአብሔር አብ ግልጽ የሆነው በወልደ እግዚአብሔር ሰው በመሆኑ ነውና። አንድም ***<u>በዓሣ ማጥመጃ መረብ</u>*** ትመሰላለች። በማጥመጃ መረብ ዓሣ እንደሚሠበሰብባት በቤተክርስቲያን የሚሰበከው ትምህርት መሰብሰቢያ ነውና በከበረ ዕንቁ ትመሰላለች። አንድም ***<u>በስናፍጭ ቅንጣት</u>***። ስናፍጭ ስትዘራ ከሁሉ ታንሳለች ባደገች ጊዜ ከአዝርዕት ሁሉ በልጣ የአዕዋፍ መስፈሪያ ትሆናለች ቤተክርስቲያን ስትመሰረት በ120 ቤተሰብ ነው ኋላ ሰፍታለች አንድም በታላቅ ***<u>የሰንዴ አዝመራ</u>*** ንፁህ ዘር ሕገ ወንጌል ሐዋርያት ዘርተውባታልና ነው።

- ***<u>ቅፅረ- ቤተክርስቲያን (የቤተክርስቲያን ግቢ)</u>***
  - የዓለም ምሳሌ ነው። በዓለም ብዙ ዓይነት ሰው እንደሚኖር እንዲሁ በቅፅረ ቤተክርስቲያንም ሁሉም በአንድነት ይኖራሉና። መሬቱ የዓለም ምሳሌ ሲሆን አዕዕዱ ደግሞ በዓለም ያሉትን ሁሉ ይወክላሉ።
- ***<u>አውደ-ምሕረት</u>***
  - የቃሉ ትርጉም ከሁለት ጥምር ቃላት "አውድ" እና "ምሕረት" የተገኘ ሲሆን ትርጓሜውም ***<u>የምሕረት አደባባይ</u>*** ማለት ነው።
  - አውደ ምሕረት **በደብረ ዘይት** ይመሰላል በደብረ ዘይት ጌታ ለደቀመዛሙርቱ ነገረ-ምዕአቱን ስለተናገረበትና በኋለኛውም ዘመን ፍርድ የሚሰጥበት በመሆኑ በዚህ ተመስሏል። አንድም በአውደ-ምሕረት ላይ ሕይወት የሚሰጠውን ብስራተ ወንጌል ለዓለም የሚነገርበት በመሆኑ የምሕረት አደባባይ ተብሏል።
- ***<u>ጠርብ</u>***
  - **የማዕዘን እንጨት** ወይም **ድንጋይ** ማለት ነው። ምሳሌነቱ **በሰማዕትነት** ነው። ቁጥራቸው 24፣ 22፣ 12 ሊሆን ይችላል። 24 ከሆነ በ24ቱ ካህናተ ሰማይ፣ 22 ከሆነ ከአዳም እስከ ያዕቆብ በተነሱት ደጋግ አባቶች፣ 12 ከሆነ ደግሞ ወንጌልን ለዓለም በሰበኩት ሐዋርያት ይሆናል።
- ***<u>ማገሩ</u>***
  - እንጨቶች ወይም ጥርብ ድንጋይ ሊሆን ይችላሉ ወይም ጊዜው እንደፈቀደው የሕንፃ ጥበብ ዕቃ ልንጠቀምበት እንችላልን። ማገሩ ምሳሌነቱ የምዕመናን /የሕዝበ ክርስቲያን/ ነው። ምዕመናን ለቤተክርስቲያን ውበቷ ናቸው
- ***<u>መስኮቶች</u>***
  - ከእንጨት፣ ከብረት፣ ከአልሙኒየም ሲሰራ ይችላል። ብዙውን ጊዜ ቁጥራቸው የታወቀ አይደለም ከፍም ዝቅም ይላል እንደቤተክርስቲያኑ መጠን ሊወሰን ይችላል። ቁጥራቸው አንዳንዴ 24 ይሆናል ትንንሹ 20 ትልልቁ 24።
    - ➲ 20 መሆኑ የ20ው ዓለማት፡-
      - ☞ ሁለት ዓለመ ነፍስ
      - ☞ አራት ዓለመ መሬት
      - ☞ አምስት ዓለመ ማይ
      - ☞ ዘጠኝ ዓለም እሳት
    - ➲ 4 ደግሞ የዓበይት ነቢያት
      - ☞ ኢሳይያስ
      - ☞ ሕዝቅኤል
      - ☞ ኤርሚያስ
      - ☞ ዳንኤል
    - ⇨ አንድም የአራቱ ሊቃነ ጳጳሳት **<u>የሮም፣ የአንፆኪያ፣ የእስክንድሪያ፣ የኢየሩሳሌም</u>**
- ***<u>የበሩ መቃን</u>***
  - ምሳሌነቱ የሙሴና የአሮን ነው። ሙሴ በምስፍንና፣ አሮን በካህናተ እስራኤል እንደመሩና እንደተሸከመ እንዲሁም ምሰሶዎቹ (የበሩ) ሕንፃ ቤተክርስቲያንን ይሸከማሉ።



- ***አዕማድ /ምሰሶዎች/***
  - ቤተክርስቲያን ሲሰራ ትላልቅና ትናንሽ ምሰሶዎች ይኖሩታል ትላልቆቹ **የሐዋርያት** ትንንሾቹ ደግሞ **የአርድዕት** ምሳሌ ናቸው። የምዕመናን ልቦና በወንጌል ላይ በመመስረታቸው አንድም አዕማድ በወንጌል ይመሰላሉ። አማናዊቷ ቤተክርስቲያን የተመሰረተችው ምስጢራቷንም የምታከናውነው የተመሰረተችው በወንጌል መሠረትነት ላይ በመሆኑ። አንድም የሠራዊተ መላዕክት ምሳሌዎች ናቸው።
- ***ደረጃ***
  - ደረጃ በአጠቃላይ ስንመለከተው በሦስቱ ዘመናት እንመስለዋለን።
  - ✓ *የመጀመሪያው ደረጃ* ፦ በዘመነ አበው-ከአዳም እስከ ሙሴ ባለው
  - ✓ *የሁለተኛው ደረጃ* ፦ በዘመነ መሳፍንት-ከሙሴ እስከ ሳሙኤል ይህ ዘመን ዘመነ ካህናትንም ያጠቃልላል። እንደምን ቢሉ ሙሴ በምስፍንና ሲያገለግል በዚያው ዘመን አሮን በክህነቱ ያገለግላል። ስለዚህም ዘመነ መሳፍንትና ዘመነ ካህናት እንደ አንድ ይቆጠራሉ።
  - ✓ *የሦስተኛው ደረጃ* ፦ በዘመነ ነገስታቱ-ከሳኦል እሰከ ክርስቶስ በተመሳሳይ ዘመነ ነቢያትም በዚህ ይጠቃለላል። እንደምን ቢሉ ዳዊት በንጉስነትም በነቢይነትም ያገለግልበት የነበረ ዘመን ስለሆነ በአንድ ይቆጠራሉ።
    - ❖ ሦስት ደረጃ ወጥተን የምናገኘው ወደ ቤተመቅደስ መግቢያ መሄጃ ወደ ሐዲስ ኪዳን ወደ ሆነችው ወደ ቤተመቅደስ መግቢያ ይሆናል። በዚህም ሦስቱን የብሉይ ዘመን ተሻግረን የምናገኛት ቤተክርስቲያን በፍፁም ሕግ የተመሰረተችው ሐዲስ ኪዳን ትሆናለች ማለት ነው።
- ***የቤተክርስቲያን ክዳን /ሣሩን/ ክፍክፍት/ ጣሪያው/***
  - ይህ የሕንፃው ክፍል ዘመን እንደሚሰጠው የሕንጻ ጥበብ ደረጃ ሊሰራ ይችላል። በሳር ክዳን፣ በቆርቆሮ፣ በአርማታ ሊሰራ ይችላል። በጥንት ጊዜ የነበረው የቤተክርስቲያን የጣሪያ ሽፋን የሚሰራው በሳር ክዳን ነበር ምሳሌነቱም ሄሮድስ ያስፈጃቸው ሕፃናት ነው። ሕፃናቱ ምንም ሳያውቁ ለሰማዕትነት ክብር እንደበቁ ሁሉ ሳሩም ምንም ሳያውቅ ለተቀደሰው የእግዚአብሔር ቤት መስሪያ ውሏልና በዚህ ይመሰላል።
- ***ጉልላቱ***
  - የክርስቶስ ምሳሌ ነው። ቅዱስ ጳውሎስ በመልዕክቱ እንደተናገረው(1ኛቆሮ11፥1) የሁሉ የበላይ ስለሆነ የቤተክርስቲያን ጉልላቷ ክርስቶስ ነው።
- ***መስቀሉና ጌጡ***
  - በጉልላቱ ላይ ያሉት መስቀሉና ጌጡ የራሳቸው የሆነ ምሳሌና ትርጉም አላቸው። ይኸውም መስቀሉ በክርስትና ሕይወት ውስጥ የሚገጥመንን መከራ ሲያመለክት ጌጡ ደግሞ ያንን መከራ(ፈተና) አልፈን የምናገኘውን አክሊል (የድል ሕይወትን) ያመለክተናል። አንድም መስቀል ውሃ ሳያጠጣት የለመለመች የአሮን በትር ምሳሌ ነው።
- ***የሰጎን እንቁላል***
  - የሰጎን እንቁላል በጥንቷ ቤተክስቲያን እና በአንዳንድ ጥንታዊ ቤተክርስቲያን እስካሁን ይገኛል። ይህ እንኳን ባይገኝ አሁንም ድረስ በብረት የእንቁላሉ ቅርፅ በመስራት በቤተክርስቲያን ላይ ይኖራል።
  - የሰጎን እንቁላል ምሳሌነቱ ሰጎን እንቁላሏን ለማስፈልፈል ከፈለገች 40 ቀን እስኪሞላ ድረስ ትመለከተዋለች እሷ ባትችል ወንድ ሰጎን ያግዛታል። ነገር ግን ቀኑ ሳይሞላ ከራቀችው በስብሶ ይፈርሳል። እንዲሁ ምዕመናን ከእግዚአብሔር እቅፍ ከራቁ የሚያጋጥማቸውን ነገር ይወክላል።
  - እንቁላሉ የምዕመናን፣ ቅርፊቱ የመከራ፣ ሰጎኗ የመንፈስ ቅዱስ አንድም ሰጎኗ የምዕመናን ምዕመናን የክርስቶስን መምጣት ተስፋ አድረገው ፀንተው የመጠበቃቸው ምሳሌ ነው።
- ***ሻኩራው /መርገፉ/***
  - በውሃ መውረጃው ጫፍ ላይ የሚገኘው በቤተክርስቲያን ውስጥ በፀጥታ በነፋስ ኃይል እየተመታ የሚጮኸውን ይወክላል። ይህም ምሳሌነት አለው። ምሳሌነቱም የሐዋርያት፣ የአርድዕት፣ የሊቃውንት የትምህርታቸው ምሳሌ ነው። አንድም ሄሮድስ ያስፈጃቸው ሕፃናት ድምፅ ተደርጎ ይወሰዳል።



- ***መርገፃ /ደጅ በሩ/***
  - የቤተክርስቲያን የግቢው በር አካባቢ ያለው ስፍራን ይወክላል። ይኸውም ምሳሌነቱ የብሉይ ኪዳን ነው። በብሉይ ኪዳን ዘመን ዓድቃንም ኃጥአንም በሲኦል ቆይተው ወደ ገነት እንደገቡ ይህ ስፍራም ወደ ሐዲስ ኪዳን ቤተክርስቲያን ከመግባታቸው በፊት ንፁሓንም ንፁህ ያልሆኑትም የሚቆዩበት ስፍራ ነው።

፪. ለቤተክርስቲያን የሚያስፈልጓት የተግባር ቤቶች

- **<u>ቤቴልሔም</u>** ፦ ስያሜው የተወሰደው ጌታችን በተወለደበት በቤቴልሔም ዘይሁዳ ነው። ምስጢሩ ዲያቆናቱ ጎብስቱን በቤቴልሔም አዘጋጅተው ወደ ቤተ እግዚአብሔር ለመስዋዕት መምጣቱ በቤቴልሔም የተወለደው በጎልጎታ ለመስዋዕት የቀረበው ክርስቶስ ይህ ነው ለማለት ነው መቅደስ የጎልጎታ ምሳሌ ናት። ሁልጊዜ የሚሰራው **በምስራቅ** አቅጣጫ ነው።
- **<u>የግብር ቤት</u>** ፦ ለመስዋዕት የሚሆነው ስንዴ /መገበሪያ/ የሚሰየምበት፣ የሚደቅበት/ የሚፈጭበት ነው። ስንዴው መገበሪያ ተብሏል። መፍጨቱ ደግሞ መሰየም ይባላል። ይህም የመስዋዕቱ አቀራረብ ቋንቋ ነው።
- **<u>ዕቃ ቤት</u>** ፦ የቤተክርስቲያን ንዋየ ቅድሳት የሚቀመጥበት /ሕዝ 44፥19/ ፍት.መን 12/
- **<u>ቤተ ምጥማቅ /የማጥመቂያ ቤት/</u>** ፦ ስርዓተ ጥምቀት የሚፈፀምበት ቤት ነው።
- **<u>ደጀ ሰላም</u>** ፦ ከቤተክርስቲያናችን ቅጥር ጋር ተያይዞ በምዕራብ በኩል የሚሰራ የካህናት መመገቢያ ነው።በገነት ይመሰላል በትምህርት ያሉ ተማሪዎች ያንን እየበሉ ወደ መንግስተ ሰማያት መቅደስ ይገባሉና።

- እነዚህ የግድ የሚያስፈልጉ ቢሆንም ከነዚህ በተጨማሪ በአሁን ጊዜ የሚሰሩ ቤቶች አሉ። እነሱም፦
  - ✓ የሰበካ ጉባዔ ጽ/ቤት
  - ✓ የሰንበት ት/ቤቶች ክፍሎች
  - ✓ የምዕመናን የስብከተ ወንጌል አዳራሽ
  - ✓ ቤተ-መፃሕፍት ናቸው።

፫. ወደ ቤተ እግዚአብሔር ለመሄድና ለመግባት የሚደረግ ጥንቃቄ

- ለፀሎት፣ ቁርባን ለመቀበል ወደ ቤተ እግዚአብሔር በሚኬድባቸው ዕለታት እንዲሁም በያምና በሰንበት በበዓላት ቀኖችም ወንድና ሴት መገናኘት ክልክል ነው። በመኝታ የተገናኘ ወደ ቤተክርስቲያን መግባት አይችልም። በበዓላትና አዕዋማት ወቅት ወደ ቤተክርስቲያን ባይሔዱም ሊጠበቁ ይገባል። /ዘፀ 19፥15/ 1ኛቆሮ7፥5-7/ ኩፋ34፥12/
- የማገዘረክረክ ነውር ያለበት በዚህ ጊዜ ወደ ቤተክርስቲያን አይገባም ስጋ ወደሙን ሊቀበል አይገባውም። /ፍት.መን. 13/
- ሴት የወር አበባዋ ሲመጣ 7(ሰባት) ቀን ድረስ፣ ስትወልድ ወንድ ከሆነ 40 ቀን ሴት ከሆነች 80 ቀን ድረስ ወደ ቤተክርስቲያን መግባት ክልክል ነው። ከዚህ በኋላ ገላዋን ታጥባ ትገባለች። /ዘሌ12፥1/ ፍት.መን 6/
- ወንድ ሕልመ ሌሊት /ዝንየት/ ከመታው በዕለቱ ወደ ቤተክርስቲያን አይገባም በማግስቱ ገላውን ታጥቦ ይገባል። /ዘሌ 15፥2-18
- ወደ ቤተክርስቲያን ሲገቡ ጫማን አውልቆ ወገቡን ታጥቆ አደግድጎ መግባት ይገባል። /ዘፀ3፥5-6/ ኢያ5፥15/
- አጭርና ያደፈ ልብስ ለብሶ ወደ ቤተክርስቲያን መሄድ ክልክል ነው። ረዘም ያለና ንፁህ ያለንን አንዷን አጥበን ለብሰን መግባት ያስፈልጋል። /ዘፀ19፥10-11/
- በቤተክርስቲያን ውስጥ መሳቅ፣ ስለዓለማዊ ስራ መነጋገር፣ መጮህ፣ መታበይ ፈፅሞ የተከለከለ ነው። ይልቅስ በዝምታ፣ በፍርሀት የእግዚአብሔርን ምሕረት በጥብዓተ ልብ መፈለግ ያስፈልጋል።



- ❖ ወደ ቤተክርስቲያን ሲመጡ መባዕ፣ ምዕዋት ይዞ መሔድ /ዘፀ 34፥20/
- ❖ በቤተክርስቲያን ውስጥ ግብግ ለማድረግ መጥራት አይገባም፡፡ /1ኛቆሮ11፥20-22/
- ❖ ወደ ቤተክርስቲያን ሲመጡ የበደሉት ሰው ካለ ይቅርታ መጠየቅ የተቀየሙት ካለ ደግሞ ይቅርታ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ /ማቴ 5፥25/
- ❖ በስርቆት በማታለል የወሰዱት ነገር ካለ መመለስ
- ❖ መጠጥ ጠጥቶ (ሰክሮ) መግባት የተከለከለ ነው፡፡/ዘፀ 10፥3/
- ❖ ወደ ቤተክርስቲያን ሲገቡ መሳለም እጅ መንሳት ይገባል፡፡ /መዝ28፥2/ኤር26፥2/ሕዝ46፥3/ፊል2፥9-10/

ወደ ውስጥ ከመግባታችን በፊት "***<u>ሰላም ለኪ ቅዱስ ቤተክርስቲያን አምሳለ እየሩሳሌማዊ</u>***" ብለን እጅ ነስተን ሰለምታ አቅርበን መግባት ይኖርብናል፡፡

፬. <u>የቤተክርስቲያን አሠራር እና ስሪት</u>

- የቤተክርስቲያን አሠራር (ሕንፃ ቤተክርስቲያን) በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ስርዓት መሰረት ሦስት ዓይነት የቤተክርስቲያን አሠራር አለ፡፡ እነሱም፡-
  1. ሰቀልማ (ሞላላ)
  2. ክብ
  3. ዋሻ

1. **<u>ሰቀልማ (ሞላላ)</u>**.....እንደ ብሉይ ኪዳን ቤተመቅደስ (ምኩራብ) ቅርፅ ያለ ነው፡፡ የዚህ ዓይነት ቤተክርስቲያን ቅርፅ የተወረሰው ከሰሎሞን ቤተመቅደስ በኋላ በዘመነ ክርስቲና በታላቁ ቆስጠንጢኖስ ንጉስ አማካኝነት ነው፡፡ ለምሳሌ፡- ደብረ ዳሞ፣ አክሱምን መውሰድ እንችላለን፡፡ ቤተክርስቲያኑ በመጋረጃ እንጂ በግምብ የተከፈለ አይደለም፡፡ ጉልላቱም እንደ ቤተክርስቲያኑ ትልቅነት የሚወሰን ነው፡፡
2. **<u>ክብ</u>**.....ክፍሎቹ በግድግዳ (በግምብ) ይከፈላል፡፡ 3 ክፍል ይኖረዋል፡፡ ቅኔ ማኅሌት፣ ቅድስት እና መቅደስ በመባል ይጠራሉ፡፡ 3 ክፍሎች መሆናቸው በሦስቱ ዓለመ መላዕክት ኢዮር፣ ራማ እና ኤረር ይመሰላሉ፡፡

A. ***<u>ቅኔ ማኅሌት</u>*** ፡-ስያሜው የተወሰደው ከግብሩ ነው መዘምራን /ደብተራ/ ስብሐተ እግዚአብሔር ማኅሌተ እግዚአብሔር ያቀርቡበታል፡፡

- ➢ በዚህ ክፍል ፡-
  - ☞ **በምዕራብ** ፡- መዘምራኑ (ቀሳውስት) ዝማሬ ያቀርቡበታል፡፡ ሰዓታት ይቆሙበታል፡፡
  - ☞ **በሰሜን** ፡- ምዕመናን (ወንዶች) ንዑሰ ክርስቲያን ወንዶች ያስቀድሱበታል፡፡
  - ☞ **በደቡብ** ፡- ምዕመናን (ሴቶች) ንዑሰ ክርስቲያን ሴቶች ያስቀድሱበታል፡፡
    - ይህ ክፍል ሦስት በሮች አሉት፡፡ ምሳሌነቱ የሥላሴ ነው፡፡

E. ***<u>ቅድስት</u>*** ፡-ስያሜው ከብሉይ ኪዳን ስያሜ ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡ የቤተክርስቲያን ማዕከላዊ ቦታ ነው፡፡ በዚህ ክፍል፡- ☞ **በስተ ምዕራብ**፡- የሚያስቀድሱት ቆሞሳት፣ ቀሳውስትና ዲያቆናት ናቸው፡፡

☞ **በስተ ሰሜን**፡- መነኮሳትና የሚቆርቡ ወንዶች ምዕመናን ያስቀድሱበታል፡፡

☞ **በስተ ደቡብ**፡- መነኮሳትና የሚቆርቡ ሴቶች ምዕመናን ያስቀድሱበታል፡፡

- ይህ ክፍል በአራቱ አዝማናት በሮች አሉት፡፡

H. ***<u>መቅደስ</u>*** ፡-የመጨረሻው ክፍል ሲሆን እንደ ብሉይ ኪዳን ቅድስተ ቅዱሳን ስያሜው ከዚያ ተወርሷል፡፡ በዚህ ክፍል ምስጢረ ቁርባን ስርዓተ ቁርባን የሚፈፀምበት መንበረ ታቦቱ ሌሎቹም ንዋያተ ቅዱሳት ይገኛሉ፡፡ በዚህ ክፍል ከርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳቱ ጀምሮ ሊቃነ ጳጳሳት፣ ጳጳሳትና ኤጲስ ቆጶሳት ያስቀድሳሉ፡፡



- መቅደስ ውስጥ ለመግባት የሚችሉት ክህነት ያላቸው ብቻ ናቸው። መቅደስ ሦስት በር ያለው ሲሆን በምስራቅ ብቻ መግቢያ የለውም። ለእያንዳንዱ በር መንጦላዕት/ መጋረጃ/ አለው። የዚህ ዓይነት ቤተክርስቲያን ባለ አንድ ጉልላት ነው።

3. ዋሻ.....በአብዛኛው ጊዜ የዋሻ ቤተክርስቲያን በሩ አንድ ብቻ ነው። ቅኔ ማኅሌት፣ ቅድስቱና መቅደሱም የሚለየው በመጋረጃ ነው። ላሊበላ ካሰራቸው አብያተ ክርስቲያናት አንዳንዶቹ ዋሻዎች ናቸው።

፫. የቤተክርስቲያን ስሪት

- አስቀድመን የተመለከትነው ቤተክርስቲያን ከሕንፃ አሰራር ዲዛይን አንፃር ሲሆን ይህ ክፍል ደግሞ ቤተክርስቲያን ካላት ስነ-አመራራዊ መዋቅር ወይም አስተዳደራዊ ቅርፅ አንፃር የምንመለከት ይሆናል።
- በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ስሪት ሦስት ክፍል አለው። ይኸውም፦

1) የገዳም ስሪት
2) የደብር ስሪት
3) የገጠር ስሪት

1. ***የገዳም ስሪት*** ፦ በሁለት ይከፈላል- A) የንፍሮ ገዳም
E) የሕግ ገዳም

A) **የንፍሮ ገዳም** ፦በመነኮሳት አንድነት የሚተዳደር ነው። ገዳሙ የሚተዳደረው **በአበምኔት** ነው። ለሴቶች ደግሞ **እመምኔት** በመባል ይጠራሉ። ይህ የገዳም ስሪት ሊሠራ የሚችለው በገለልተኛ ቦታ ተወስኖ በተጋድሎ ሕይወቱን ያሳለፈ ፃድቅ ባረፈበት የታሪክና የሃይማኖት ቦታ ነው።ስያሜውን ያገኘው መነኮሳቱ በአንድነት የሚመገቡበት ንፍሮ ቀቅለው ዳቤ ጋግረው ስለሆነ ነው።

ለ) **የሕግ ገዳም** ፦ ስሪታቸውና አስተዳደራቸው የአድባራት ሆነው ሳለ በቤተክህነቱ ወይም በጊዜው በነበሩ ነገስታት ገዳም በመባላቸው ነው። በስም ብቻ እንጂ አስተዳደራዊ አወቃቀራቸው የደብር ስሪት ነው።

2. ***የደብር ስሪት*** ፦ብዙውን ጊዜ በከተማና በታሪክ ቦታዎች የሚመሰረቱ ሲሆን የእነዚህ አድባራት አስተዳደር በርስትና በጉልት የሚተዳደሩ የነበረ ሲሆን በአሁን ጊዜ በሰበካ ጉባዔ በደብሩ አስተዳደር መሪነት የሚተዳደር ነው።
- የጥንቷ ቤተክርስቲያን ርስትና ጉልት የሚሰጣት በዘመኑ በነበሩ ነገስታት፣ መሳፍንትና መኳንንት ነበር። ይህ አሰራር ቤተክርስቲያን ተጠቃሚ አላደረጋትም ነበር። ይህም የሆነበት ምክንያት ሰዎች ኃላፊ ናቸውና ሌላ ባለጊዜ ሲመጣ ሌላ መመሪያ ስለሚያመጣ ነው። ሌላው የጎዳት ደግሞ ርስትና ጉልት የሚሰጡት ሹማምንት ለልጆቻቸው ሳይቀር እያስተላለፉ ካህኑ ኩርማን እንጀራ ሲበላ በዓመት ለሹመ ዳውላ እህሉን ይልኩ ስለነበር በካህኑ ስም የሚያተርፉትና የሚነግዱት ባለስልጣናቱ በመሆናቸው ነው።

3. ***የገጠር ስሪት*** ፦ የገጠር ቤተክርስቲያን ርስት ጉልት የለውም። ገበሬው ለሃይማኖት ካለው ፍቅር ቤተክርስቲያን ይሠራል። ለቤተክርሲቲያንም መተዳደሪያ የሚሆን የተወሰነ የእርሻ ቦታ ይመደባል። ይህም ***ሪሞ*** ይባላል። እንደ ገበዝ እና እንደ አለቃ ሆነው የሚያስተዳድሩት ገበሬዎች ሲሆኑ በዓመቱ በመስከረም ምርጫ እየተደረገ በመፈራረቅ ይመሩታል።
- የቤተ መቅደሱን ሁኔታ የሚከታተል ግን **ውስጠ ገበዝ** የሚባል ሹመት አላቸው።

1.1.2 ንዋየ ቅዱሳት

- ንዋየ ቅዱሳት ማለት የሁለት ጥምር ቃላት ሕብረት ሲሆን "ንዋይ" እና " ቅድሳት" የሚሉት ቃላት ድምር ነው።
- ንዋይ ማለት ገንዘብ፣ ጥሪት፣ ቅርስ፣ ንብረት ማለት ነው።

- ቅዱሳት ማለት ደግሞ ቅድስና፣ ክብር፣ ንፁህ ፀጋ ያላቸው የእግዚአብሔር የሆኑ የተለዩ ማለት ነው። ስለዚህም ንዋየ ቅዱሳት ማለት ከተመረጡ የተመረጡ፣ ከተለዩ የተለዩ ለዘለዓለም ስመ የሚኖርበት ምርጥ ዕቃ ማለት ነው። /1ኛ ዜና26፥26/1ኛ ዜና 28፥12/

፩. <u>የንዋየ ቅድሳት ምስጢር</u>

- **ምስጢር** ማለት ለማንኛውም ሰው የማይገለፅ ለወዳጅ የሚነገር ማለት ሲሆን እግዚአብሔር በሚያውቀው መንገድ ለልጆቹ በረቂቅ ስራው ይነግራቸዋል። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዚህ ምድር በተመላለሰ ጊዜ ሲያስተምር በምሳሌ ነበር ይኸውም እኛ ምድራውያን ስለሆንን ሰማያዊውን ምስጢር በሚገባን በምናውቀው ነገር እየመሰለ እንድንረዳው በማድረግ ነው ልክ እንደዚሁ ሁሉ ንዋየ ቅዱሳትም በምስጢር የከበሩ በምሳሌ የተነገሩ ናቸው። ምስጢር ለወዳጅ እንደሚነገር ለእኛም ይህን ምስጢር ፍቺ መረዳት እንችላለንና።

፪. <u>የንዋየ ቅድሳት ዓይነትና አገልግሎት</u>

- **ታቦት** ፡- ማለት **ማደሪያ** ማለት ነው። ማደሪያነቱም ለልዑል እግዚአብሔር ነው። ምሳሌነቱ ታቦት የእመቤታችን፣ ጽላት የጌታ አንድም ታቦት የእመቤታችን፣ ጽላት የትእብእቱ ቃሉ የአካላዊ ቃል ምሳሌ ነው። አንድም ታቦት የጌታ፣ የማይነቅዝ እንጨት የእመቤታችን ምሳሌ፣ ከማይነቅዝ እንጨት ታቦት መሰራቱ ጌታ በኃጢአት ከማትለወጥ ከእመቤታችን ለመወለዱ ምሳሌ ነው።
- **ፅላት** ፡- ማለት **ሰሌዳ** አንድም **መፀለያ** ማለት ነው። የመጀመሪያው ፅላት በግብረ አምላካዊ የተገኘች 2 ክፍሎች ያሏትና 10ቱ ትዕዛዛት የተፃፉበት ሙሴ በደብረ ሲና ተቀብሎ ሲመለስ እስራኤል ጣኦት ሲያመልኩ አይቶ ቢደነግጥ ከእጁ ወድቃ የተሰበረቸው የዕንቁ ጽላት ናት። /ዘፀ 32፥15-20/
  - ሁለተኛዋ ሙሴ በፊተኛዋ አምሳል የሠራት በግብረ አምላካዊ 10ቱ ትዕዛዛት የተፃፈባት ናት። /ዘፀ34፥1-28/ በንጉስ ሰሎሞን ዘመን ወደ ሀገራችን መጥታ በአክሱም ጽዮን እንደተቀመጠች የሚነገርለት ጽላት ናት።
  - በሐዲስ ኪዳን ጽላትም ታቦትም አንድ ነው።
- **መንበር** ፡- ማረፊያ መቀመጫ መኖሪያ የተለየ ከፍ ያለና የተከበረ የጽላት ማስቀመጫ ነው። ከወርቅ ከብር ከብረት ወይም ከእንጨት ይሰራል። በመንበር ታቦት ይቀመጥበታል ይፀለይበታል። መስዋዕት ይሰዋበታል። በመንበር በመደበኝነት የሚቀመጡ ታቦት፣ ስዕለ ማርያም ምስለ ፍቁር ወልዳ ሲሆኑ በቅዳሴ ጊዜ ስጋውና ደሙን ለመፈተት የምንገለገልባቸው ፃህል፣ ጽዋዕ ማኅፈደት፣ ዕርፈ መስቀል፣ መስቀልና ዕጣን ይቀመጡበታል።
  - መንበሩን የሚዳስሱና የሚያገለግሉበት ቀሳውስቱ ናቸው። ዲያቆናቱ ግን ከበው ይቆማሉ እንጂ መንካት አይቻላቸውም። ምሳሌነቱ መንበር የእመቤታችን፣ ታቦት/ፅላት/ የጌታ፣ አንድም መንበር የመንበረ ፀባዖት፣ ታቦት/ጽላት/ የሰማያዊ ንጉስ የጌታ ልዑካን የሠራዊተ መላዕክት ምሳሌ ነው።
- **ፃሕል** ፡- ከወርቅ፣ ከብር፣ ከነሐስና ከብረት የሚሰራ ጎድጓዳ ወይም ዝርግ ወጭት/ሳህን/ ነው። በኦሪት ጎብስተ ገፅ ይቀርብበት ነበር። ዛሬም ከመንበሩ ላይ ሆኖ የጌታ ስጋ ይቀመጥበታል።
  - ምሳሌነቱ ፃሕል የእመቤታችን ፣ የጌታ ቅዱስ ስጋ የክርስቶስ እመቤታችን ጌታን በማኅፀኗ የመሸከሟ ምሳሌ ነው። አንድም ፃህል ጌታ የተወለደበት ግርግም ምሳሌ ተወልዶ አድሮባታልና። አንድም ፃሕል የጌታ መቃብር ምሳሌ ነው። ሦስት ቀን ሦስተ ሌሊት አድሮበታልና። /ምሳ 25፥11/ ማቴ 14፥8/ 2ኛ ዜና 4፥8/ ማቴ 23፥25/
- **ጽዋዕ** ፡- ከተለያየ ማዕድናት ሊሰራ የሚችል ሲሆን ጽዋዕ አገልግሎቱ የጌታችን ክቡር ደም የሚይዝ የሚከብርበት ምርጥ ዕቃ ነው።
  - ምሳሌነቱ ጽዋዕ የእመቤታችን ማኅፀን ጌታ የተሸከመችበት ምሳሌ ነው። አንድም ጽዋዕ መላዕክት ከጌታ ጎን በዕለተ አርብ የፈሰሰውን ደም ተቀብለው በዓለም ሁሉ የረጨበት የብርሀን ጽዋዕ ምሳሌ ነው። አንድም የጌታ መቃብር ምሳሌ ነው።



- **እርፈ መስቀል** ፡- የደሙ ማቀበያ (መጨለፊያ) ሲሆን ከእጀታው መስቀል ይኖረዋል፡፡ ከብዙ ማዕድናት ሊሠራ ቢችልም ነገር ግን ጽዋው ከተሰራበት ቁስ በተመሳሳይ ማዘጋጀት አለበት፡፡
  - ምስጢሩ፡- ኢሳይያስ ከንፈሩን ከለምፅ የነፃበት ፍህም የያዘ ጉጠት ምሳሌ ነው፡፡ ኢሳ 6፥6 አንድም ክርስቶስ ጎኑን የተወጋበት ጦር ምሳሌ፣ ከወደ መያዣው ያለው መስቀል የጌታችን ደም መስቀል ላይ መፍሰሱን ያመለክታል፡፡
- **ዐውድ** ፡- በቁርባን ጊዜ ፃህሉ የሚቀመጥበት ዕቃ ነው፡፡ ቅዱስ ስጋው እንዳይወድቅ /እንዳይነጥብ/ መከለያ ይሆናል፡፡
  - ምስጢሩ ፡- ዐውድ ማለት **አደባባይ** ማለት ነው፡፡ ጌታችን በጲላጦስ አደባባይ የፈረደበት ምሳሌ ነው በቅዳሴ ጊዜ በሕዝቡ ፊት የሚቆመው ዐውድም የዚህ ድርጊት ምሳሌ ነው፡፡
- **አጉበር** ፡- ዐውድ ላይ የሚደፋ ከእንጨት ወይም ከብረት የተሰራ ሦስት እግር ያለው ሆኖ አገልግሎቱም ከላይ የሚለብሰው ልብስ ስጋውን እንዳይነካ የሚከላከል ክብር የሚሰጥ ነው፡፡ ምሳሌነቱም ጌታ ተቀብሮበት የነበረው ማኅተመ መቃብር ነው፡፡
- **ማኅፈዳት** ፡- ከተመረጠ ጨርቅ የሚሠራ የስጋውና የደሙ መሸፈኛ ነው፡፡ አምስት ማኅፈዳት አገልግሎት ይሰጥባቸዋል፡፡ አንድ በፃሕሉ፣ አንድ በዕዋው፣ ሦስቱ ጎብስተ ቁርባን ይሸፈንባቸዋል፡፡ ሦስቱም እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡
  - ዐውዱ የሚለብሰው ምሳሌነቱ የእመቤታችን ድንግልና
  - ፃሕል ላይ ያለው ምሳሌነቱ የሰፋድል (በማኅፀን ውስጥ ያለ የሕፃን መጠቅለያ)
  - በጎብስቱ ላይ ያለው ማኅፈድ አኅበር ላይ ያሉት ሦስቱ የአብ፣ የወልድ፣ የመንፈስ ቅዱስ ምሳሌዎች ናቸው፡፡ አብ ለማጽናት፣ ወልድ በተለየ አካሉ ስጋን በመዋሐዱ፣ መንፈስ ቅዱስ ለማንፃት አድርበውታልና፡፡
  - አንድም ማኅፈድ የጌታ ሰበን ምሳሌ ነው፡፡
- **መሶበ ወርቅ** ፡- መስዋዕት ማክበሪያ ነው፡፡ ዲያቆን በራሱ ተሸክሞ መስዋዕቱን ከቤተልሔም ወደ መቅደሱ ያቀርብበታል፡፡ ምሳሌነቱ መሶብ የእመቤታችን፣ ወርቅ የንፅህናዋ፣ የቅድስናዋ፣ ጎብስቱ የጌታ፣ ዲያቆኑ የትንቢተ ነቢያት ምሳሌ ፣ ከቤቴልሔም ወደ መቅደስ መምጣቱ ጌታ ነቢያት (በተናገሩለት) ትንቢት መሠረት በቤቴልሔም ተወልዶ በቀራንዮ የመሰዋቱ ምሳሌ ነው፡፡
  /ዕብ 9፥4/
- **ጽንሐሕ /ማዕጠንት/** ፡- የዕጣን ማሽተቻ (ማጠኛ) ዕቃ ነው፡፡ /ዘሌ 16፥12/ ዕብ 9፥4/ የሚሠራው ከተለያዩ የእሳት ባሕር መቋቋም ከሚችሉ ማዕድናት ሲሆን እያንዳንዱ ጌጥ ቁጥሩ ሳይዛባ የተዘጋጀ መሆን አለበት፡፡
  - ምስጢሩ ፡- ጽንሐሕ የእመቤታችን፣ ፍህሙ የመለኮት ምሳሌ፣ በሦስቱ ሐብሎች መኃል ያለው ሐብል የወልደ እግዚአብሔር፣
    - ዘንጉ መውጣት መውረዱ፡-
      - መውረዱ፡- ወልድ ከሰማየ ሰማያት ወረደ ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወለደ
      - መውጣቱ፡- ትንሳኤውና እርገቱ ሲሆን
      - እንደገና መውረዱ፡- ዳግም ለመምጣቱ (ለዳግም ምፅአቱ) ምሳሌ ነው፡፡
    - መያዣው አንድ መሆኑ የሥላሴ የአንድነታቸው ነገር ምሳሌ በሐብሎቹ ላይ ያሉት ሻኩራዎች ብዛት ቢያንስ 12 ቢበዛ 24 መሆን አለበት፡፡ 12 ቢሆን በሐዋርያት 24 ቢሆን በካህናተ ሰማይ ምሳሌ
    - ሻኩራው የሚይዙት ዘንጎች ሦስት መሆን የሥላሴ፣ የሻኩራዎቹ ድምፅ ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እያሉ የሚያመሰግኑ መላዕክት ድምፅ ምሳሌ ነው፡፡ ክዳኑ ላይ ያለው መስቀል በቀራንዮ መሰቀሉን /ዘጉ 16፥16-25/ ዘሌ 10፥1-2/ 1ኛ ነገ 7፥50/ ራዕ 8፥3-5/
    - ጽንሐው መጨረሻ ያለችውን መስቀል ይዘው ማጠን የሚችሉት ቀሳውስቱ ናቸው፡፡ ለአገልግሎት ግን ዲያቆኑ መኃል ላይ የሻኩራዎቹን መንጠልጠያ ገመድ ይዞ ሊታዘዝ ይችላል፡፡



✞ **ዕጣን** ፡- ለቤተመቅደስ የተዘጋጀ መስዋዕት ሆኖ የሚጨስና ፀሎት ማሳረጊያ ነው፡፡ ቅዳሴን ጨምሮ በሌሎች መንፈሳዊ አገልግሎቶች ጊዜ የሚቀርብ መባዕ ነው፡፡ ዕጣን መልካም ነጭ (ፀዓዳ) የሆነ ሲሆን 24ቱ ካህናተ ሰማይ በእግዚአብሔር ዙፋን ፊት እየሰገዱ ለዓለም ድኅነት የሚለምኑበት ነው፡፡ /ራዕ 8፥3-5/ ማቴ 2፥11/ መዝ 140፥2/ በመሆኑም ንፅህና ነውር የሌለበት መዓዛው ያማረ ሊሆን ይገባዋል፡፡ /ዘፀ 30፥35/ የተመረጠና ለእግዚአብሔር የሆነ ዕጣን ከመቅደስ ውጭ ለግል መጠቀም አልተፈቀደም፡፡ /ዘፀ 30፥38/

▪ ምሳሌነቱ ዕጣን የቅዱሳን፣ ጢሱ የምስጋናና የፀሎት፣ ሽታው(መዐዛው) የመልካም ስራቸው፣ የጢሱ ማረግ የቅዱሳን ፀሎት ወደ እግዚአብሔር ፊት መድረሱ፣ ጢሱ እንደ ደመና ምዕመናን/ት ላይ ሲያጅብ መታየቱ እግዚአብሔር ከእኛ ጋር መሆኑን ያስረዳል፡፡

✞ **ሙዳይ** ፡- መክተቻ (ሙዳዬ ዕጣን) ነው፡፡ አገልግሎቱ ዕጣን ማስቀመጫ ነው፡፡ በቅዳሴ ጊዜ ከሙዳይ ውስጥ አምስት ቆቆር ዕጣን ይቀመጣል፡፡ ምስጢሩም ሙዳይ የእመቤታችን በሙዳይ ውስጥ አምስት ራስ ዕጣን መቀመጡ የአምስቱ ኪዳናት ምሳሌ፡-

ሀ. የቁርባነ አቤል
ለ. የመስዋዕተ ኖኅ የሂሩተ አብርሃም
ሐ. የመብዐ ይስሐቅ
መ. የተልዕኮ ሙሴወአሮን
ሠ. የመስዋዕተ መልኬ ጼዴቅ ናቸው ፡፡

✞ **ሞፍሐም** ፡- ለማዕጠት የሚሆነው እሳት የሚቀጣጠልበት ነው ቦታው ከመቅደሱ ውጭ በመዘጋጃ ክፍል ወይም በምስራቅ ደጃፍ ነው፡፡

✞ **ጉጠት** ፡- ፍሕም የሚያዝበት ነው፡፡ /ኢሳ6፥6/

✞ **መኮስተሪያ** ፡- የመብራቱ ጫፍ ማስተካከያ (ሲጎብጥ ማቅኛ) ነው፡፡ /ዘፀ 25፥38/ 1ኛ ነገ 7፥49/ ምሳሌነቱ መብራቱ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ፣ ክሩ የአካለ ስጋ፣ መኮስተሪያው የአካለ መለኮት፣ መኮስተሪያው ሲያቃና በወንጌል መዶሻ መምህራንና ሰባኪያን የተሰናከሉትን ሲያቀናላቸው፡፡

✞ **ስንና ብርት** ፡- እንደ ማንቆርቆሪያ ያለ መታጠቢያ ነው፡፡ አንዳንዴ መቁረሪት ወይም ኩስኩስት ይሉታል፡፡ **ስን**...<u>**ውሃ መያዣው**</u> ሲሆን **ብርት**...<u>**ማስታጠቢያው**</u> ነው፡፡ ምሳሌነቱ ስንና ብርት ጲላጦስ "ከዚህ ሰው ደም ንፁህ ነኝ..." ብሎ እጁን የታጠበበት ምሳሌ ነው፡፡ /1ኛ ነገ 7፥38-39/ ማቴ 27፥24/

✞ **መቅረዝ /ተቋመ-ማኅቶት/** ፡- የመብራት መስቀያ /ማስቀመጫ/ ነው፡፡ የብሉይ ተቀዋም እንደ ዕዋ እግርና ሰባት ቅርንጫፎች ያሉት ባለዘንግ ነበር፡፡ /ዘፀ 25፥31-40/ ዕብ 9፥2/ ዛሬም በሐዲስ ኪዳን ያለው አገልግሎት ተመሳሳይ ነው፡፡ በዘይቱ ፋንታ ሻማ ይበራበታል፡፡ መብራቱ ቢያንስ ከሁለት ሊያንስ አይገባውም፡፡

▪ ምሳሌነቱ መቅረዝ የእመቤታችን መብራቱ /ብርሃን/ የጌታ ዘይት የመንፈስ ቅዱስ ቅርንጫፎቹ የምዕመናን ቅርጫፎቹ 7(ሰባት) መሆናቸው የእመቤታችን ፍዕምትነት ያጠይቃል፡፡ ሰባት ቁጥር በዕብራውያን ፍፁም ነውና፡፡ " *እስመ ኃልቀ ሳብዕ በኀበ ዕብራውያን ፍፁም ውእቱ* " እንዲል፡፡

✞ **አትሮንስ /መንበረ መፃሕፍት/** ፡- የመፅሐፍ ማስቀመጫ ሲሆን አንባቢንና ሰባኪያን መጽሐፋቸውን የሚያስቀምጡበት የቤተክርስቲያን ንዋይ ነው፡፡ ምሳሌነቱ አትሮንስ የእመቤታችን ማኅፀን ምሳሌ ሲሆን በላዩ ላይ ያለው መፅሐፍ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌ ፣ አንድም አትሮንስ የጌታ ዙፋን፣ መጽሐፉ ደግሞ ጌታን ያጠይቃል፡፡

✞ **ጧፍና ሻማ** ፡- ከሰምና ከፈትል የሚዘጋጅ ለብርሃን መስጫ መገልገያ ነው፡፡ ምሳሌነቱ የመላዕክት ምሳሌ ነው፡፡ ብርሀኑ ደግሞ የኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌ ነው፡፡ /ዮሐ 8፥12/ አንድም የሰማዕትነት ቅዱሳን ሰማዕታት እየነደዱ ብረሃን መስጠታቸው ፣ አንድም የሊቃውንት፣ ሊቃውንት ብርሃን ሁሉም እንዲያዩ የረቀቀውን ምስጢር ይገልጣሉና፡፡

✞ **መጥቅዕ /ደወል/** ፡- ከጠንካራ ብረት መሰል ድንጋይ ይዘጋጃል፡፡ አገልግሎቱ ሌሊት ከሰዓታትና ማኅሌት በፊት በያም ቀን ስድስት ሰዓት ሲሆን ተጋብኦ ተብሎ ይደወላል፡፡ ምዕመናንን

ለማንቃት ደወላል፡፡ ምሳሌነቱ ደውል የትንቢተ ነቢያት ምሳሌ ነው፡፡ ኖኅ በመርከብ በነበረበት ዘመን ጧት /ነግህ/፣ ቀን /ቀትር እና ምሽት/ሠርክ/ ይደውል ነበር፡፡

<u>በአጠቃቀም ያለው ምሳሌነትና ምስጢር</u>

- **ከቅዳሴ በፊት** - አምስት ጊዜ መደወሉ አምስቱ አዕማደ ምስጢር ምሳሌ አንድም የትንቢተ ነቢያት ምሳሌ ነው፡፡
- **የቅዳሴ መግቢያ** - የዮሐንስ ስብከት ነው፡፡ የብሉይ መዝጊያ የሐዲስ ኪዳን መጀመሪያ ነውና፡፡
- **የወንጌል** - የሐዋርያት፣ የ72ቱ አርድዕት ምሳሌ
- **ፍሬ ቅዳሴ ከመጀመሩ በፊት ዲያቆኑ ፃሁ ሲል** ሦስት መደወሉ የሥላሴ
- **የእግዚኦታ** - የእመቤታችንና የዮሐንስ ለቅሶ
- **የድርገት** - የዮሴፍና የኒቆዲሞስ ለቅሶ ምሳሌ ነው፡፡

✞ **ቃጭል** :-ከተለያ ማዕድናት ሊዘጋጅ ይችላል፡፡ 4 ጊዜያት ቃጭል ይቃጨላል፡፡

- **የቅዳሴ መግቢያ-** የብስራተ ገብረኤል ሠራዒ ዲያቆን ያቃጭላል፡፡
- **የፃዉ-**የዮሐንስ ስብከት
- **የእግዚኦታ-** የጌታ ትምህርት
- **የድርገት-** የሐዋርያትና የ72ቱ አርድዕት ስብከት ምሳሌ ነው፡፡

✞ **መስቀል** :- በብሉይ ዘመን የርጉማን የነበረው መስቀል ጌታ በቀራንዮ ተሰቅሎ የነፃነት አርማ የሰላም ምልክት አድርጎታል፡፡ /1ኛቆሮ 1፥18/

- በቤተክርስቲያን ብዙ አይነት የመስቀል ማዘጋጃ (መስሪያ ቁስ) አለ፡፡ እነሱም እንጨት፣ ወርቅ፣ ብር፣ ነሐስ፣ መዳብና ብረት ይገኙበታል፡፡
- በእንጨት ቢሰራ ጌታችን የተሰቀለበት ዕፀ መስቀል፣ በወርቅ ቢሰራ ደግሞ ንፅሐ ባህርይ አምላክ ስለሆነ፣ በብር ቢሰራ በይሁዳ አማካኝነት በ 30 ብር ለመሸጡ የነሐስ መስቀል ቢሆን የብሩኅነቱ ምሳሌ፣ በብረት ቢሰራ ደግሞ የተቸነከረበት ኃጉን የተወጋበት ብረት ምሳሌ ፣ በመዳብ ቢሰራ የአማናዊው ደሙ ምሳሌ ይሆናል፡፡

- ***<u>ቤተክርስቲያናችን መስቀልን በተለያየ መንገድ ትጠቀምበታለች</u>***
  1. የመፆር መስቀል መቀደሻ ከቅዳሴ በኋላ ካህኑ ምዕመናንና ምዕመናትን የሚባርክበት
  2. በንዋየ ቅዱሳት ላይ በስዕል በጥልፍና በቅርፅ የሚዘጋጅ
  3. ካህናት የሚይዙት መባረኪያ/መሳለሚያ/ መስቀል
  4. ምዕመናትና ምዕመናት በአንገታቸው የሚያስሩት መስቀል
  5. በቤተክርስቲያን እና በቤቴልሔም ጉልላት ላይ የሚሰቀል መስቀል ናቸው፡፡

<u>የመስቀል አይነቶች</u>

✞ ከአሰራራቸውና ከአጠቃቀማቸው አንፃር የተለያየ ስያሜ ያላቸው መስቀልን እንመልከት፡፡

፩. ቀራንዮ ሐዋርያ መስቀል	፮. አርዌብርት መስቀል	፲፩. ትእምርተ ከዋክብት መስቀል
፪. ቀርነ በግዕ መስቀል	፯. ልሳነከለባት መስቀል	፲፪. እሳተ ጋቡእ መስቀል
፫. ዕፀ ሳቤቅ መስቀል	፰. ትእምርተ ንትፊት መስቀል	፲፫. ለንጊኖስ መስቀል
፬. ዕፀ ሰርናይ መስቀል	፱. ሐረገዌን መስቀል	
፭. ጽጌ ዳንጉላ መስቀል	፲. ዓመደ ዓለም መስቀል	

<u>የመወያያ እና የቤት ስራ ጥያቄ</u>

1) ከላይ የተጠቀሱትን የመስቀል ዓይነቶች ስያሜያቸውን እንዴት አገኙ ታሪካዊ ዳራቸውንና ሃይማኖታዊ ፍቺያቸውን አብራርታችሁ ፃፉ፡፡
2) መስቀል መሳለም መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርቱን አብራርታችሁ ፃፉ፡፡

፫. ቅዱስ አልባሳት

- ✓ ቅዱስ አልባሳት በቤተክርስቲያናችን ውስጥ ካህናት ሊቃውንት የሚለብሱአቸው እንዲሁም ንዋየ ቅዱሳት የሚጎናፀፉአቸው (የሚሸፈኑባቸው) ናቸው።

❖ ***ልብሰ ተክህኖ***

- በፀሎትና በቅዳሴ ጊዜ እንዲሁም በተለያዩ የቤተክርስቲያናችን አገልግሎት ካህናት የሚለብሱት ነው። /ዘፀ 31፥10-11/ ዘፀ 39፥29/ ዘፀ 28፥40-42/

ሀ. **የቀሳውስት ቀሚስ**

- ❖ ቀሚስ የሚለው ቃል ከዐረብኛ የመጣ ሲሆን ይኸው በጥንት ዘመን አብዲላከኒ ቀሚስ የሚባል ነበር። የሚቀድሱ ካህናት ነጭ ልብስ እንዲለብሱ ፍትሐ ነገስት ያዛል። ካህናት ልብሰ ተክህኖ ከመልበሳቸው በፊት በጸጸሳት እንዲያስባርኩ ጳጳስ ካልኖረ ግን ከመካከላቸው ከፍ ያል ባርከው እንዲለብሱ ተደንግጓል።
- ❖ ካህናት የሚለብሱት ልብሰ ተክህኖ እስከ ተረከዛቸው መድረስ አለበት። ከለበሱ ማውለቅ የለባቸውም። ከረዘመ እንኳን በዝናር /በቀበቶ/ መሠብሠብ ይገባቸዋል።
- ❖ ምሳሌነቱ ጌታ ከተወለደ ጀምሮ ያደርጋት የነበረች ቀሚስ ምሳሌ ሲሆን ጌታ በመጨረሻ ሲሰቀል ይሕች ቀሚስ እንዳላደረገ ካህናት በአዘቦት ልብሳቸው መቀደስ የተከለከለ ነው።/ዘፀ 28፥35/ ዘፀ 39፥1-5/

ለ. **ካባ**

❖ መደረቢያ ነው። ከቀሚስ በላይ የሚደረግ ነው። ካባ አምስት መንዲል /ክልጅ/ እንዲኖረው ታዟል። መንዲሉ እንደ ላንቃ እየሆነ ስለሚወርድ ካባ ላንቃ ተብሏል።
❖ ምሳሌነቱ አምስቱ መንዲል የካህኑ እምነት በአምስቱ አዕማደ ምስጢር ላይ የተመሠረተ መሆኑን ያጠይቃል።

ሐ. **ሞጣሕት**

- ❖ በአንገት ጠልቆ የሚገባ ከቀሚሱ ላይ የሚደረብ ፊት ለፊት ረዘም ብሎ የሚወርድ ልብስ ነው።
- ❖ ምሳሌነቱ የፍኖተ ቅዱሳን ምልክት ነው። ከፊት መርዘሙ ረጅም መንገድ ይጠብቅሀል አሁን ካሳለፍከው ገና የምታሳልፈው ይረዝማል ማለት ነው።

መ. **ቆብ**

- ❖ መነኮሳትና በሕግ ያሉ ቀሳውስት ቆብ እያደረጉ ይቀድሳሉ። እንዲሁም በማንኛውም አገልግሎት ከጭንቅላታቸው አይጠፋም የመቀደሻው ግን የተለየ አክሊል የመሰለ ነው። መሪጌታዎቹ ጥምጥም ያደርጋሉ።
- ❖ ምስጢሩ በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ራስ ላይ አይሁድ የደፉት የሾህ አክሊል ምሳሌ ነው። /ዘፀ 28፥40/ ዘፀ 8፥9/ ዘፀ 29፥6/

ሠ. **ጥምጥም /ሰበን ወይም በፍታ/**

- ❖ ሰበን የራስ ልብስ ጌጥ ሽልማት ጥምጥም ማለት ነው። /ዘካ 3፥5/
- ❖ ምሳሌነቱ ቅዱስ ቶማስ ከህንድ ወደ ኢየሩሳሌም በደመና ተጭኖ ሲመለስ እመቤታችን ስታርግ አግኝቶ ለምልክት የሰጠችው ሰበኗ ምሳሌ ነው። አንድም የእመቤታችን ምሳሌ ነው።

ረ. **ፈርጂያ**

- እጀ ሰፊ ቀሚስ የጳጳሳት ቀሚስ ማለት ነው፡፡
- ምሳሌነቱ ቀሚሱ ኢየሱስ ክርስቶስ ለብሶት የነበረው/ መክፈዕተለምዕ/ ሲሆን እጅጌው ሰፊ መሆኑ ደግሞ ብዙ መክሊት መቀበላቸውና ብዙ አደራ እንዳለባቸው ያመለክታል፡፡

ሰ. **አክሊል**

- ከመልካም ጨርቅ የሚዘጋጅ መሀሉ ላይ መስቀል ያለበት ሆኖ ይዘጋጃል፡፡
- ምሳሌነቱ የድል አክሊል /የሕይወት አክሊል/ ረጅሙ የቅዱሳን መንገድ ስንፈፅም የምናገኘው ፡፡ /2ኛ ጢሞ 4፥7-8/

ሸ. **አስኬማ**

- ጳጳሳት የሚያደርጉት እና ከራሳቸው የሚደፉት በቆብ ደረጃ የመጨረሻው ማዕረግ ነው፡፡
- ምሳሌነቱ በክርስቶስ ራስ የተደፋበት የሾህ አክሊል ምሳሌ ነው፡፡

❖ ***ልብሰ ታቦት***

- ከተመረጡ መልካም ጨርቅ የሚዘጋጅ ጌጥና ዘርፍ ያለው ታቦት የሚከብርበትና የሚጎናፀፈው ነው፡፡

ሀ. **መጎናፀፊያ**

- መንበሩ የሚለብሰው ሆኖ ታቦት በክብረ በዓል ጊዜ ሲወጣ የሚጎናፀፈው ነው፡፡

ለ. **ቀፀላ**

- ታቦቱ መጎናፀፊያውን ከተጎናፀፈ /ከለበሰ/ በኋላ ከላይ የሚደረግ ባለጌጥ ዘርፈ ልብስ ነው፡፡ /1ኛነገ 21፥38-41/ ኢሳ 3፥9/ ራዕ 12፥3/ ባሮ 5፥2/

ሐ. **ማክበሪያ**

- ታቦት ማክበሪያ (ታቦት መሸከሚያ) ለታቦት ክብር በራስ ላይ አስቀድመው የሚያኖሩት ነው፡፡

✓ ***መጋረጃ /መንጦላዕት/***

- አገልግሎቱ ለመቅደሱ ክብር የሚሰጡና ምዕመናንንና ምዕመናትን ለመለየት ነው፡፡ ምሳሌነቱ የኪሩቤል ነው፡፡ ክንፋቸውን ፀንፍተው የመከለላቸው፡፡ መጋረጃ ለሁለት የተከፈለበት ምክንያት ጌታ በተሰቀለ ሰዓት የቤተመቅደስ መጋረጃ ለሁለት ከላይ ታች የተከፈለበት ምሳሌ ነው አንድም የስጋ የነፍስ ምሳሌ ነው፡፡/ዘፀ 26፥7-10/ ማቴ 27፥51/ ዕብ 10፥20/ የሐዋ 11፥5/

✓ ***ምንጣፍ***

- የወለል ላይ ልብስ መረገጫና ለወንበርም ይዘጋጃል፡፡ ለወለል የሚዘጋጅ ምንጣፍ ምንም ዓይነት ስዕል ሊኖረው አይገባም፡፡
- ምሳሌነቱ በሆሳዕና ዕለት ለጌታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ በአህያ ውርንጭላ ተቀምጦ ሲሄድ ያነጠፉለትን የዘንባባ ዝንጣፊ ለክብሩ ሲሉ ያነጠፉለትን ምሳሌ አንድም እግዚአብሔር እስራኤልን እንቅፋት ሳይመታቸው እሾህ ሳይወጋቸው የብርሀን ደመና አንጥፎ መምራቱ የሚያስታውሰን ነው፡፡

✓ ***ድባብና ጥላ (ፀላል)***

- ❖ ታቦት በሚከብርበት ጊዜ ጥላ ይዘረጋል። በቅዳሴ ጊዜ ጥላ አገልግሎት አለው። ይኸውም ወንጌል ሲነበብ ቅዱስ ቁርባን ከቤቱልሔም ሲመጣ በአጠቃላይ ክቡር የሆነ ነገር የሚጠለልበት ነው።
- ❖ ምሳሌነቱ ሙሴ የኪዳኑን ታቦት ሲቀበል የጋረደው ደመና ምሳሌ ነው።

✓ **ግምጃ**

- ❖ አገልግሎቱ ለቅዱሳን መዛህፍት መሸፈኛና ለሌሎች ንዋያተ ቅዱሳን ልብስ ያገለግላል። /ምሳ 31፥22/

✓ **ማኅደር**

- ❖ ከቆዳ የሚሰራ የቅዱሳን መዛሕፍት መክተቻ፣ ማኖሪያ፣ ማሳደሪያ ነው።
- ❖ ምሳሌነቱ ማኅደር የእመቤታችን፣ መፅሐፍ የጌታ ምሳሌ ነው።

፬. የዜማ ንዋያት

- ዜማ ስልት ያለው ጩኸት ማለት ነው። የሰዎች ዜማ በ 3 ይመደባል። **ግዕዝ፣ ዕዝልና አራራይ** ናቸው።

የዜማ ዕቃዎች /ንዋያት/ በሦስት መደብ ይከፈላሉ፡-

፩. በክር የሚመቱ (የሚከረከሩ) ፡- በገና፣ መስንቆ

፪. በትንፋሽ የሚነፉ ፡- መለከት፣ እንቢልታ፣ ዋሽንት

፫. እርስ በርስ በመማታት ድምፅ የሚሰጡ ፡- ከበሮ፣ አታሞ፣ ነጋሪትና ፅናፅል ናቸው።

1. **በገና** ፡- አስር አውታር ያለው ከጅማት የሚዘጋጅ ነው። ርዝመቱ የረዘመ ሆዱ ሰፋ ያለ ነው። ምሳሌነቱ በገና የእመቤታችን ምሳሌ ነው። አስሩ አውታር የአስርቱ ቃለተ አሪት ምሳሌ ነው። ግራና ቀኝ ያሉት ሁለት ዓምዶች የፍቅረ ቢፅና ፍቅረ እግዚአብሔር ምሳሌዎች ናቸው። አንድም ሁለቱ ዓምዶች በብሉይና በሐዲስ ይመሰላሉ። የበገና ትልቅና ግዙፍነት እግዚአብሔር በሁሉ ቦታ የሞላ /ምሉዕ በኩለሔ/ መሆኑን ያመለክታል።
   /ዘፍ 31፥27/ ኢሳ 5፥2/ ዳን 3፥5/ 2ኛሳሙ 6፥5/ ሲራ 40፥21/ ራዕ 5፥8/ መዝ 32፥2/ ሰቆ 5፥14/
2. **መስንቆ** ፡- መስንቆ አንድ ምሰሶና አንድ ክር ያለው የዜማ መሳሪያ ነው። ክሩ ከፈረስ ጭራ ይዘጋጃል። ምሳሌነቱ መስንቆ የእመቤታችን ፣ አንድ ምሰሶ የአንዲት ሃይማኖት፣ ክሩ አንድ ወራጅ አንዲት ጥምቀት፣ ክሩ ዕጣን ሲቀባ ድምፅ መስጠቱ የመንፈስ ቅዱስ፣ ክሩ የጥምቀት ዕጣኑ የመንፈስ ቅዱስ እንደሆነ ልጅነት በመንፈስ ቅዱስ ይገኛልና። ደጋኑ (መከርከሪያው) የኖኅ ቃልኪዳን ምሳሌ ነው። ሲመሳቀል የሚሰጠው መስቀል የክርስቶስ መስቀል ምሳሌ ነው። /ሲራ 40፥2/ መዝ 32፥2/ ዳን 3፥10/ 2ኛነሴና 29፥25/ 2ኛሳሙ 6፥5/ ኢሳ 5፥12/
3. **እምቢልታ** ፡- ከቀርከሃና ከቱቦ መሰል ነገር የሚዘጋጅ ነው። ከዋሽንት በመጠን የሚተልቅ ነው። ታቦት ሲወጣ (ሲከብር) ይዘመርበታል። ነገስታት ግብር ሲያስገቡ የሚያስነፉት ነው። በእምቢልታ መዝሙር ይዘመርበታል። /መዝ 150፥4/ ዳን 3፥15/ ማቴ 9፥13/ ኢዮ 30፥31/ ኢሳ 5፥12/ 1ኛነሴና 15፥28/
4. **መለከት** ፡- ከከብት ቀንድ ከሌላም ብረት ነክ ነገር ሲሰራ ይችላል። በአዋጅ መንገሪያና ለመዝሙር ያገለግላል። /2ኛሳሙ 6፥15/ ዘኁ10፥1/ 2ኛነሴና 5፥12/ ማቴ 24፥31/ ኢያ 6፥20/ ዘፍ 4፥21/
5. **ዋሽንት** ፡- ከሸንበቆ ወይም ከቀጭን ቀርከሃ ከብረትም ሊሰራ የሚችል የዜማ ዕቃ ነው። ዋሽንት አራት ቀዳዳዎች አሉት። ምሳሌነቱ አራት ቀዳዳዎች በአራቱ ወንጌላዊያን የሚወጣው ድምፅ እንደሚማርክ የወንጌል ቃል ጣፋጭነት ያስረዳል። /ዳን 3፥5/ ዳን 3፥10/ ዳን 3፥15/
6. **ከበሮ** ፡- ከእንጨት ተዘጋጅቶ በጠፈርና በቆዳ የሚለጎም /ንዋየ ማኅሌት/ ነው። ከበሮ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ይመሰላል። ምሳሌነቱ አፉ ሁለት ነው ሰፊው ምሉዕ በኩለሄ ጠባቡ ደግሞ



በአጭር ቁመት በጠባብ ደረት መወሰኑን፡፡ ጠፍሩ ጌታን አይሁድ ሲገርፉት ጅራፍ በወገቡ ያሳየው ሰንበር፣ ከበሮ የምንሸከምበት ገመድ የጅራፍ ምሳሌ፣ ከበሮው የሚለብሰው ሱቲ ጌታችን የለበሰው ቀይ ግምጃ ምሳሌ ነው፡፡ /መዝ 150፥4/ 2ኛሳሙ· 6፥5/ ዘፍ 31፥27/

7. **ጽናጽል** ፡- ከተለያዩ ማዕድናት ሊሰራ የሚችል በውስጡ የብረት ቅጠል (መርገፍ) ይደረግበታል፡፡ ፅናፅል ከከበሮ ጋር አብሮ የሚሄድ የዜማ ዕቃ ነው፡፡ ምሳሌነቱ በግራና በቀኝ ያለው ዓምድ የብሉይና ሐዲስ፣ በሁለቱ አምድ ያሉት ሁለቱ ቀጫኙን ዘንጎች ያዕቆብ በፍናኖተ ሎዛ ያያት መሠላል፣ በዘንጎቹ ላይ ቅጠሎች (መርገፍ) ሊወጡ ሊወርዱ የነበሩት መላዕክት አንድም 2ቱ ልደታት፣ 3ቱ የሥላሴ ቢደመሩ አምስት ይሆናሉ፡፡ የአምስቱ አዕማደ ምስጢር፣ ወዲህ ወዲህ ማለት አይሁድ ጌታን እንዳንገላቱት ያመለክታል፡፡ /2ኛ ዜና 29፥25/ መዝ 105፥5/ 1ኛቆሮ 13፥1-2/ 1ኛዜና15፥16/ 2ኛዜና 5፥12/ 2ኛ ሳሙ·6፥5/
8. **መቋሚያ** ፡- ብዙውን ጊዜ ከእንጨት የሚዘጋጅ አንዳንዴ ቀንድና ሌሎች ማእድናት የሚጠቀም ነው፡፡ አገልግሎቱ መመርኮዣና መዘመሚያ ነው፡፡ ከከበሮውና ከጽናጽል ጋር ለዝማሜና ለሽብሸባ ያገለግላል፡፡ ምሳሌነቱ የአዳም ተስፋ ከእመቤታችን ተወልዶ በቀራንዮ በእጸ መስቀል ላይ የተሰቀለው የኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌ ነው፡፡ ካህናት በትከሻቸው አድርገው መንቀሳቀሳቸው አይሁድ ጌታን መስቀል አሸክመው ያንገላቱት ምሳሌ፣ ከዜማ ጋር አስማምተው ወደ መሬት መጣል አይሁድ ጌታን በዘንግ የመምታታቸው ብድግ አድርገው ትከሻቸው ላይ ማሳረፋቸው ጌታ መስቀል ተሸክሞ (ማሸከማቸውን) ያመለክታል፡፡
9. **አታሞ** ፡- በእጅ የሚመታ ባለ አንድ አፍ የዜማ እቃ ነው፡፡ ይህ የዜማ እቃ በዚህ ዘመን ብዙም ተጠቃሚነት የለውም፡፡ በጥንቱ ቤተክርስቲያን ግን ትልቅ የዜማ ንዋይና ለአዋጅ መጥሪያ ሆኖ አገልግሏል፡፡ /መሳ 21፥21/ 1ኛሳሙ· 18፥6/
10. **ነጋሪት** ፡- ይህ የዜማ ዕቃ ከአታሞ ጋር ይመሳሰላል በመጠኑ ግን ከአታሞ ይተልቃል፡፡ አገልግሎቱ መልዕክት ለማስተላለፍና ለክብረ በዓል ማድመቂያ ነው፡፡ ምሳሌነቱ የነጋሪተ ድምፅ የክርስቶስ ዳግም ምፅአት ምሳሌ ነው፡/ 2ኛ ሳሙ· 6፥5/

<u>የቤት ስራ ጥያቄ</u>

፩. በዜማ ንዋያት የተጠቀሱት ንዋያት ምን እንደሚመስሉ በስዕል አሳዩ?

፪. እነዚህ የቤተክርስቲያን ዕቃዎች እንዴት ከዓለማዊ ይለያሉ? ዓለማውያን ይህን ነገር መጠቀማቸው የሚፈጥረው ነገር ያለ ይመስላቸዋል?

<u>ቅዱሳን ስዕላት</u>

ስዕል በኢትዮጵያ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን በፊትም ሆነ በኋላ የታወቀና ከአምልኮት ጋር የተያያዘ ነው፡፡ ክርስትና በፊት ለቤተ አይሁድ እንደ አሕዛብ ያልሆነ በታቦተ ሕጉ በጽላተ ኪዳን ላይ ሥዕለ ኪሩብን እንዲስል ሁሉ እግዚአብሔር ለሙሴ አዞት ነበር፡፡ እነዚህም የኪሩቤል ስዕሎች ከታቦቱ አይለይም፡፡

ምክንያቱም ታቦት የእግዚአብሔር መገለጫ ዙፋን ስለሆነ የመንበረ ፀበኦት አምሳል፣ ስዕለ ኪሩብ ደግሞ የፀወርተ መንበር ኪሩቤል ምሳሌ ነው፡፡ /ዘፀ 25፥19/ 1ኛነገ 6፥23/ ሕዝ 9፥3/ሕዝ 10፥1-3/

✞ ስዕል በሐዲስ ኪዳን በቤተክርስቲያን የተጀመረበት የተለየ ታሪካዊ ምክንያት አለው፡፡ የመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች በዘመነ ሰማዕታት ዋሻ ፈልፍለው ጉድጓድ ቆፍረው በካታኮም (ግበበ ምድር) አፅመ ቅዱሳንን እየሰበሰቡ ፀሎት ይፀልዩና ያስተምሩ በነበረበት ጊዜ የሚያስተምሩበት ቅዱሳን መፃሕፍት ባለመኖራቸው በዋሻዎቹ ግድግዳ ላይ ስዕሎቹን በመሳል በምሳሌነቱ ያስተምሩባቸው ይፀለይበት ነበር፡፡ አንድም ስለሃይማኖታቸው ሲሉ በአላውያን ነገስታት ሰይፍ የወደቁትን ሰማዕታት እስከነአሟሟታቸው በስዕል ለመታሰቢያነት ይቀረጽ ነበር፡፡



- ቅዱሳን ስዕላት ክርስቲያኖች እስከ ስምንተኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ድረስ ከቆዩ በኋላ በስዕል ምክንያት በሮም በባዛንታዬን ግዛት በሚኖሩ ክርስቲያኖች ዘንድ አለመግባባት ተፈጠረ። ይኸውም የሆነበት ነገር አንዳንድ ክርስቲያኖች ስዕል ከመውደዳቸው የተነሳ ስዕሎች አማልክት ናቸው በማለታቸው የሁለቱን ክፍሎች ሃሳብ በሚጣጣም መልኩ በመመርመር በ784ዓ.ም ጉባዔ ተደርጎ ለስዕል ክብርና ስግደት እንደሚገባ ቀኖና ተሠራ።
- ልብ ማለት ያለብን በስዕል ፊት ቆሞ መፀለይ ከባለ ስዕሉ ረዲኤትን በረከትንና ምጃን ለማግኘት ነው እንጂ ስዕሉ መለመናችን አይደለም። ይልቅስ ለስዕሉ ባለቤት ክብርና ፍቅርን መግለፃችን ነው።

<u>ለምሳሌ</u>፡- በሐዋርያት ዘመን ብዙ ሕመማን በጥላቸው ይፈወሱ እንደነበር ተፅፎ እናገኛልን። /ሐዋ 5፥15/ እንግዲህ በጴጥሮስ ስዕል ፊት ቆመን ብንለምን የምንሻውን አናገኝም? ቅዱስ ጳውሎስም የልብሱ እራፊ አየቆረጡ በመውሰድ ከደዌያቸው ይፈወሱ ነበር። /ሐዋ19፥11-12/

- ከነዚህ የመፅሐፍ ቅዱስ ትምህርቶች የምንረዳው ስዕልን ማክበር የስዕሉን ባለቤት ማክበር ስእሉ ፊት መስገድ ለስዕሉ ባለቤት መስገድና መለመን እንደሆነ ነው።

<u>የጌታ ስዕል ምንጭ</u>

፩. ከ14 እስከ 37 ዓ.ም የነበረው ጢባርዮስ ዮሐንስ ወንጌላዊ የሳለው ስነ-ስቅለት

ጌታ የተሰቀለውም በእሱ ዘመን ነው ጢባርዮስ የሚወደው አንድ ልጅ ነበረው። እሱም ሞተበት። በልጁ ሞት በጣም አዘኖ ሬሳው ሳያስቀብር ሰነበተ። ጌታም በኢየሩሳሌም ያደርገው የነበረው ተዓምራት ያውቅ ስለነበር ጌታ የሰማይ የምድር ገዥ መሆኑን ፅፎ የምልጃ የልመና ጽህፈቱንና የልጁን ሬሳ ወሰደው። ጎልጎታ (የጌታ መቃብር) ላይ እንዲያኖሩልት በባለሟሎቹ ላከ። እነርሱም ሄደው ደብዳቤውን እና የልጁን ሬሳ በጌታ መቃብር ላይ ሲያኖሩት ሬሳው ቀና ብሎ ተነስቷል።

ጢባርዮስም ከደስታው ብዛት የተነሳ የጌታን ውለታ ለመክፈል እናቱ ማርያምን አምጡልኝ። እኔ ቋሚ፣ ለጓሚ ሚስቱ ገረድ ደንገጡር ሆነን እናገለግላታለን አለ። ነገር ግን የድንግል ማርያም ክብር ሰማያዊ እንጂ ምድራዊ ስላልሆነ ተሰውራባቸው አላገኟትም።

ጢባርዮስም ተስፋ ሳይቆርጥ ዮሐንስ ወንጌላዊ በዕለተ አርብ ላይ እንዳየው አድርጎ ከለሜዳ አስታጥቆ ጌታን ስሎታል። አንድም ጲላጦስ ስለጌታ አቋምና ውበት ግርማ ሞገስ ለጢባርዮስ ቁሳር የላከለት መልዕክት ለስዕሉ መነሻ ሆኗል።

፪. አውሳብዮስ ዘቂሳርያ በፃፈው የቤተክርስቲያን ታሪክ ደም ሲፈሳት የነበረችው ሴት ውለታውን ለመክፈል ስትል ያሰራችው ሐውልት ለስዕሉ መነሻ ሆኗል።

፫. ቬሮኒካ የተባለች መበለት በዕለተ አርብ ጌታ መስቀል ተሸክሞ ደም ፊቱን ጋርዶት ልቧ በሐዘን ተነክቶ ሻሽዋን አውልቃ ፊቱን እንዲያብስበት ብትወረውርለት ፊቱን አብሶ የመለሰላት ሻሽ ላይ መልኩ ቀርቷል።

፬. ዮሐንስና ጴጥሮስ በባዶ መቃብር ውስጥ ገብተው ያዩት ጌታ ተገንዘቦት የነበረው ከፊን (ሰበን) መጠምጠሚያ ላይ መልኩ ታትሞበት ነበር በማለት የቤተክርስቲያን ሊቃውንት አረጋግጠዋል።

- የእመቤታችን ስዕል ደግሞ ሉቃስ እንደሳላት አስረጂ አለ። የቅዱሳንም ስዕል በታዩበት በተገለፁበት ሁኔታ ስዕላቸው ተስሏል። /ኢሳ 5፥13-15/ መሳ13፥6/ ዳን 3፥25/ ዳን 10፥1/ ሉቃ 1/ ኢሳ 6/
- በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ስዕል ብዙ ጥንቃቄ ተደርጎበት የሚሳል ነው።
- በወንጌላዊ መልዕክትነቱ አስተማሪነቱ ማንበብ ለማይችሉ አስተማሪ በቀለማቸው ውስጥ የሚታየው የወንጌል መንፈሳዊ ምስጢር ማስተላለፊያና ምዕመናን ለሚጠባበቁት አዲስ ሕይወት ተስፋ አመልካች መሆን አለበት።

ሀ. <u>አሳሳል</u> ፡- ስዕሎች ትምህርተ ሃይማኖትን የጠበቁ ሊሆኑ ይገባል፡፡ ለምሳሌ ፡- ስዕለ ሥላሴ በአንድ መንበር ተቀምጠው 3ቱን ዓለምን ይዘው ወደ አንድ አቅጫጫ እየተመለከቱ በተመጣጠነ አካላዊ ገፅታ በአምሳለ አረጋዊ መሳል አለባቸው፡፡ /ዘፍ 18/ ምሰለ ፍቁር ወልዳ ሲሳል እመቤታችን በቀኙ ሆና በግራዋ ጌታችንን ታቅፋው መሆን አለበት፡፡/መዝ 44፥9/ ዓድቃን ሲፀልዩ ወይም አጋንንት ሲታገሉ መላዕክት በሰሩት ተዓምራት፣ ሰማዕታት በፈረስ፣ መምህራን (ሊቃውንት) ካባ ለብሰው ወንጌል ይዘው መስቀል ተሰሎባቸው መሆን ይገባል፡፡ /ራዕ 19፥11-16/

ለ. <u>አቋም</u> ፡- የባለ ስዕሉን ክብር፣ ስልጣን... ሊያሳይ የሚችል መሆን ይገባዋል፡፡ የስዕሉን ባለቤት አግዝፎ ሌላውን አሳንሶ ይሳላል፡፡ ለምሳሌ ፡-ስነ ስቅለቱ ጌታችን ቀይ ግምጃ አገልድሞ አንገቱን ወደ ቀኝ አዘንብሎ አክሊለ ሶክ እንደደፋ እግሮቹ ተነባብረው ተቸንክረው በቀኙ እመቤታችን በግራው ቅዱስ ዮሐንስ ወንጌላዊ ሆነው ከእግረ መስቀሉ አፅመ አዳም እንዲታይ ተደርጎ ሲሳል ይገባል፡፡

ሐ. <u>መልክዕ</u> ፡- ቅዱሳን ስዕላት ፊታቸው ሰፊና ክብ ነው፡፡ በስዕሉ ባለቤት አናት አክሊለ ብርሀን ይደረግላቸዋል፡፡ የስዕሉ ባለቤት ዓይኑ ጎላ ተደርጎ ይሳላል፡፡ መናፍቃን ከሃድያን ሲሳሉ ግን በግማሽ ፊት በአንድ ዓይን መጠናቸው አንሶ ይሳላል፡፡ ይህም ሕፁፃነ ሃይማኖት መሆናቸውን ለመግለፅ ነው፡፡ ሰይጣን ሲሳል ደግሞ በተደበላለቀ ቀለም ዓይኑ የፈጠጠ ጥርሱ የገጠጠ ቀንድ ጅራት ያለው ሆኖ እኩይ ምግባሩን ለመግለፅ ይሳላል፡፡

መ. <u>ቀለም</u> ፡- ቀለማቱ በአብዛኛው ሰማያዊ ቀይና ነጭ ናቸው ቢጫም መጠቀም ይቻላል፡፡

- ***ሰማያዊ*** ፡-ሰማያዊ ሕይወት ገንዘብ በማድረግ በፈቃደ ነፍስ መመራትን ያመለክታል፡፡
- ***ቀይ*** ፡- የሰማዕትነት፣ የነፃ አውጭነት መስዋዕትነት ደስታ መለኮትን ያመለክታል፡፡
- ***ነጭ*** ፡- ድል አድራጊነትም ንፅህን ፍፅምነትን ያመለክታል፡፡
- ***ቢጫ*** ፡- አክሊለ ብርሃንን ለመሳል ይጠቅማል፡፡

<u>**ለምሳሌ**</u>፡- በጌታ ስነ-ስነስቅለቱ ያገለደመው ቀይ መሆኑ እኛን ከነበረብን ፍዳ ለማውጣት የከፈለልንን ቤዛነት ያመለክታል፡፡

<u>የስዕል አሳሳል በቤተመቅደስ</u>

- በቤተክርስቲያን በመቅደሱ፣ በቅድስቱ፣ በቅኔ ማኅሌት፣ በበር፣ በመስኮት፣ በምኅዋር፣ በደፉ በሁሉ ይሳላል፡፡ ይኸውም፡-
  - **በምስራቅ** ፡- መድኃኒታችን የፈፀመውን ገቢረ ተአምራቱና ገቢረ ሐዋርያት እንዲሁም እመቤታችን ቅዱስ ኤፍሬምን ስትባርከው ይሳላል፡፡ ከምህዋሩ (ከደፉ) በላይ እርገተ እግዚዕነ ይባላል፡፡
  - **በምዕራብ** ፡- ስቅለቱ፣ ልደቱ፣ ጥምቀቱ ሕማማተ መስቀሉ ትንሳኤው፣ ምስለ ፍቁር ወልዳ እና ቅዱስ ጊዮርጊስ ይሳላሉ፡፡ ከምህዋሩ በላይ የቅድስት ሥላሴ ስዕል ይሳላል፡፡ በመቅደስ በር ደግሞ ቅዱስ ሚካኤል ፈርኦንን እንዳሰጠመውና ቅዱስ ሩፋኤል ዓሳ አንባሪውን እንደወጋ የሚያሳይ ስዕል ይሳላል፡፡
  - **በሰሜን** ፡- ሰማዕታትና እመቤታችን እሞሙ ለሰማእታት ይሳላሉ ከምህዋሩ በላይ በደብረ ታቦር ብርሃነ መለኮቱን የገለጠበት ይሳላሉ፡፡
  - **በደቡብ** ፡- እመቤታችን ከልደቷ እስከ እርገቷ ያለው ታሪክ የሚያሳይ ነገረ ምጽአቱን የሚያሳይ እና ከምህዋሩ በላይ ተአምረ ማርያምን የሚያሳይ ስዕል ይሳላል፡፡
- በአጠቃላይ ስዕል በቤተክርስቲያን አምልኮ ስርዓት ማቅረቢያን አማኒያን በስዕሉ ፊት ቆመን በመፀለይ በመስገድ ለስዕሉ ባለቤት ያለንን ፍቅር አክብሮት በመግለፅ ከባለ ስእሉ ረድኤትና በረከት ማግኘ ነው፡፡ ለስዕሉ ባለቤት ክብርና ፍቅርን በመግለፅ በእምነት የሚፈፀም የሚያድን ስርዓት ነው፡፡



ስለዚህም ለስዕል የሚገባ ክብር በቤተክርስቲያንም በቤትም በየትኛውም ቦታ ክርስቲያኖች ልንሰጥ ይገባናል።

ለቤተክርስቲያን ለንዋየ ቅድሳት እና ለስዕላት ማድረግ ያለብን

እንክብካቤ (ጥንቃቄ) እና ክብር

ሀ. ቅዱስ መሆናቸው ከሌሎች ነገሮች ተለይተው ለእግዚአብሔር አገልግሎት የተመረጡ በመሆናቸው ስለሆነ የእግዚአብሔር የሆነውን ማክበር ተገቢ ነው። /መዝ 64፥5/ 2ኛነገ 7፥6/ ዘፀ 15፥33/

ለ. የቤተክርስቲያን ዙሪያ ገባውን ቆሻሻ እንዳይገባበት መጠበቅ እንዲሁም ቆሻሻም ከገባ ማፅዳት ተገቢ ነው።

ሐ. ከንዋየ ቅዱሳት በምዕመናን ደረጃ መንካት የማይገባን ክህነት ያላቸውም መንካት ያለባቸውን ብቻ በመጠቀም ማገልገል ተገቢ ነው።

መ. ለቅዱሳን መገልገያ ዕቃዎች የተለየ ዕቃዎች የተለየ ቦታ (ዕቃ ቤት) በማዘጋጀት መጠበቅ

ሠ. ቅዱሳን ስዕላትን በቤታችን ስንጠቀም በተማርነው መሰረት የቤተክርስቲያናችንን ሃይማኖታዊ ትምህርት፣ ስርዓትና ትውፊት በተከተለ መልኩ የተሰራ (የተዘጋጀ) ሲሆን እና በአንድ ቦታ (በመፀለያ ቦታችን) ተሰብስበው በመጋረጃ ተሸፍነው ሊቀመጡ ይገባል።

ረ. ቅዱሳን ንዋያተ ለአገልግሎት ከመዋላቸው በፊት ስልጣነ ክህነት ባላቸው አባቶች በፀሎትና በሜሮን መክበር አለባቸው።

ሰ. በቅዱስ ሜሮን እና በፀሎት የከበረውን ቅዱስ ዕቃዎች ወደ ዓለም ወስዶ መገልገል አይፈቀድም። /ፍት 1፥8/

ሸ. ከምዕመናን ወገን ለአንድ እንኳን ካህን ካልሆነ በቀር ወደ መሰዊያው (መቅደስ) ሊገባና ቁርባን ሊቀበል አይገባውም።

ቀ. በስርዓተ-ቤተክርስቲያን ትምህርት መሰረት በቤተክርሰቲያን ውስጥ መቀመጥ (ማስቀደስ) በተፈቀደልን ቦታ መገኘት ይኖርብናል።

በ. ካህናትም ይሁኑ ምዕመናን ለአገልግሎት ከመጠቀማችን በፊት የማይገባን መሆኑን እየተረዳን ራስን ዝቅ በማድረግ በፀሎት እየጠየቅን በንዋየ ቅዱሳት ልንገለገል ያስፈልጋል።

ተ. ለቤተክርስቲን የፀጋ ስግደት መስገድ ተገቢ ነው። ሌሎች በንዑሰ ክርስቲያን ያሉት ሰዎች መረዳት ያልቻሉትን ማስረዳት ቤተክርስቲያን በፀጥታ እንዲፀለይባት ሁላችን በፀጥታ መቆየት አለብን።

ቸ. በአሁን ሰዓት (ጊዜ) በስርዓት ደረጃ ያሉት የቤተክርስቲያን ትምህርቶች በማጥፋት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክስቲያን ውበት (ቀለም) ማዳከም ተያይዘዋል። ምን ችግር አለው በሚል ፈሊጥ የቤተክርስቲያን ስርዓት ለማጥፋት ይንቀሳቀሳሉ ስለዚህም እኛ የቤተክርስቲያን ልጆች በጥብቅ ይህ ነገር ልናስተምር ልንጠብቀው ያስፈልጋል።

ኀ. በቤተክርስቲያን ምስጢራት ውስጥ አለማድረግ፣ አለመንካት ያለብንን ነገር ለምን እያሉ በአጉል ጥያቄ ራስ ከመሙላት ወደዚያ ምስጢር የሚያቀርበን ትምህርትና ስልጣን ለማግኘት በትህትና መትጋት ያስፈልገናል።

ነ. ስዕላት አገልግሎት መስጠት ሳይችሉ ለምሳሌ በማርጀት፣ በመቀደድ፣ በአግባቡ በመሰብሰብ እንደ እምነት ልንጠቀምበትና ፈውሰ ስጋ ልናገኝበት ያስፈልጋል፡፡

- በአጠቃላይ ሰዎች በአፀደ ስጋ እያሉ ሰማያዊ ስርዐት የሚሳተፉበት እንዲሁም ከዚህ ዓለም በሞት ሲለዩም የሚያርፉበት ስፍራ እንደመሆኑ መጠን ታላላቅ ስርዓት የሚከናወነው በእነዚህ ከላይ (በርዕሱ በጠቀስናቸው) ነው፡፡ ስለዚህም ይህ የቤተክርስቲያናችን ታላቅ ሀብት እድዳይጓደል መጠበቅ ያስፈልጋል፡፡ ይህ ደግሞ የተሰጠው ለካህናት ብቻ አይደለም፡፡ ምንም የእነሱ ስልጣን የበዛ ቢሆን እያንዳንዱ ምዕመን የቤተክርስቲያን ስርዓት እንዲጠበቅና ለትውልድ ትውልድ እንዲተላለፍ የማድረግ ሃይማኖታዊ ግዴታ አለበት፡፡ በመሆኑም እኛ የተማርናቸውን በተግባር በመፈፀም መክሊታችንን ልናተርፍ ይገባል፡፡ በአሁኑ ጊዜ ከቤተክርስቲያናችን ወጭ ያሉት ሐሳውያን መምህራን ከእኛ ለማፍለስ እየተጉ ያሉት በዚሁ ስርዓት ላይ በመሆኑ የተማርነውን በማስፋፋት ምዕመናን ከሐሰት ጎዳናም መጠበቅ ሃይማኖታዊ ኃላፊነት በመሆኑ ሁላችንም የተማርነውን ከማስተማር መቦዘን የለብንም፡፡



ምዕራፍ ሁለት (፪)

2. አንቀፅ ሁለት - ቅዳሴ

ቅዳሴ ቀደሰ አመሰገነ ከሚል የግዕዝ ቃል የመጣ ሲሆን ትርጉሙም **ምስጋና** ማለት ነው። ልዑል እግዚአብሔር ባሕርዩ ምስጋና ነውና እኛም የተፈጠርነው ለምስጋና ነውና።

2.1 የቅዳሴ አገልግሎት

የቅዳሴ አገልግሎት ሦስት ዐበይት ክፍሎች አሉት፡-

2.1.1 አንደኛ ዐቢይ ክፍል የዝግጅት ክፍል

2.1.2 ሁለተኛ ዐቢይ ክፍል ስርዐተ ቅዳሴ

2.1.3 ሦስተኛ ዐቢይ ክፍል ፍሬ ቅዳሴ

2.1.1 አንደኛ ዐቢይ ክፍል /የዝግጅት ክፍል/

✞ **የዝግጅት ክፍል** ፡- በዚህ ክፍል ልዑካኑ (ቀዳሲያኑ) ራሳቸውን ለአገልግሎት የሚያስፈልጉትን ንዋያተ ቅዱሳት ያዘጋጃሉ በተለይ ሰራዒው ቂስ ልዑካኑ ተሟልተው መቅረባቸውን የማረጋገጥ፣ ንዋያተ ቅዱሳቱ 6ቱ መዝሙራትን ጨምሮ ለየራሳቸው የተዘጋጀውን ፀሎት በማድረስ ለአገልግሎት የማብቃት ኃላፊነት አለበት።

✞ **የልዑካን መጠንና የአገልግሎት ድርሻ**

በቅዳሴ ጊዜ የሚሰየሙ የልዑካን (ቀዳስያኑ) ቁጥር 5 ወይም 7 ወይም 12 ወይም 24 ነው። አብዘኛው ጊዜ የተለመደውና ለአገልግሎት አመቺ የሚሆነው የልዑካን ቁጥር 5 ነው። እነርሱም ፡-

፩. **ሠራዒው ቂስ** ፡- ቅዳሴውን በዋነኛነት ይመራል ፣ይፀልያል፣ ይባርካል ስጋውን ደሙን ይፈትታል ያቆርባል።

፪. **ንፍቅ ቂስ** ፡- ዕጣን በመውገር፣ ማኅፈድ በመግለጽ ቂሱን ይረዳል።

፫. **ሠራዒ ዲያቆን** ፡- ተንስኡ ፀልዩ ስግዱ እያለ ሕዝቡን ለፀሎት ያተጋል ቅዱስ ደሙን ይፈትታል ያቀብላል።

፬. **ንፍቅ ዲያቆን** ፡- መብራት ይይዛል ንባብ ያነባል።

፭. **አብሪ ዲያቆን** ፡- መብራት ጥላ ይይዛል መፅሐፍ ይገልፃል ፍሕም ያቀርባል።

ከነዚህ በተጨማሪ በመቅደስ ሆኖ የሚመርቅ የሚባርክ ኤጲስቆጶስ አንባቢ ደውል የሚደውል ሕዝን የሚያስተናብሩ ከመቅደስ ውጭ የየራሳቸውን አገልግሎት ይሰጣሉ ቁጥራቸው ግን ከልዑካኑ ቁጥር ጋር ተደምሮ ትርጉሙን አያሳልስም። በአጠቃላይ በዚህ ክፍል ላይ ወደ ቅዳሴ ከመግባታቸው በፊት ያሉ ዝግጅቶች ይከናወንበታል።

2.1.2 ሁለተኛ ዐቢይ ክፍል /ስርዐተ ቅዳሴ/

✞ በሌላው ስያሜ የንዑሰ ክርስቲያን ቅዳሴ ተብሎ ይጠራል ከአረማዊነት ከመናፍቅነት ተመልሰው ለጥምቀት፣ ለቁርባን ያልደረሱ አዳዲስ የሚሳተፉት ስለሆነ ነው። ይህም ከፀሎተ ንስሐ ዓው እስኪል ድረስ ያለውን የያዘ ነው።

2.1.3 ሦስተኛ ዐቢይ ክፍል ፍሬ ቅዳሴ

✞ ይህ ክፍል ዓው ካለ በኋላ እትው በሰላም እስኪል ድረስ ያውን ሁሉ የሚያካትት ዐሚይ ክፍል ነው።



<u>የመወያያና የቤት ስራ ጥያቄ</u>

፩. የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ስንት ቅዳሴዎች አሉዋት? ስማቸውን ዘርዝር?

፪. ማን ዓፋቸው? በምን በምን ወቅት ይቀደሳሉ?

2.2 <u>በቅደሴ አገልግሎት የሚገኙ ስርዓቶች የአገልግሎት ዓይነቶች</u>

❖ በቅዳሴ አገልግሎት በሁለቱ ዐቢይ ክፍሎች (በስርዐተ ቅዳሴና በፍሬ ቅዳሴ) ላይ የሚገኙት አገልግሎቶችና ስርአቶች በ16 ከፍለን እናያቸዋለን፡፡

፩. **ምስጋና** ፡- የፀሎተ ቅዳሴ ንባብ በሙሉ ምስጋናና ጸሎት የያዘ ነው በተለይ በቁርባን የምስጋና ክፍሎች ብዙዎች ናቸው፡፡

፪. **ፀሎት**

- ✓ **ፀሎተ ንስሐ** ፡- የስርዐተ ቅዳሴ የመጀመሪያ ፀሎት ነው፡፡ *“መቅድም ኩሉ ይደሉ ቀሲስ ፀሎተ ንስሐ”* እንዲል ስርዓተ ቅዳሴ ቂሱ ከመቅደሱ ደጃፍ ቆሞ ፊቱን ወደ ሕዝቡ መልሶ ይፀልያል፡፡ ሕዝቡም ወድቀው ይሰሙታል፡፡ ይህ ፀሎት ከእግዚኦታ በፊት በድጋሚ ይፀለያል፡፡
- ✓ **ፀሎተ አኮቴት** ፡-ተናጋሪው ቅዱስ ባስልዮስ ነው ይህም ነአኩቶ ለገባሬ ሠናይት ላዕሌነ ያለው ነው፡፡ ዲያቆን ፀልዩ ጎሡ ወአስታበቁዑ ይላል ሕዝቡ ኪርያላይሶን ይላሉ፡፡
- ✓ **ፀሎተ መባዕ**፡- ተናጋሪዎቹ ሐዋርያት ናቸው የሚፀልየው ንፍቁ ቂስ ሲሆን ፀሎተ መባዕ ስለሚያቀርቡ ሰዎች የሚለመን ነው ቂሱን ተከትሎ ንፍቁ ዲያቆን ፀልዩ በእንተ እለ ያበውዑ መባዕ ሲል ሕዝቡ ተወከፍ መባዖሙ ይላሉ፡፡
- ✓ **ፀሎተ እንፎራ** ፡-ተለውጦ ስጋና ደሙ እንዲሆን በጎብስቱና በጽዋው ላይ የሚፀለይ ፀሎት ነው፡፡ የሚፀልየው ሠራዒው ቂስ ነው ይህን ፀልዮ ጎብስቱና ጽዋው በማጎፈድ ይሸፍናቸዋል፡፡
- ✓ **ፍትሐት ዘወልድ** ፡- ዲያቆኑ ስገድ ካለ በኋላ ፊቱን ወደ ሕዝቡ መልሶ ንፍቁ ቂስ ይፀልየዋል ጸሎቱም ጌታ ለሐዋርያት ስልጣነ ክህነት እንደሰጣቸው በማዘከር ሕዝቡ ከጎጢአት ቁርኝነት ነፃ ያደርጋቸው ዘንድ ይለምናል፡፡ መታሰቢያ ለተደረገላቸው ነፍሳተ ሙታንም ዕረፍተ ነፍስን ይጠየቃል፡፡
- ✓ **በእንተ ቅዱሳት** ፡-ከፍትሐት ዘወልድ አያይዞ ዲያቆኑ ያደርሰዋል፡፡ ይህ የፀሎት ክፍል በጥቅሉ 31 ልመናዎች ይዟል፡፡ ሕዝቡ በየማረፊያው አሜን ኪርያላይሶን እግዚኦ ተሠሃለነ ይላሉ፡፡
- ✓ **ፀሎተ ዕጣን** ፡- በዕጣኑ ላይ የሚፀለይ ፀሎት ነው፡፡
- ✓ **ፀሎተ ወንጌል** ፡- ዲያቆኑ ፀልዩ በእንተ ወንጌል ከማለቱ በፊት ሠራዒው ቂስ እግዚአብሔር እግዚኦ ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክነ ብሎ ወንጌልን ሰምቶ ስለመስራት የሚፀልየው ነው፡፡
- ✓ **ፀሎተ ሃይማኖት** ፡- ዲያቆኑ ንበል ኩልነ ባለ ጊዜ በዲያቆኑ መሪነት ይባላል፡፡
- ✓ **ፀሎተ አምኃ** ፡- ተናጋሪው ቅዱስ ባስልዮስ ነው፡፡ ይህም እግዚአብሔር ዐቢይ ዘላለም ያለው ነው፡፡
- ✓ **አኮቴተ ቁርባን** ፡- የቁርባን ፀሎት መጀመሪያ ነው ከ14 ቅዳሴያት ለዕለቱ የተመረጠውን (የታዘዘውን) ያስገባል፡፡
- ✓ **ፀሎተ ቡራኬ** ፡-ዲያቆኑ በእንተ ብፁዕ ካለ በኋላ ንፍቁ ቂስ በመቅደሱ ደጃፍ ቆሞ ፊቱን ወደ ሕዝቡ መልሶ አ ሥሉስ ቅዱስ ብሎ የሚፀልየው ፀሎት የፀሎት ክፍል ነው፡፡
- ✓ **ፀሎተ ፈትቶ** ፡- ስጋው በሚፈተትበት ጊዜ የሚፀለየው ፀሎት ነው፡፡
- ✓ **እግዚኦታ** ፡- እግዚኦ መሐረነ ክርስቶስ አቤቱ ክርስቶስ ሆይ ማረን ይቅር በለን የሚል ልመና ነው በዐቢይ ዜማ 3 ጊዜ በንዑስ ዜማ ጊዜ ቀጥሎ ቂሱ 3 ሕዝቡ 2 ይላሉ የቂሱ 21 የሕዝቡ 20 በጠቅላላ 41 አዳም በእግረ ገነት ወድቆ በንዘን ባሳለፋቸው 41 ዕለታት ምሳሌ ነው፡፡
- ✓ **የቁርባን ፀሎት** ፡- ስጋውና ደሙን በመቀበል ጊዜ የሚፀለይ ፀሎት ነው፡፡ “ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ ሥሉስ ዘኢይትነገር ሀበኒ ከመ እንሣእ ለሕይወት ዘንተ ስጋ ወደመ ዘንበለ ኩናኔ ...” እያለ ያቀብሉታል ይቀበሉታል፡፡

- ✓ **ጎዳፌ ነፍስ** ፡- ድርገት ሲመለስ ዲያቆኑ ነአኩቶ ለእግዚአብሔር ካለ በኋላ አያይዞ ቁሱ የሚፀልየው ፀሎት ነው፡፡ የጸሎተ ቁርባኑም የመጨረሻ ክፍል ነው፡፡

- በአጠቃላይ ስንመለከተው በስርዐተ ቅዳሴ ሰዓት ከ17 የሚደርሱ የፀሎት ዓይነቶች እና ርዕስ ያልተሠጣቸው ብዙ እንዳሉ ያስረዳናል፡፡

፫. **ምዕዳን ምክር** ፡-ሰብሕሥ ለእግዚአብሔር ኩልክሙ አሕዛብ፣ አእኮትሥ ለአምላክነ፣ አልዕሉ አልባቢክሙ እንዳለው ያለ ነው፡፡

፬. **ትእዛዝ**

- **ፃዑ ንዑሰ ክርስቲያን** ፡- አዳዲስ አማኞች ከሕዝቡ መካከል ወጥተው ስርዓቱን እንዲከታተሉ ለማሳሰብ
- **ተንስኡ ለፀሎት** ፡-በቅዳሴ ውስጥ 15 ያህል ጊዜ ሕዝቡን በፀሎት ለማትጋት ይተላለፋል ሠራዒው ዲያቆን 12 ጊዜ ይናገሩታል 3ቱ የሥላሴ 12ቱ የሐዋርያት ምሳሌ ነው፡፡
- **እለትነብሩ ተንስኡ** ፡- ፀሎተ ቡራኬ ከተደገመ በኋላ ዲያቆኑ ቁሱን ተከትሎ የሚናገረው ቃል ነው፡፡ በቅዳሴ በደሜ ካለ በቀር መቀመጥ የተከለከለ ነው ስለዚህም የተቀመጣችሁ ተነሱ አለ፡፡
- **ውስተ ጸባሕ ነጽሩ** ፡- ወደ ምስራቅ ተመልከቱ መልዕክቱ ምስራቃዊ ሕገ ወንጌል አንድም የእመቤታችንን አማላጅነት አንድም የጌታን መምጣት እንድናስብ የሚያሳስብ መልዕክት ነው፡፡
- **ንነጽር** ፡- እናስተውል የሚነገረውን በጥንቃቄ ስለመስማት
- **አውሥኡ** ፡- ተሰጥሥ መልሱ ሕዝቡ ካህናቱን እየተከተሉ ፀሎቱን መሳተፍ እንዳለባቸው ለማዘከር ነው፡፡
- **አንሥኡ እደዊክሙ ቀሳውስት** ፡-ቀሳውስት እጃችሁን አንሱ፡፡

፭. **ስግደት** ፡- የአምልኮት መገለጫ ነው ዲያቆኑ የሚያውጀውን ስግዱ የሚል ትዕዛዝ ሰምቶ ከመሬት ወድቆ ፀሎቱ መስማት ይገባል፡፡

፮. **መዝሙር** ፡- ይህ በዕለቱ ያለው የመዝሙር ዝማሬ ምስባኩን ይመለከታል፡፡

፯. **ትምህርተ ወንጌል** ፡- የተዘመረውን መዝሙርና የተነበበው የወንጌል ክፍል ማብራራት የንባቡ ምስጢር ገልጦ ለምዕመናን ማስተማር ይገባል፡፡

፰. **ቡራኬ** ፡- በቅዳሴ ጊዜ የሚፈፀመው ቡራኬ ቁጥር 42 ነው ይህም የሚባረከውን የመለወጥ የመቀደስ የማክበር ኃይል ያለው ስርዓት ነው፡፡

፱. **ንባብ** ፡- በቅዳሴ ጊዜ የሚነበቡት መፅሐፍ ይመለከታል፡፡ ሠራዒ ዲያቆን የጳውሎስ መልዕክትን፣ ንፍቁ ዲያቆን ከ7ቱ ሐዋርያት መልዕክታት፣ ንፍቁ ቂስ ግብረ ሐዋርያት በየ3ቱ ማዕዘናት እየዞሩ ያነባሉ፡፡ አራኛተኛውን ወንጌል ሠራዒው ቂስ ፊቱን ወደ ምስራቅ መልሶ ያነበዋል፡፡ ወንጌል ከተነበበ በኋላ ሕዝቡ ልዑካኑም **ነአምን በቃለ ወንጌል ቅዱስ** እያሉ ይሳለሙታል፡፡

፲. **ማዕጠንት** ፡- በዝግጅት ወቅት ያማረው ዕጣን መርጦ ያሰናዳውን በፀሎተ ዕጣን ጊዜ ቡራኬውን ፈፅሞ (በማዕረግ በሚበልጠው) አስባርኮ 5ቱን አንኳር ዕጣን አግብቶ ወንጌል ሲባል ተዘክረነ ሲባል ያጥነዋል፡፡

፲፩. **ዑደት** ፡- በቅዳሴ ጊዜ የሚፈጸመው የዑደት መጠን 10 ሲሆን አራት ክፍል አለው፡፡

፲፪. **ተዘክር ሞተ ወልድ** ፡- ጌታ የቁርባን ስርዓት ሲሠራ ይህን ለመታሰቢያ አድርጉት 1ኛ ቆሮ11፥24 እንደ መስዋዕቱን ስንሰዋ *"ንዜኑ ሞተክ እግዚኦ ወትንሳአክ ቅድስት ነአምን ዕርገተ ወዳግም ምጽአትክ ..."* ብለን ሞት ትንሳኤው ዕርገቱን ዳግም ምፅአቱን እናስባለን፡፡

- **ሕጽበተ እጅ፡-** ከፀሎተ ሃይማኖት በኋላ ቄሱ በመቅደሱ ደጃፍ ሆኖ እጁን " ንጽህ አነ እምደመ ኩልክሙ" እያለ ታጥቦ ማዩ በእጁ ይነዘዋል፡፡ የጲላጦስ ቃል ነው በዕለተ አርብ የተናገረው እኔ ከደሙ ንፁህ ነኝ የሚለውን፡፡

፲፫. **ድርገት** ፡- ድርገት ማለት **አንድነት** ማለት ነው፡፡ ስጋውና ደሙ አንድ ሆኖ መስጠቱን የሚያስረዳ ስያሜ ነው፡፡ ድርገት ሲወርድ ወድቆ እጅ መንሳት ይገባል የትንሳኤ ዕለት ሴቶች ጌታ ሲገለፅላቸው ከእግሩ ስር ወድቀው እጅ ነስተውታልና የዚህ ምሳሌ ነው፡፡ /ማቴ 28፥9/ ሲመለስም እንዲሁ ወድቆ እጅ መንሳት ይገባል ጌታ ሲያርግ ሐዋርያት እጅ ነስተው ተመልሰዋልና /ሉቃ 24፥52/ የዚያ ምሳሌ ነው፡፡

፲፬. **ምርቃት** ፡- ሰላም ለኩልክሙ ሰላም ለሁላችሁ ይሁን ቄሱ 12 ያህል ጊዜ ንፍቁ ቄስ 3 ጊዜ ይናገሩታል፡፡ ቃሉ የጌታ ነው፡፡ አዳም በሲኦል ሆኖ በዕለተ ዓርብ በአካለ ነፍስ ወርዶ ሰላም ለሁላችሁ ይሁን ብሏቸዋል፡፡ ቄሱ ይህን ሲናገር ሕዝቡም እንደቃልህ ይሁንልን ብለው ይቀበሉታል፡፡

፲፭. **አንብሮተ ዕድ** ፡- ድርገት ከተመለከ በኋላ ቄሱ እጁን ከታቦቱ ላይ አመሳቅሎ የሚፀልየው ፀሎት ነው፡፡ ይህም ጌታ ሲያርግ በሐዋርያት እጅን አኑሮ ባርኳቸው የማረጉ ምሳሌ ነው፡፡ /ሉቃ 24፥50/

፲፮. **ሥርዎት** ፡- ከአንብሮተ እድ በኋላ እጅ አኑሮ ያለው ፀሎት የስንብት ፀሎት ነው፡፡ የስርዓቱ መፈፀም የሚታወጅበት ነው፡፡ /ዘኁ 20፥23/

2.3 <u>ለመቀደስ-ማስቀደስ የሚደረግ ዝግጅት</u>

፩. ቂም በቀልን አስወግዶ በንፁህ ሕሊና መቅረብ ያስፈልጋል አገልግሎቱ አማናዊ ነውና፡፡ /ማቴ5፥23/

፪. ስርዓት ሳይፈፀም መውጣት ስለማይገባ ስጋዊ ተግባርን አከናውኖ ከስጋዊ ሐሳብ ነፃ ሆኖና ፀሎቱን በንቃት ለመከታተል ወስኖ (ተዘጋጅቶ) መቅረብ ያስፈልጋል፡፡

፫. ቦታው ቅዱስ መስዋዕቱ ቅዱስ ነውና እድፍ ስጋዊ በውሃ ነፍሳዊ እድፍን በንስሐ አስወግዶ በፍፁም ንፅህና መቅረብ ይገባል፡፡

፬. በተገረገገ ልብስ ጌጥ ማንጠልጠልና ቅባት መቀባት ፍፁም ተገቢ እይደለም የመዓዛችንም ማማር በፀሎት በትሩፋት እንጂ በሽቶ ሊሆን አይገባም፡፡

፭. ቤተክርስቲያን ማዕድ የሚቀርብባት ናትና ማንኛውንም የእህል ዓይነት ወደ ውስጥ ይዞ መግባት የተከለከለ ነው፡፡

፮. ስርዓቱን በንቃት ለመከታተል በሚያመች በተፈቀደ ቦታ መቆም

፯. ድምፅ ያላቸውን መሳሪያዎች (ተንቀሳቃሽ ስልክ) አስቀምጦ ወይም ዘግቶ መግባት ያስፈልጋል፡፡

2.4 <u>በስርዓተ ቅዳሴ ጊዜ የሚደረግ ጥንቃቄ</u>

፩. ዓለማዊ ሀሳብ እንዳያስብ ሕሊናን መሰብሰብ ይገባል፡፡

፪. በፍቅር በትህትና ሆኖ ማስቀደስ ይገባል፡፡

፫. የሚነገረው ቀል በጥንቃቄ መከታተል ተሰጥኦ መመለስ ይገባል፡፡

፬. ቀጥ ብሎ ፊትን ወደ ምስራቅ (መቅደሱ) መልሶ መቆም ተገቢ ነው፡፡

፭. ቢቻል እጅን አልያም ጎሊናን ዘርግቶ ማስቀደስ ይገባል፡፡

፮. በተመጠነ ድምፅ በመጠባበቅ እንጂ ከልክ ባለፈ ድምፅ መጮህ ተገቢ አይደለም

" ኢትክላህ በሕቁ አላ ዘመር " እንዲል ማር ይስሐቅ

፯. ስርዓቱ እስኪያልቅ ድረስ የግል ፀሎት ማድረግ ተገቢ አይደለም

፰. በቤቱ የቆምነው እንደቸርነቱ መጠን መሆኑን አምነን ቸርነቱ በማድነቅ በማመስገን መቆም ይኖርብናል

፱. ጎብስቱና ወይኑ በፀሎት ተለውጦ አማናዊ የጌታ ስጋና ደም እንደሚሆን ማመን ይገባል

- እነዚህን ተግባሮች ማድረግ ያስፈለገው ስለአገልግሎቱ ታላቅነት ስለሚያሰጠውም ፀጋ ክቡርነት ነው። ቅዳሴ ማለት በመላዕክት ታጅቦ ማመስገን ማለት ነውና እንደ መላዕክት ስርዓት ራስን ዘንበል አድርጎ በትህትና መቀደስ-ማስቀደስ ተገቢ ነው። /ፍትሐ ነገስት 14./ ምንም ለአገልግሎት ዲያቆኑ ስገዱ ቢልም እሱም በልቦናው ጉልበት መስገድ ይገባዋል።

2.5 ቅዳሴ በመቀደስ እና በማስቀደስ የሚገኝ በረከት

- ቅዱስ አባ ሕርያቆስ እንደተረጎመው በቅዳሴ ማርያም " ዘንተ ቅዳሴ ዘይቄደስ ካህን አኮ ለማርያምሃ ዘይቄደስ አላ ላሊሁ ይተቄደስ ውኩሎሙ እለ ይስምዕዎ ይተቄደሱ። " ይህን ቅዳሴ የሚቀደስ ካህን እመቤታችንን የሚቀድስ አይደለም እርሱ ራሱን ይቅደሳል የሰሙት ሁሉ ይቀደሳሉ እንጂ እንዳለ በትልቁ የፀሎት ስርዓት ስንሳተፍ እንቀደሳለን፣ እንባረካለን።
- ስርዓቱ ሰማያዊ እንደሆነ ቅዱስ ያሬድ በድርሰቱ ይነግረናል። ራሱ የስርዓተ ቅዳሴ ዜማ የተቀዳው ከመላዕክት የሰማያዊ ስርዓት ስለሆነ በቅዳሴ በምንገኝበት ወቅት ከመላዕክት ሕብረት ከሰማያዊው የአምልኮ ስርዓት ተካፋይ እንሆናለን።
- ስርዓተ ቅዳሴ ዘለዓለማዊ ሕይወት የምናገኝበት ስርዓት ነው። ምክንያቱም የክርስቶስ ኢየሱስ ቅዱስ ስጋውና ክቡር ደሙ የሚሰዋበት (የሚፈተትበት) የቤተክርስቲያን ታላቁና የመጨረሻው የፀሎት ስርዓት በመሆኑ እና ማንም በቅዳሴ ስርዓት የተገኘ የተለየ ምክንያት ከሌለበት ይህ ትልቅ ምስጢር መፈፀም ስላለበት ዘላለማዊ ሕይወት ይጎናፀፍበታል። /ዮሐ 6፥53/
- በውስጣችን ያለውን ሃይማኖት ያጠናክርልናል። በትምህርት የምናውቃቸው ምስጢራት በተግባር የሚከናወኑበት ስርዓት ስለሆነ።
- ስርየተ ኃጢያት እናገኝበታለን /1ኛ ዮሐ 1፥7/ ስርዓቱ የሚከናወነው ስልጣነ ክህነት ባላቸው አባቶች በመሆኑ (የመፍታትና የማሰር ስልጣን ባላቸው) የመፍታቱ (በካህን ኃጢአታችን ማስተሰረይ) እንችላለን።

<u>የመወያያ ጥያቄዎች</u>

1. በቤተመቅደስ ገብተው አስቀድሰው ያውቃሉ? ስርዓቱ ስትታደሙ ምን ተሰምቶት ያውቃል?
2. በሳምንት አልያም በዓመት ምን ያህል ጊዜ ያስቀድሳሉ? ደካማ ከሆኑ ለምን?



ምዕራፍ ሦስት (፫)

አንቀፅ 14- ፀሎት

ጸሎት ማለት ከእግዚአብሔር ጋር መነጋገር ማለት ነው። "ፀሎትሰ ተናግሮ ምስለ እግዚአብሔር" እንዲል።

3.1 የፀሎት ስርዓት

- የፀሎት ስርዓት በብዙ ወገን ይከፈላል።
  - ሀ. የግል ፀሎት /ማቴ 6፥5-13 /ፍት.ነገ 14/
  - ለ. የቤተሰብእ ፀሎት /ዮሐ 10፥1-2 /ፍት.ነገ 14/
  - ሐ. የማኅበር ፀሎት /የሐዋ 1፥14 /ፍት. ነገ 14/

3.2 የፀሎት ስርዓት አፈፃፀም

- በፀሎት ጊዜ ለፀሎት የቆመ ማንኛውም አካል የሚከተሉት ክንዋኔዎች መተግበር ይገባዋል።
- ዓምድ ግድግዳ ሳይዙ በሀብተ እግር ቀጥ ብሎ መቆም ይገባል። /መዝ5፥3/
- ወገብን በዝናር መታጠቅ-የአገልግሎትና የብርታት ምልክት ነው። /ሉቃ12፥35/
- ፊትን ወደ ምስራቅ መመለስ ይገባል፡-ኢየሱስ ክርስቶስ በዳግም መምጣቱን ተስፋ እያደረግን መፀለይ ለማመልከት
- በመስቀል አምሳል ማማተብ አጋንንትን ድል በማድረግ /ሉቃ11፥20/ አንድም ክርስቶስ በመስቀል የከፈለልንን ዋጋ በማሰብ
- በመፍራትና በመንቀጥቀጥ የጸሎት ቃላት ማንበብ ይገባል።
- የሚፀልይ ሰው በጎኩዕ ልብ በፀሎት ከእግዚአብሔር ጋር ይነጋገራል ሀሳቡን በእግዚአብሔር ላይ ይጣል።
- አስተባርኮና ስግደት በሚገባ ሰዓት ቦታ ስግደት ሊያደርግ ይገባዋል። /ማቴ 4፥10/ ዮሐ 4፥24/ የሚሰገድባቸው ጊዜያቶችና ቁጥሮች በቤተክርስቲያን ተደንግገዋል። በፀሎት ላይ ስግደት የሚያነሳ አንቀፅ ሲደርስ መስገድ ይገባል።
- እጆች ማንሳት በፀሎት ስርዓት ይገባል። /1ኛ ጢሞ2፥8/ ዮሐ 11፥41/
- ማንጋጠጥ፡-እግዚአብሔርን መለመን (መማፀንን) ያመለክታል። ተስፋ መጠበቅን ምልክት ይሆናል።
- በዜማ መፀለይ፡- በዜማ መጸለያችን ለእግዚአብሔር መደሰታችንን ምሳሌ ነው።
- ዑደት በመዞር መፀለይ የእግዚአበሔር ምሉዑ በኩዓት መሆኑን ያመለክታል።/መዝ25፥6/
- በለሆሳስ መፀለይ የእግዚአብሔር አዋቂነት ያመለክታል። /መዝ61፥8/ 1ኛሳሙ1፥13/
- አንድ ቀል በመደጋገም መፀለይ አፅንኦትን ያመለክታል።

3.3 የት እንፀልያለን ?

የፀሎት ጊዜያት በያለንበት እንድናደርግ የተፈቀደልን በየትኛውም ቦታ ሆነን እግዚአብሔርን ማምለክ እንችላለን /1ኛጢሞ 2፥8/ የሐዋ 16፥25/ሉቃ 5፥16/ሉቃ22፥29/ በተለየ ሁኔታ ግን የነግህ (የጠዋት) እና የሰርክ ቤተክርስቲያን ውስጥ ሊሆን ይገባዋል ነገር ግን የሚቻለን ከሆነ ሁሉንም በቤተክርስቲያን ብንፀለይ መልካም ነው።

3.4 መቼ እንፀልያለን ?

ዘወትር በትጋትና በመጠባበቅ መፀለይ አለብን ነገር ግን በቀኖና ቤተክርስቲያን መሰረት በቀን ውስጥ 7 የፀሎት ጊዜያቶች እንዳሉ ፍቺያቸውም መጽሐፍ ቅዱሳዊ እንደሆኑ ያስቀምጣል። "አቤቱ በየዕለቱ ሰባት ጊዜ አመሰግንሃለሁ።" አለ /መዝ 118፥164/



ሰባቱ የፀሎት ጊዜያት

1. **ፀሎተ ነግህ** - የጨለማውን ጊዜ ስላሻገረን የምናመሰግንበት ነው።
2. **ፀሎተ ሠለስቱ** - ጲላጦስ በጌታችን ላይ የፈረደበት ስለሆነና መንፈስቅዱስ ለሐዋርያት የወረደበት ሰዓት ስለሆነ ነው።
3. **ፀሎተ ስድስቱ (ቀትር)** - የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተሰቀለበት ስለሆነ ነው።
4. **ፀሎተ ተሠዓቱ (ዘጠኝ ሰዓት)** - ጌታችን ቅዱስ ስጋው ከክቡር ነፍሱ የተለየችበት ስለሆነ ነው።
5. **ፀሎተ ሠርክ**- ቀኑን በሙሉ የሰራነውን ኃጢአት ለመናዘዝ ወደ ቤተክርስቲያን የምንሄድበት ነው። /ዘፀ 29፥39/
6. **ፀሎተ ንዋም (ማታ)** - ቀኑን በሰላም አውሎ ለዚህ ሰዓት ስላበቃንና ሌሊቱን እንዲባርክልን የምንፀልይበት ነው።
7. **መንፈቀ ሌሊት (ዕብለ ሌሊት)** - /መዝ118፥62/ የእግዚአብሔር መምጫው መቼ እንደሆነ ስለማናውቅ ተዘጋጅተን መጠበቅ ስላለብን ተግተን እንፀልያለን። /ማር13፥2-26/

❖ ከእነዚህ የፀሎት ጊዜያት ውጭ ልንፀልይባቸው የሚገቡ ሁኔታዎች አሉ እነሱም፡-

- ❖ **ፀሎተ ማዕድ** ፡-ከመብላታችን በፊትና ከበላን በኋላ ስለሰጠን አመስግነን እንበላለን።
- ❖ **የመንገድ ፀሎት** ፡-ከመንገድ በፊትና በኋላ ወደ ቀና ቦታ እንዲመራንና በሰላም ስላደረሰን እንፀልያለን።
- ❖ **የመከራ (ችግር)** ፡-ችግር ሲገጥመን እንዲያወጣንና ከችግር ካወጣን ስለቸርነቱ እናመሰግነዋለን።
- ❖ **የስራ ፀሎት**፡-ስራችንን ከመጀመራችን በፊትና ከጨረስን በኋላ በፀሎት መጠየቅ ይገባል። በአጠቃለይ አንድ ተግባር ከማከናወናችን በፊት በፀሎት ፈቃደ እግዚአብሔርን መጠየቅ ይኖርብናል።

3.5 <u>ፀሎታችን ተቀባይነት እንዲኖረው ማድረግ ያለብን</u>

✞ በመንፈስ ቅዱስ እየተመራን መሆን አለበት።
- ልቦናችንን ከዓለማዊ ሀሳብ ከገታን መንፈስ ቅዱስ በውስጣችን ያድራልና።

✞ በእምነት ሊሆን ይገባል።
- ስንፀልይ የምንጠይቀውን ነገር እንደሚደረግልን በፍፁም ልባችን ልናምን ይገባል።

✞ ያለማቋረጥ እና ያለመሰልቸት
- በትጋት ሁልጊዜ ያለመሰልቸት በተስፋ በመጠበቅ መፀለይ

✞ በተጋድሎ
- እኛ ከእግዚአብሔር ጋር ስንሆን ጥንተ ጠላት በተለያዩ ፈተናዎች እና መከራዎች ይፈትነናል ስለዚህ በተጋድሎ (በመጋደል) መፀለይ

✞ ከይቅርታ ጋር
- ቢበድሉ ይቅርታ ቢበደሉ ማሩኝ ማለት ተገቢ ነው። "ቂም ይዞ ፀሎ ሳል ይዞ ስርቆት" አይገባም መባዕ ለመስጠት ፀሎት ለመፀለይ ከመሄዳችን በፊት ከሁሉ ጋር በሠላም ልንሆን ይገባል።

✞ የእግዚአብሔርን ፈቃድ መጠየቅ
- ሰዎች በስህተት የተሞላን እንደመሆናችን መጠን የምንጠይቀው ነገር ለእኛ የማይጠቅም ሊሆን ይችላል ስለዚህም የአንተ ፈቃድ ይሁን ብለን ልንፀልይ ይገባል።

<u>የመወያያ ጥያቄ</u>

1. በቀን ማድረግ ካለብን ሰባት የፀሎት ሰዓታት ስንቱን ይፀልያሉ? የማይፀልዩ ከሆነ ለምን?
2. ነገሮችን ከመጀመርዎ በፊት ይፀልያሉ? ለምሳሌ ከመብላትዎ በፊት ካልፀለዩ ለምን?



ምዕራፍ አራት (፬)

አንቀፅ ፲፫-አስራ አምስት ፆም

✓ ፆም ማለት "ፆመ" ተወ፣ ታቀበ፣ ታረመ ከሚሉ ቃለት የተገኘ ነው። ፆም ማለት በታወቀ ጊዜ የሰው ከምግብ መከልከል ነው። ነገር ግን በሌላ መልኩ አይናችን ከመጥፎ እይታ አፋችን ከክፉ ንግግር ጆሮአችን አልባሌ ወሬ ከመስማት በአጠቃላይ ሕዋሳቶቻችንን ከክፉ ምግባራት መከልከል ማለት ነው።

4.1 ፆም ለምን ?

- ፆም ለስርየት አበሳ ዋጋው ይበዛለት ዘንደ የፈተና ፆር ይቀልለትና ስጋ ለነባቢተ ነፍስ ትገዛ ዘንድ ይፆማል።

ሀ. ፆም ፈቃደ ስጋን ለፈቃደ ነፍስ ለማስገዛት

- ከሁለቱ ባሕርያት ባህርይ ነፍስ የበላይነት እንድትይዝ ለማድረግ ይፆማል።

ለ. ከእግዚአብሔር በረከት ለማግኘት

- ፆም ከእግዚአብሔር መልካም የሆነውን ለመቀበል ይጠቅማል።

ሐ. ፆም ሀዘንን ለመግለፅ

- ስለስራችን ስለወገኖቻችን (በመከራ ውስጥ ስላሉት) ምህረት ለመለመን

መ. ፆም ወደ እግዚአብሔር ለመመለስ

- ፆም የፀፀትና የልብ ንፅህና ጊዜ ነው ከገባንበት የኀጢአት መንገድ ማምለጫ (መውጫ) ነው።

ሠ. ፆም ኃይለ አጋንንትን ለማድከም ለማብረድ ለማስወገድ ይጠቅማል።

- ከጥንተ ጠላታችን ጋር ላለብን የተጋድሎ ሕይወት መውጊያ አይነተኛ መሳሪያ ነው።

ረ. ፆም ድካምን አውቆ ሰውነትን ቅድመ እግዚአብሔር ለማዋረድ ይረዳል።

- ደካማ መሆናችንን አውቀን በትህትና በእግዚአብሔር ፊት ለማዋረድ ይረዳል።

ሰ. ፆም የፀሎት ምክንያት እናት ነች።

- ፆም የያዘው ሰው የመጀመሪያ ስራው ከእግዚአብሔር ጋር በመነጋገር ይጀምራል።

ሸ. ፆም ሕይወትን ዘለዓለም ለመውረስ ይረዳል።

- ፆም የፅድቅ መሰረት የገነት በር መግቢያ ይባላል ጿሚ ሰው የረሃቡን ፆር ስለሚያውቅ ለተራቡት ሰዎች ይራራል ለሌሎች መንፈሳዊ ስራዎች መሰረት ይሆናል።

4.2 የፆም ዓይነቶች

- ፆም በሁለት ዓቢይ መደብ ይመደባል።

4.2.1 የግል ፆም

4.2.2 የአዋጅ ፆም

4.2.1 <u>የግል ፆም</u>

- ሰዎች እግዚአብሔር ኃይልና ብርታቱን እንዲሰጣው የሚፆሙት ዓይነት ፆም ነው። ነገር ግን ከአዋጅ ጾም ጋር አንድ መሆን አይገባውም።
- ይህ ክፍል በሁለት ከፍለን እናየዋለን። እሱም፡-

ሀ. <u>የንስሐ የግል ፆም</u>

ምዕመናን ከመምህረ ንስሐቸው ጋር ተመካክረው ንስሐ ገብተው በአንቀፀ ንስሐ መሰረት ቀኖና ሲሰጣቸው የሚፆሙት ፆም ነው። ቀኖናው የሚፈፀመው ማንም ሳያውቅባቸው ነው።

ለ. <u>የፈቃድ የግል ፆም</u>

በግል ወይም በማኅበር ሊፈፀም ይችላል። የቤተክርስቲያን አዋጅ የማያስገድዳቸው አፅዋማት ሲሆን በፈቃደኝነት የሚፆሙት ይሆናል። እነሱም፡-

1. ***ፅጌ ፆም*** ፡-በእመቤታችን ቅድስት ድግል ማርያም ስም የሚፆም ነው ከመስከረም 26-ኅዳር6 በማኅሌት በሽብሸቦ ከድግል ማርያም በረከት ለማግኘት ይፆማል።
2. ***ፆመ ዮዲት*** ፡- እንደ ፅጌ ፆም የታወቀ ባይሆንም በአመቱ መጨረሻ ወር በጳጉሜ የሚፆም ነው መሰረቱም ዮዲት ጠላቷ ድል ለመንሳት ከእግዚአብሔር ኃይል ለማግኘት የፆመችው ፆም ነው።

<u>የግል ፆም ለምን ይፆማል?</u>

- በግል ሕይወታችን የገጠመን ችግር ካለ እንዲወገድልን
- መንፈሳዊ በረከት ለመጎናፀፍ ከእግዚአብሔር እንዲደረግልን የምንፈልገው ነገር ካለ ለመጠየቅ
- ምስጢር እንዲገለጥልን ከባዱና ጥልቅ የጥበብ ባህር ለመጎብኘት ለመረዳት
- መንፈሳዊ ስራ ለመስራት ስንፈልግ የፈጣሪያችንን ፈቃድ እርዳታ ለመጠየቅ
- ኃጢአታችንን በማሰብ፣ ስለወገኖቻችን ሞት፣ ሞተ ወልደ እግዚአብሔር፣ ግፍአ ሰማዕታትን በማሰብ እንፆማለን።

<u>ከመፆማችን በፊት ማድረግ ያለብን</u>

- ከምንም በፊት የጀመሩት ጉዳይ አጠናቆ መፈፀም ይገባል ሃሳባችን ወደዚያ እንዳይበተን።
- ከንስሐ አባት ጋር መመካከር ይገባል
- ግድ ማወቅ አለባቸው ለሚሏቸው ቤተሰቦቹ (ጓደኞቹ) መናገር ይገባዋል
- በፆም ወቅት የሚያስፈልጉት ነገሮች ቀድሞ ለይቶ ማሰናዳት ቀዳሚ ተግባሩ ማድረግ አለበት
- ጿሚው ሰው አቅሙን ማወቅ ይኖርበታል ምን ያል ጊዜ (ሰዓት) መፆም እንዳለበት ያለውን ጥንካሬ፣ ልምዱን፣ ፅናቱን ማወቅ ይኖርበታል። አለበለዚያ ገና ከመጀመሪያው ቀን አስራ ሁለት (12) ሰዓት እፆማለሁ ቢል ራሱ ሊጎዳ አልያም ለዲያቢሎስ ፈተና ራሱን ሊያጋልጥ ይችላል።
- የሚፆምበት ቦታ መምረጥ ቦታው ሕሊና ሊበትን የሚችል መሆን አይኖርበትም በፈተና የሚያጋልጥ ሁከት ግርግር የሌለበት ሊሆን ይገባዋል።
- ጿሚው የተለየ ዓላማ ሊይዝ በሚያሳልፋቸው የፆም እለታት እግዚአብሔር አምላኩን የሚጠይቀውን ጥያቄ ጠንቅቆ ማወቅና መዘጋጀት ይገባዋል።

4.2.2 <u>የአዋጅ ፆም</u>

- በአዋጅ በቤተክርስቲያን ቀኖና መሠረት ተነግሮ ሕዝቡ ሁሉ አውቆት በአንድነት የሚፆሙት ነው። በአዋጅ ፆም ሁሉም ሕዝብ ስለሚፆም ለውዳሴ ከንቱ አይደረግም ይልቅ በዚህ የአዋጅ ወቅት እፆማለሁ ማለት ሰበካ (ትምህርት) እንጂ ውዳሴ ከንቱ አይገባም።
- በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ስርዓት መሠረት ሁሉም ሊፆማቸው የሚገቡ አፅዋማት መጀመሪያቸው መጨረሻቸው ተቀምሮ ጊዜና ወቅት ተወስኖላቸው የተደነገጉ ናቸው።



- ቤተክርስቲያናች በአዋጅ የሚያሙት 7 አዕዋማት ናቸው። እነሱም፡-
  1. ዓቢይ ፆም
  2. የነቢያት ፆም
  3. የሐዋርያት ፆም
  4. ፆመ ፍልሰታ
  5. ፆመ ነነዌ
  6. ፆመ ድኅነት
  7. ፆመ ገሀድ ናቸው።

፩. ዓቢይ ፆም

- ይህ ፆም ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የፆመው ፆም ነው። ጌታችን የፆመው እቀደስ እከብር ወይም እነዛ ብሎ ሳይሆን ለእኛ አርአያ ለመሆን ነው።
- ዓቢይ ፆም በተለያዩ ስያሜዎች ይጠራል **<u>የካሳ ጾም</u>** አዳምንና ልጆች ለመካስ የጾመው በመሆኑ፣ **<u>የድል ፆም</u>** ሶስቱ አርእስተ ኃጣውእ ድል የተነሱ በመሆናቸው፣ **<u>የመሸጋገሪያ ፆም</u>** ከሕገ ኦሪት ወደ ሕገ ወንጌል በመፆም ያሸጋገረን በመሆኑ፣ **<u>የስራ መጀመሪያ ፆም</u>** ጌታ ስብከት ከመጀመሩ በፊት የፆመው በመሆኑ ነው።

<u>ዓቢይ የተባለበት ምክንያት</u>

፩. ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የፆመው በመሆኑ

፪. ሶስቱ የኃጢአት መነሻዎች (ስስት፣ ትዕቢት፣ ፍቅረ ንዋይ) የተረቱባቸው በመሆኑ

፫. ከሰባቱ አዕዋማት በቁጥር ብዛት የሚበልጠው እሱ በመሆኑ

ቅዱስ ያሬድ በፆመ ድጓው በዓቢይ ፆም ለሚገኙት ሰንበታት ሁሉ የተለየ መዝሙር ሰርቶላቸዋል። ሰንበታቱም፡-

፩. ዘወረደ (ሕርቃል)	፭. ደብረዘይት
፪. ቅድስት	፮. ገብርኄር
፫. ምኩራብ	፯. ኒቆዲሞስ
፬. መፃጉዕ	፰. ሆሳዕና

- ከሆሳዕና እስከ ትንሳኤ ያለው ሳምንት **ሰሙነ ሕማማት** ይባላል። ኢየሱስ ክርስቶስ ያያቸውን መከራ፣ መገረፍ፣ መተፋት፣ ጎን መወጋት፣ ሌሎች ስቃይ በማሰብ የምንሰነብትበት ነው። እንዲሁም ከአዳም ጀምሮ የነበሩት የአዳም ልጆች በእግረ አጋንንት ተረግጠው በሲኦል ያዩትን መከራ የምናስብበት ሳምንት ነው።

<u>የቤት ሰራ ጥያቄ</u>

፩. ጌታ የፆመው 40 ሌሊት መዓልት ነው እኛ ለምን 55 ቀናት እንፆማለን?

፪. አንዳንድ የሐሰት መምህራን ኢየሱስ ክርስቶስ አንዱ ሞቶልናል መፆም መፀለይ መከራ መቀበል አይገባም ይላሉ እናንተ እንደምን ታስቡታላችሁ የቤተክርስቲያን አባቶች በመጠየቅ መልስ ስጡ?



፪. **የነቢያት ፆም (የገና ፆም)**

- ይህ ከልደት አስቀድሞ የሚፆም ነው። ከኅዳር 15 ጀምሮ ታህሳስ 29 ይሔዳል። በአራት ዓመት አንዴ በ14 ጀምሮ በ28 ይፈታል። የነቢያት ፆም የተባለበት ዓቢይ ምክንያት ነቢያት ጌታ እንዲወርድ፣ እንዲወለድ የፆሙት ስለሆነ ነው። በሐዲስ ኪዳንም ሱባዔ የተቆጠረለት ትንቢት የተነገረለት ኢየሱስ ክርስቶስ መወለዱን እያሰብን እንፆማለን።

፫. **የሐዋርያት ፆም (የሰኔ ፆም)**

- ሐዋርያት መንፈስ ቅዱስ ከተቀበሉ በኋላ ለስብከተ ወንጌል ከመሰማራታቸው በፊት የፆሙት ፆም ነው። ይኸውም ከበዓለ ፶ (50) ቀጥሎ ባለው ቀን ሰኞ ጀምሮ እሰከ ሐምሌ 5 የሚፆም ነው። ፍሰካው በቅዱስ ጴጥሮስና ቅዱስ ጳውሎስ በሰማዕትነት ባረፉበት ዕለት ነው።
- ይህ ፆም በሃገራች **የወታደር ፆም** የሚልም መጠሪያ አለው ይህም ለውትድርና የተዘጋጀ ሰው ወይም ከግዳጅ የተመለሰ የሚፆመው በመሆኑ ነው። አንዳንዶች ሐዋርያት የጾሙት በመሆኑ የቁስ (ክህናት ላላቸው) ብቻ አድርገው ይናገራሉ። ነገር ግን ሁሉም ሕዝበ ክርስቲያን እንዲፆመው የቤተክርቲያን አዋጅ ይነግረናል።

፬. *ፆመ ፍልሰታ*

- "ተንስአ እግዚኦ ወለተ ዕረፍት አንተ ወታቦተ መቅደስ" አቤቱ ወደ እረፍትህ ተነስ አንተና የመቅደስህ ታቦት የዕላት ማደሪያ እንደሆነ ሁሉ እመቤታችንም ለክርስቶስ ማደሪያ ነች። ይህ ፆም ሐዋርያት የእመቤታችን ዕርገት ባለማየታቸው ይህ ታላቅ ነገር ለማየት የፆሙት ነው። እኛ ከእመቤታችን አማላጅነቷን ፍቅሯን በረከቷን ለማግኘት እንፆመዋለን። ከነሐሴ 1-16 የሚፆም ነው።

፭. *ፆመ ነነዌ*

- ለሦስት ቀናት የምንፆመው ፆም ነው። በቤተክርስቲያን የአዕዋማት ማውጫ ቀመር ከፍም ዝቅም ይላል። ይህ ፆም ሰብአ ነነዌ እግዚአብሔርን በማስቆጣታቸው በነቢዩ ዮናስ አማካኝነት መክሮአቸው (ገስጿቸው) ስለኃጢአታቸው ፆመው ከመከራ (ቅጣት) የዳኑበት ነው። እኛም በፆምና በፀሎት ከፈጣሪያችን ምህረት ይቅርታ ለማግኘት ስንል እንፆመዋለን። ይህ ፆም ለዓቢይ ፆም መዘጋጃም በመሆን ያገለግላል።

፮. *ፆመ ድኅነት (ረቡዕና አርብ)*

- ረቡዕና አርብ በየሳምንቱ በሚያደርገው ዑደት እንፆመው ዘንድ ሐዋርያት አዘውታል።
- ረቡዕ መፆማችን በአይሁድ ሸንጎ የኢየሱስ ክርስቶስ ምክረ ሞቱ ተፈፅሞበታልና።
- አርብ መጾማችን ለ5500 ዘመን ሲጠበቅ የነበረው የጌታችን ፈቃደ ድኅነት ዓለምን ለማዳን በመስቀል ላይ ተደርጎባታልና እንፆመዋለን።
- ከድኅነት ጋር የተስተካከለ በመሆኑ ፆመ ድኅነት ተብሏል። ሐዋርያት ዓርብና ረቡዕ በዓለ ልደት በዓለ ጥምቀት በበዓለ አምሳ ቢውሉባቸው አይፁሙ ብለዋል ይህም የሆነው እነዚህ ዕለታት የሰላም የፍስሐ ጊዜ በመሆናቸው ማዘን መጨነቅ መራብ አይደረግባቸውምና ነው።

፯. *ፆመ ድኅረ ጥምቀት (ገሀድ)*

- የጥምቀት ዋዜማ ነው። አንዳንዶች የነቢያት ፆም ገሀድ አለው ብለው ያስተምራሉ ይህ ግን ፈፅሞ ትክክል ያልሆነ ነው። ገሀድ ያለው ለጥምቀት ብቻ ነው። መለወጥ ያመለክታል።



ምዕራፍ አምስት (፭)

አንቀፅ ፲፱ ስለ በዓላት

ስለ ዕለተ እሑድ፣ ስለ ዕለተ ቀዳሚት፣ ስለጌታ በዓላት ስለሚከበሩበት ምክንያት

- በዓል ማለት ለአምልኮ የተለየ ጊዜ (ዕለት) ነው፡፡ ነቢዩ ዳዊት "ግበሩ በዓለ ለትፍስሕት" በደስታ በዓል አድርጉ /መዝ 117፥27/ ታላቅ የቸርነት ስራውን ለማመስገን ለመመስከር በዓሉ ከሚደረግለት ባለቤት ረድኤትና በረከት ለማግኘት ልዩ የአምልኮ ጊዜ ማዘጋጀት (በዓል ማድረግ) አስፈላጊ መሆኑን ገልጿል፡፡

በዓል በምናደርግበት ጊዜ መከወን ያለብን

- በዓሉ ስለሚደረግበት ዓቢይ ምክንያት መረዳት ይህም ለምናደርጋቸው ነገሮችን እውቀት እንዲኖረን ይረዳናል፡፡
- በትሕትና በንፅህና መምጣት ይገባል፡፡
- በከንቱ ስራ መፍታት ሳይሆን በበዓሉ የታዘዙትን መንፈሳዊ ስራዎች በመፈፀም መዋል ይገባል፡፡
- በመንፈሳዊ ተድላ ደስታ ሊደረግበት ይገባል ይህም በዝማሬ በሽብሻቦ ሊከበር እንደሚገባ ያስገነዝባል፡፡
- የሚቻለው ከሆነ በዓሉ በልዩ ሁኔታ በሚከበርበት በሚታሰብበት ቤተክርስቲያን ያክብር፡፡
- በዓሉ በሚደረግበት ባለቤት ስም መዘከር ቀዝቃዛም ውሃ ቢሆን መስጠት ተገቢ ነው ምክንያቱም የፃድቁ ዋጋ ማግኘት እንችላለንና፡፡
- ባልና ሚስት በዓል ለማክበር ሲመጡ ከሩካቤ ስጋ መከልከል አለበት፡፡
- ምዕመናን ለበዓል ለመምጣት ሲዘጋጁ ለቤተክርስቲያን የሚገባውን ክርስቲያናዊ አለባበስ መልበስ ይኖርባቸዋል፡፡ ይህ ማለት ነጭ የሆነ ረጅም ልብስ መሆን ይኖርበታል ነገር ግን እንደዚህ ያለ ነገር ማግኘት ለማይችል ሰው ያለውን አጥቦ መልበስ ይኖርበታል፡፡
- ሴቶች ረዘም ያለ አለባበስ ዓለማዊ የሆነ ጌጣጌጥ አውልቀው መምጣት ይኖርባቸዋል ወንዶችም ሰፋ ያለ እና ነጠላን አመሳቅለው ለብሰው መምጣት ተገቢ ነው፡፡

በዓልን ቤተክርስቲያን ተገኝቶ ማክበር ጥቅሙ

- ክርስቲያን ሁሉ መረዳት ያለበት የመጀመሪያው ነጥብ በቅዱሳኑ ስም የሚደረግ የመታሰቢያ በዓል የሚያከብረው የሚያነግሰው የቅዱሳን አባት እግዚአብሔርን መሆኑ ነው፡፡ በቅዱስ ሚካኤል፣ በቅዱስ ጴጥሮስ ስም በዓል ቢደረግም የሚከብረው ግን እግዚአብሔር ነው፡፡
  - ✓ በዓሉ ከሚደረግለት ቅዱስ (ፃድቅ) ረድኤት በረከት ማግኘት ያስችላል፡፡
  - ✓ ቅዱስ ጳውሎስ ለዕብራውያን ሰዎች እንደፃፈላቸው /ዕብ 13፥7/ "የእግዚአብሔር ቃል የተናገሯችሁን ዋኖቻችሁን አስቡ፡፡" ባለው መሰረት የቅዱሳኑን ፍኖት እንድንረዳና እነርሱ በአስተከሉን መልካም ጎዳና ለመጓዝ ይረዳናል፡፡
  - ✓ ክርስቲያኖች በሕብረት ሆነው (ተሰብስበው) ከእግዚአብሔር ጋር ለመገናኘት ያስችላል፡፡
  - ✓ የቅዱሳን በዓል ከሆነ ፈተናን ያለፉበትን ጥበብና ተጋድሎ እንማርበታለን፡፡ መንፈሳዊ ቆራጥነትና ጀግንነት እናይበታልን፡፡
  - ✓ የእግዚአብሔር ጠባቆት እናይበታለን እግዚአብሔር እንዴት ባለ ጠባቆቱ ቅዱሳኑን እንደሚረዳ እናያለን፡፡
  - ✓ የራስን ባዶነት ለማወቅና ከትዕቢት ያር ለመዳን ይጠቅማል፡፡ ቅዱሳኑ ምንም እግዚአብሔር ያከበራቸው ታላላቆች ቢሆኑም ራሳቸውን በትህትና አስገዝተው ኖረዋል፡፡ ስለዚህም ቅዱሳን ይህ ክብር እያላቸው ዝቅ ሲሉ እኛማ ካለን ከትዕቢት ኃጢአት መጠበቅ እንችላለን፡፡



ስለ ሰንበት

- በዕብራይስጥ የቃሉ ትርጉም ***ማቆም መተው*** ማለት ነው፡፡ እግዚአብሔር ፍጥረታትን ፈጥሮ በሰንበት አርፏልና፡፡ ይህም አምላካችን ያረፈበት ቀን ሰንበት በመባል ይታወቃል /ዘፍ 2፥2/ ከ10ቱ ትዕዛዛት ውስጥ አንዱ ደግሞ ሰንበትን ማክበር ነው፡፡ /ዘፀ 20፥8/
- ሰንበትን ማክበር እንደሚገባ መጽሐፍ ቅዱስ እንደ ግዴታ ይደነግገዋል፡፡/ዘፍ፡15፥32-36/ በሰንበተ ክርስቲያን እንኳን ሰው እንስሳትም እንዲያርፉ እግዚአብሔር አዟል፡፡ /ዘዳ 5፥12-16/ እስራኤላውያን ሰንበታትን ባለማክበራቸው እግዚአብሔር በነቢያት የገሰፀበትን ጊዜ እናስታውሳለን፡፡ /ሕዝ 20፥12-16/ ኢሳ 8፥6/ ለሚያከብሩት ደግሞ የዘለዓለም መታሰቢያን እንደሚሰጣቸው ተናግሯል፡፡ /ኢሳ 56፥2-4/ የአባቶቻቸውን በረከትም እንደሚሰጣቸው ተናግሯል፡፡ /ኢሳ 58፥13-14/
- ሰንበት የሚለውን ቃል በሁለት አገባብ ብዙውን ጊዜ እናውቃለን እነሱም፡- **ቀዳሚት ሰንበትንና ሰንበተ ክርስቲያን** በመባል ነው፡፡

ቀዳሚት ሰንበት

- እግዚአብሔር የፈጠረውን ፍጥረት በጊዜ መለካት ሲጀምር ቋሚ መለኪያ ያደረጋቸው ሰባት እለታት ነበሩ እነዚህም በዐደት (በዙረት) ተመልሰው የሚመጡ መለኪያዎች ናቸው፡፡ "ሰባቱ ምስሶች አለትንም አፀናው" እንደተባለ /ምሳ 9፥1/ እግዚአብሔር ጊዜን ለመለኪያነት ሊለካበትና ፍጥረቱን ሊመግብበት አንዱ እና ሰባተኛውን (ቀዳሚት ሰንበትን) በዚያው በመጀመሪያነቱ የተቀደሰች የተከበረች በዓል አደረጋት፡፡ /ዘፍ 2፥3/ በኋላም በሙሴ ሕግ እስራኤል ከ10ቱ ትእዛዛት አንዱ አድርገው እንዲተገብሯት ተሰጥታለች፡፡ /ዘፀ 20፥5/
- በብሉይ ኪዳን ዘመን በዓላት ጥንትነታቸውን ቀዳሚት ሰንበት ነበረች ቀዳሚት ሰንበት ለበዓላተ አይሁድ ወይም ለብሉይ ኪዳን በዓላት ጥንትነታቸው ብቻ ሳትሆን ወክላ መጠሪያቸው ጭምር ነበረች፡፡ "የምቀድሳቸውን እኔ እግዚአብሔር እንደሆንሁ ያውቁ ዘንድ በእኔና በእርሱ መካከል ምልክት ይሆን ዘንድ ሰንበታቴን ሰጠዋቸው" ተብሎ ተፅፏል /ሕዝ 20፥12/ ሰንበታቴ ብሎ ያበዛቸው በብሉይ ኪዳን ሌላ በዓል የለም ነበር ታዲያ እንደምን ነው? ቢሉ፡-
  - በአንባር ቀዳሚት ሰንበት ስለሌሎች በዓላት መናገሩ
  - ቀዳሚት ሰንበት በብዙ ቁጥር የበዓላት መጠሪያ ሆኖ እንዳገለገለች ያስረዳል
  - በብሉይ ኪዳን ዘመን የወል መጠሪያቸው መሆኗን ለመግለፅ /ዘሌ 23፥32/

ሰንበተ ክርስቲያን እና እረፍት

- እረፍት ከስጋ ብቻ አያይዘን ካልተረጎምነው በቀር በሰንበትና በበዓላት ላይ ብዙ ነገሮች ያካትታል፡፡ የቀደመው የአይሁድ አስተሳሰብ በዕለተ ቀዳሚት ተግባር ማጉደል ላይ ያተኩራል፡፡ ነገር ግን በዚህች ዕለት በዕለተ እሁድ እንደ ክርስቲያን ይስሩ እንጂ ሁሉንም ነገር አልተከለከሉም፡፡ ኒቂያ ፳ "ወኢተአቀቡ ሰንበተ ከመ ኢይሁድ" እንደ አይሁድ ቀዳሚትን አትጠንቀቁ እንዲል፡፡
- የሰንበተ ክርስቲያን አከባበር ታሪክ ከመጀመሪያው ምእተ ዓመት የክርስትና ታሪክና የወቅቱ የአምልኮ ስርዓት ነጥለን ልንመለከተው አንችልም፡፡ እስከ ቆስጠንጢኖስ መነሳት ድረስ ክርስቲያኖቹ የሚሰደዱበት መከራ የሚቀበሉበት ብቻ ሳይሆን በዓለም ላይ ለሚነሳው ቀውስ ሁሉ ምክንያት ተደርገው የአፀፋውን ቅጣት የሚቀበሉበት ጊዜ ነበር፡፡ ስለዚህም የመጀመሪያዎቹ ዘመን አምልኮ (ክርስትና) በድብቅና በዋሻ እንደነበር የቤተክርስቲያን ታሪክ ያስረዳል፡፡ ነገር ግን በዚህ ሁኔታ ውስጥም ያከብሩ ነበር፡፡
- በመጀመሪያ ሰንበት ማክበር የጀመረችው በማርቆስ እናት ቤት ጌታ ካረገ በኋላ ባሉት ዕለታት ወይም ከበዓለ አምሳ ጀምሮ ነው፡፡/ሐዋ 2፥1/ አጀማመሩ በሐዋርያት ከመሆኑ በላይ ፍስሐ መንፈሳዊ የሚደረግበትና ስርዓተ አምልኮ የሚፈፀምባት ነበረች፡፡ ይህም አከባበር የሰንበት ማዕድ አብሮ ለመቁረስና በፍፁም ልባዊ ፈቃድ በመንፈሳዊ ሀሴት ገንዘብ ከሌሎች በማካፈል ይፈፀም ነበር፡፡



- ሰንበተ ክርስቲያን (ዕለተ እሁድ) በአዋጅ እንዲከበር ያደረገው ንጉስ ቆስጠንጢኖስ ነው። የተጀመረው ግን ቀድመን እንደተናገረው በመጀመሪያው ክርስቲያኖች በሐዋርያት ነበር።
- ዕለተ እሑድ የብዙ ነገር መጨረሻ ነች ዓለም የተፈጠረባት፣ ጌታ የተነሳባት፣ ጌታ የተወለደባት፣ ድኅነታችንን ያገኘንበት፣ የትንሳኤ ነገር የተከወነበት፣ ወደ ፊት ጌታ ይመጣበታል ተብሎ የሚታሰብበትና ታላላቅ የቤተክርስቲያን ምስጢራት የተፈፀመባት ስለሆነች በዕለተ እሁድ በሐዲስ ኪዳን በታላቅ መንፈሳዊ ስራ እናከብራለን።

<u>ሰንበት እንዴት ይከበራል?</u>

- በዕለተ እሑድ ስግደት ማድረግ አይገባም። /ፍት.ነገ 19፡715/
- እንደ አይሁድ አከባበር ሰውነት ከስራ አርፎ ልብ ግን በክፋት ስራ ውስጥ መስመጥ ሳይሆን ልቦናችንን በመንፈሳዊ ስራ በማትጋት
- በቤተክርስቲያን በመሰባሰብ (ዲድስቅልያ 12) በከንቱ መሰባሰብ ግን አትሰብሰቡ/ ፍት.ነገ 19፡718/
- ግኖስቲኮች እስዳስተማሩ ሰንበት በያም ማሳለፍ አይገባም ከቅዳመ ስዑር በቀር የሚያም ሰው በሐዋርያት ተወግሏል። ካህን ቢሆን ከክህነቱ ይሻር ምዕመን ከሆነ ደግሞ ከምዕመን ይለይ የሚል ነው።
- በፀሎት በትምህርት መቆየት
- የታመመ መጠየቅ፣ የታሰረ መጠየቅ፣ የተጣሉ ማስታረቅ፣ የታረዙ ማልበስ፣ የተራበ ማብላት ይገባል።

- ይህ ማለት ግን ክርስቲያናዊ ምግባራት በዕለተ ሰንበት መፈፀም አለበት ማለት ሳይሆን በተለየ ሁኔታ መንፈሳዊ ስራ ለመስራት የምንጣደፍበት ከስጋዊ ጭንቀት (ስራ አለብኝ፣ አለቃዬ) ከሚል የሀሳብ ሁካታ ነፃ ሆነን ለመከወን ስለሚረዳ ነው በተረፈ ሁልጊዜም ቢሆን በጠዋት በማታ ከክርስቲያናዊ ምግባር መራቅ የለብንም።

<u>ዓበይት በዓላት</u>

- የጌታ ዓበይት በዓላትና ንዑስ በዓላት ተብለው የተከፈሉበት ምክንያት በግልፅ የተቀመጠ ባይሆንም ይሁን እንጂ በተፈፀመባቸው በተደረገባቸው ተዓምራት መሆኑ ግን ከብዙ መጽሐፍት መረዳት ይቻላል።
- የጌታ ዐበይት በዓላት ቁጥራቸው ዘጠኝ(9) ሲሆን እንደሚከተለው እንመለከታቸዋለን ነገር ግን አንዳንድ ሊቃውንት ዕለተ እሑድን በማሰብ የጌታን በዓላት ሰባት (10) የሚያደርጓቸው አሉ።

፩. በዓለ ትስብእት (ጽንሰት)

- ይህ በዓል በአዋድያት ካልሆኑት ወስጥ ነው። በየአመቱ **መጋቢት ሃያ ዘጠኝ (29)** ይከበራል። ጥንተ እለቱ እሑድ ስለሆነ በየእለቱ የሚውሉ (የሚከበሩ) በዓላት አዋድያት አይደሉም። ሁልጊዜም መጋቢት 29 ይከበራል።
- ትስብእት ቃሉ ራሱ የአምላክን ሰው መሆን ያስረዳል። ይህ መላዕኩ ቅዱስ ገብርኤል ለድንግል ማርያም የአምላክን ከእርሷ ሰው መሆን ያበሰረበት አካለዊ ቃል ወልድ እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስ የእለት ጽንስ ሆኖ በማኅፀኗ ያደረበት መታሰቢያ በዓል ነው። ይህም በመንፀፈ ደይን ወድቆ ለነበረው የሰው ዘር ተስፋ ድኅነት የተጀመረበት የምሕረት የይቅርታ ቀን ነው። በዚህም ምክንያት ክርስቲያኖች እንዲያከብሩት ፍትሐ ነገስት ያዛል።

፪. በዓለ ልደት

- ይህ በዓል አካላዊ ቃል ወልደ እግዚአብሔር ከቅድስት ድንግል ማርያም ከስጋዋ ስጋ ከነፍሷ ነፍስ ነስቶ ሰው ሆኖ የተወለደበት ዕለት መታሰቢያ ቀን ነው። ይህም የሰው ዘር ለማዳን የተደረገ በመሆኑ ደገኛ በዓላችን ነው።

- በዓሉ በየዓመቱ **ታኅሳስ ሃያ ዘጠኝ** (29) የሚከበር ሲሆን በዘመነ ዮሐንስ ግን የዘመነ ሉቃስ ጳጉሜ ስድስት ስለምትሆን **ታኅሳስ ሃያ ስምንት** (28) ይከበራል፡፡ ይህ ሰርዓት ሆኖ በግልፅ ተቀምጧል፡፡
- በዓሉን የሚያከብር ሰው የሚያገኘው ጥቅም ሊቃውንቱ "እመቦ ዘአክበረ ልደተ እግዚእ ይከውን ክብሩ ምስለ ሰብአ ሰገል" "የጌታችን በዓለ ልደት የሚያከብር ሰው ክብሩ በተወለደ ጊዜ ተገኝተው መበዐ እንደሰጡት እንደሰብአ ሰገል ይሆንበታል፡፡" ብለዋል
- "ወይኩን ገብረ ቁርባን በልደት ወጥምቀት መንፈቀ ሌሊት" በልደትና በጥምቀት ቅዳሴ በመንፈቀ ሌሊት ይሁን፡፡

፫. በዓለ ጥምቀት

- ጌታችን ሰውን ለማዳን ሰው ሆኖ ከተገለጠ በኋላ የማዳን ስራውን የጀመረው በጥምቀት ነው፡፡ የተጠመቀው በ ሠላሳ ዘመኑ ሲሆን አጥማቂው የካህኑ የዘካሪያስ ልጅ ቅዱስ ዮሐንስ ነበር፡፡ ጌታችን በተጠመቀበት ጊዜ አብና መንፈስ ቅዱስ የባሕርይ አምላክነቱን መስክረዋል፡፡/ማቴ 3፥17/ ዮሐ1፥32-34/
- ይህ በዓል ቤተክርስቲያን በአራት ዘርፍ ትመረምረዋለች፡፡ እነሱም፡-
  - ሀ. ትንቢቱን ለመፈፀም
  - ለ. ውሃን ለመቀደስ
  - ሐ. ለጥምቀት ኃይል ለመስጠት
  - መ. ለእኛ አርአያና ምሳሌ ለመሆን (ያሳየውን ትሕትና ለመመስከር)
- የአከባበሩ ስርዓት ስንመለከት ከሌሎች በዓላት የሚለይበት መንገድ አለው፡፡ይኸውም ታቦታቱ ከመንበረ ክብራቸው የሚወጡበት በመሆኑ ነው፡፡ እንደተገለፀው ታቦት በዋዜማው ከቤተክርስቲያን ወጥተው በሕዝብ ታጅበው እግዚአብሔር እየተመሰገነ ወንዝ ዳር ይወርዳሉ (ታቦተ ማደሪያ) በዚያም ዳስ ተጥሎ (ድንኳን ተተክሎ) ከተራ ተከትሮ ሌሊቱን መዘምራኑ በማኅሌት ካህናቱ በሰዓታት እግዚአብሔርን ሲያመሰግኑ ያድራሉ፡፡ ይህም ጌታ ከገሊላ ወደ ዮርዳኖስ የመሐዱ ምሳሌ ነው፡፡ ሲነጋም ፀሎት ቅዳሴው ተጠናቅቆ ወደ ወንዙ (ወደ ተከለለው ውሃ) በመሔድ ፀሎተ አኩቴት ተደርሶ አራቱ ወንጌላት ከተነበበ በኋላ ውሃው ተባርኮ ለተሰበሰበው ሕዝብ ይረጫል፡፡
- ይህ በዓል የሚከበረው **ጥር አስራ አንድ** (11) ቀን ነው፡፡ በዓሉ ዕለተ ረቡዕ ቢሆን እንኳን አይፆምም፡፡ ረቡዕ ከዋለ ማክሰኞ፣ አርብ ከዋለ ደግሞ ሐሙስ ይፆማሉ፡፡
- ይህም ቤተክርስቲያን ስለበዓሉ ያላትን አመለካከትና ቦታ ያሳያል፡፡ በዚህ ዕለትም ስጋዊ ስራ ፈፅሞ የተከለከለ ነው፡፡ በምዕመናን ዘንድም መክበር እንዳለበት /ፍት.ነገ 19፡726/ ያዘናል፡፡
- በአሁኑ ጊዜ ከሃይማኖትም አስተሳሰብ በላይ ሆኖ በቱሪስት መስህነቱ የየትኛውም ሃይማኖት ተከታይ ለክብረ በዓል ተዘጋጅቶ "የሚያከብርበት" ሁኔታ እየታየ ነው፡፡ ስለዚህም ይህ የሀገር ሀብት ከሆነው የጥምቀት አከባበር እንዲቀጥል ሁሉም የበኩሉን ድርሻ ማድረግ አለበት፡፡

፬. በዓለ ደብረ ታቦር

- በዓሉ የሚከበርበት ምክንያት ደግሞ ጌታችን በዘመነ ስጋዌ በሚያስተምርበት ወቅት ምስጢረ መንግስቱንና ብርሃነ መለኮቱን የገለጠበት በመሆኑ ነው፡፡ /ማቴ 17፥4/ ይህ ጉዳይ ከቅዱስ ዮሐንስ በቀር ሦስቱም ወንጌላውያን መዝግበውታል፡፡ /ማር 42-13/ ሉቃ 9፥28-36/ ከዚህ በተጨማሪም /2ኛ ጴጥ1፥17-18/ ገልፆታል፡፡
- በኦሪት ፊት አሳየኝ ብሎ የለመነውን ሙሴ ከሙታን አስነስቶ ስለክብሩ የቀናውን ኤሊያስን ከብሔረ ሕያዋን አምጥቶ ክብሩን አሳይቷቸዋል፡፡ /ዘፀ 33፥19/ ከሐዋርያት ደግሞ ያዕቆብ፣ ጴጥሮስ፣ ዮሐንስን
- በዓሉ የሚከበረው **ነሐሴ 13** ቀን ነው፡፡ በዓሉ ከጥንታዊና ምስጢራዊ ከመሆኑ አስተሳሰቦች በመነሳት በኢትዮጵያ የተለየ የአከባበር ስርዓት አለው፡፡
- ይህ በዓል "**ቡሄ**" በሚል መጠሪያ በኢትዮጵያ በሰፊው ይታወቃል፡፡ ቡሄ ማለት መላጣ (ገባጣ) ማለት ነው፡፡ በሀገራችንም ክረምቱ አልፎ የብርሃኑ ወገግታ የሚታይበት ወቅት በመሆኑ ነው፡፡ "ዶሮ ከጮኸ የለም ሌሊት ቡሄ ካለፈ የለም ክረምት" የሚለው ብሂል ይህን ያስረዳናል፡፡



- በበዓሉ፡- ➲ **የጅራፍ መጮኽ**....የድምፀ መለኮት
  - ➲ **ጅራፍ ሲጮህ መደንገጣችን**...ሐዋርያት በድምፀ መለኮት መውደቃቸውን
  - ➲ **ችቦ ማብራታችን**.....በደብረታቦር ለታየው ብርሃነ መለኮቱ ምሳሌ
  - ➲ **ዳቦ መሰጣጣቱ**.....በተራራው ግርጌ ይጠብቁ የነበሩ እረኞች ብርሃን በተራራ ላይ ሲገለፅ ቀን መስሎአቸው በማምሸታቸው ወላጆቻቸው ችቦ እያበሩ ሙልመል ይዘው የመፈለጋቸው ምሳሌ ነው።

፩. በዓለ ሆሳዕና

- ሆሳዕና ማለት **መድኃኒት** ማለት ነው። ይህም ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ኢየሩሳሌም ገብቶ የተመሰገነበት ነው። በዚህ ዕለት አቀባበል ያደረጉለት የሰው ልጆችም በቅዱስ ዳዊት አስቀድሞ እንደ ተናገረው "ሆሳዕና ለዳዊት ልጅ በጌታ ስም የሚመጣ የተባረከ ነው ሆሳዕና በአርያም" እያሉ አመስግነውታል።/ማቴ21፥9/
- የበዓሉ አከባበር ሌሊቱን ስብሐተ እግዚአብሔር ሲደርስ ያድርና ጠዋት የቅዱስ ያሬድ መዝሙር እየተዘመረ በአራቱም ማዕዘናት አራቱ ወንጌላት ይነበባሉ ከዚያም የዘንባባው ዝንጣፊ ተባርኮ በካህናተ ዝማሬ ታጅቦ ለሕዝቡ ይታደላል። ምዕመናኑም የመስቀል ምልክት በመስራት በቤታቸው ይሰቅሉታል በራሳቸው እንደ አክሊል ይቀዳጁታል አንዳንዶች እንደ ቀለበት እየሰሩ በጣታቸው ያደርጉታል።
- እለቱ የሰሙነ ሕማማት ዋዜማ ስለሆነና ሰሙነ ሕማማት የዓመተ ፍዳ የዓመተ ኩነኔ መታሰቢያ ሳምንት በመሆኑ ፀሎተ ቡራኬ፣ ፀሎተ ፍትሐትና ፀሎተ አስተሥርዮ ስለማይፈፀምበት በዚህ ዕለት ለሳምነቱ የሚገባውን ሁሉ ይፈፀማል።
- በዚህም ምክንያት ሆሳዕናን "የይፍቱን ዕለት" እያሉ የሚጠሩ ብዙ ናቸው። በአንዳንድ ቦታዎች ደግሞ (በአክሱምና በእንጦጦና ማርያም) ምሳሌውን አጉልተው ለማሳየት አህያ ጭነው (ሰው አስቀምጠው) ስርዓተ ዑደት ይፈፅማሉ።
- በዓሉ ትንሳኤ ከመከበሩ በፊት ያው የመጨረሻው የዐቢይ ሳምንት እሁድ ነው። በነዚህ ምክንያት "መድኃኒት" እያልን በታላቅ ስነ-ስርዓት እያሰብን የምናከብረው በዓል ነው።

፪. በዓለ ስቅለት

- ይህ በዓል ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለዓለሙ መድኅን ሆኖ የተሰጠበት ራሱን መስዋዕት አድርጎ ያቀረበበት ዕለት ነው። ታሪኩ በአራቱ ወንጌላት ተዘርዝሮ ይገኛል።
  - ✞ **የስቅለት አከባበር** ፡- ከጠዋት ፀሎት በኋላ የቤተክርስቲያን መቅደስ በጥቁር ጨርቅ ይሸፈናል። የስነስቅለቱ ስዕል በመቅደሱ መካከል ከፍ ብሎ ይሰቀላል። በዙሪያው መስቀሎች ሻማዎች ይደረግበታል። ካህናቱም የዕለቱን አገልግሎት የሚፈፅሙት ጥቁር ልብሰ ተክህኖ በመልበስ ሲሆን ይህም ሀዘንን ለመግለፅ የሚደረግ ነው።
- በዚህ እለት የሚደረጉት ንግግሮች ትምህርቶች (ስብከቶች) እና ጸሎቶች በሙሉ ነገረ ስቅለቱን የሚያዘክሩ ሲሆኑ የሚቀርቡትም በሚያስተዛዝን ሁኔታ ነው። ፀሎቱ ሲጠናቀቅ ከቀኑ አስራ ሁለት ሰዓት ላይ በፓትርያርኩ ወይም በሊቀጳጳስ ወይም በቤተክርስቲያኑ ውስጥ በተገኘው ትልቅ አባት እየተመራ ኪራያላይሶን ይባላል።
- ካህናቱ መቅደስ ውስጥ ገብተው ከዘመሩ በኋላ ከቤተመቅደስ ወጥተው ሦስት ጊዜ እየዞሩ ይምራሉ። ከዚህ በዓል ከካህናቱ ወይም ከአረጋውያኑ ካሉት (ከቤተክርስቲያኖች አባቶች) ውስጥ በመዓረግ ታላቅ የሆነው የስነ-ስቅለቱን ስዕል በመንበሩ ላይ በነጭ በፍታ ይሸፍነዋል። የግንዘቱ ምሳሌ ነው።
- ከዚህ በኋላ ከመንበሩ ሰሜንና ደቡብ ጫፎች ላይም ሁለት ሻማዎች ይበራሉ እነዚህም ነጭ ለብሰው ከመቃብሩ ራስጌና ግርጌ የተገለፁት መላዕክት ምሳሌዎች ናቸው። /ዮሐ 20፥10/ ይህ በዓል ለየት ያለ አከባበሩ በሦስት ዐበይት ሰዓታት (ሠለስቱ፣ስድስቱ ተሰዓቱ) ሰዓታት ፀሎታት የሚደርሰው የጸሎተ ወንጌል ስርዓት የስግደት ስርዓት በልዩ አኳኋን ይከናወናል።



- ይህ በዓል ከሌሎች በዓላት የሚለይበት ከአዝማደ መባዕልተ ተከልክለን ለብዙ ሰዓት እየፆምን የምናሳልፈው መሆኑ ነው። በስርዓቱ መጨረሻ 400 እግዚኦታና 400 በእንተ ማርያም መሐረነ ክርስቶስ በዐራቱ ማዕዘናት ይደርሳል። ከዚህ በኋላ ምዕመናኑ በሰሙነ ሕማማት የሠሩትን ይናዘዛሉ። ቄሱም በወይራ ቅጠል እየጠበጠበ ቀን ሙሉ ከሰገዱት በላይ ተጨማሪ ስግደት ይሰጣቸዋል። ጥብጣቤው የተግሳፅ ምሳሌ ነው።
- ካህናቱ በማስተዛዘል በአንዱ ስንኝ ሲያነብ በዚያ ያሉት ሁሉ በአንድ ቃል "ለይሁዳ ወልዱ ወዉሉደ ውሉዱ ይደምሰስ" የሚለውን ይመልሳሉ። የዚህ ስንኝ መጨረሻ "ወፈኖቶሙሉ ለኃጥኢተ ትጠፍእ" "የክፍዎች መንገድ ግን ትጠፋለች" የሚል ነው ከዚያም የሚበራውን ጧፍ ያጠፋሉ። ምዕመናኑም በዚህ ጊዜ እያጨበጨቡ በእልልታ እግዚአብሔርን ያመሰግናሉ። በመጨረሻ መዘምራኑ ዝማሜውን ዘምመው ተፀንፅሎ ከተፀፋ በኋላ "ንሴብሐ" የሚለው ወረብ ይወረባል። ከዚያ ኑዛዜ ተሰጥቶ ሠርሆት (ስንብት) ይሆናል።
- በዕለተ ስቅለት (ዓርብ) የተፈፀሙ ድርጊቶች፡-
  - በሐሰት መሰከሩበት በሊቀካህናቱ ፊት
  - ለጲላጦስ አሳልፈው በመስጠት በፖለቲካዊ ክስ በሐሰት መሰከሩበት
  - ጲላጦስ ወደ ገሊላው ገዥ ወደ ሄሮድስ ልኮ በዚያ ተጠየቀ
  - ሄሮድስ ንቆት ወደ ጲላጦስ መለሰው ጲላጦስም መረመረው
  - ጲላጦስም በርባንን ፈትቶ ኢየሱስን ግን ገርፎው ይሰቅሉት ዘንድ አሳልፎ ሰጣቸው
  - ቀይ ግምጃ ልብስ አልብሰው የሾህ አክሊል ደፍተው ዘንግ አስይዘው ዘበቱበት።
  - መስቀሉን አሸክመው ሊሰቅሉት ወሰዱት።
  - በስድስት ሰዓትም በመስቀል ላይ ቸንክረው በሁለት ወንበዴዎች መካከል ሰቀሉት።
  - ልብሱን ለአራት ተካፈሉት በእጅ ጠባቡም ላይ ዕጣ ተጣጣሉበት።
  - በመስቀል ላይ ተፋበት ሆምጣጤ አጠጡት ጎኑን በጦር ወጉት
  - ከስድስት እስከ ዘጠኝ ሰዓት ሲሰቃይ ቆይቶ ነፍሱን ሰጠ።
  - ዮሴፍ ዘአርማትያስ እና ኒቆዲሞስ በአዲስ መቃብር ቀበሩት። /ማቴ26፥27-61/ ማር 14፥15-53/ ሉቃ 22፥54-56/ ዮሐ 18፥12/
- 13ቱ **ሕማማተ መስቀል** የሚባሉት በጌታ ላይ የደረሱት ሕማማት በዚሁ እለት የተፈፀሙ ናቸው። እነሱም፡-
  1. ተስርኦተ ርእሰ (ራሱን መምታት)
  2. ተአሰሮ ድኃሪት (የኋሊት መታሰሩ)
  3. አክሊለ ሶክ (የሾህ አክሊል መድፋት)
  4. ከትየ ሐሞት (ሐሞት መጠጣቱ)
  5. ወዲቀ ምድር (በምድር ላይ መውደቁ)
  6. ተቀስፎተ ዘባን (ጀርባውን መገረፉ)
  7. ፀዊረ መስቀል (መስቀል መሸከሙ)
  8. ተፀፍኦተ መልታህት (በጥፊ መመታት)
  9. ሳዶር
  10. አላዶር
  11. ዳናት
  12. አደራ
  13. ሮዳስ

  → **አምስቱ ቅንዋት(ችንካሮች)**

- ***<u>በዕለተ አርብ በስቅለት እለት የተፈፀሙ ተዓምራቶች፡-</u>***
  - ፀሐይ ጨለመች
  - የመቃብር መከፈት
  - ጨረቃ ደም ሆነች
  - የመ·ታን መነሳት
  - ከዋክብት ረገፉ
  - የቤተመቅደስ መጋረጃ ለሁለት መቀደድ ናቸው።
  - አለቶች ተሰነጣጠቁ



- በአጠቃላይ እስከ አሁን የዘረዘርናቸው ታላላቅ የቤተክርስቲያን ትምህርት ይህ በዓል ምን ያህል በክርስትና እምነት ውስጥ መሠረት እንደሆነና በረከት የሚገኝበት መሆኑን ነው።

፯. በዓለ ትንሣኤ

- ትንሳኤ ከቃሉ ለመረዳት እንደምንችለው **መነሳት** ማለት ነው። ጌታችን አስቀድሞ በትምህርቱ "ነፍሴን ደግሞ...አነሳት ዘንድ አኖራታለሁና...ላኖራት ስልጣን አለኝ ይህችንም ትዕዛዝ ከአባቴ ተቀብያለሁ" ብሎ ነበር።/ዮሐ 10፥1718/ በዚህ መሰረት ጌታችን እንደተናገረው ራሱን በመስቀል ላይ መስዋዕት አድርጎ ተሰቅሎ ሞተ ተቀበረም። በሦስተኛው ቀን መግነዝ ፍቱልኝ መቃብር ክፈቱልኝ ሳይል ተነሳ። ይህች ጌታችን ከሙታን ተለይቶ የተነሳበት ዕለት ትንሳኤ ትባላለች።
- ዕለቲቱ የድል፣ የነፃነት፣ የተስፋ ዕለት ናትና ስለዚህም በዚህ በዓል ሰው ያለውን አዘጋጅቶ ያንኑ ተካፍሎ አብሮ ይበላል ይጠጣል ከዘመድ ከባዳው ጋር አብረው ይደሰታሉ።
- የትንሳኤ በዓል መከበር የጀመረው በዚያው በመጀመሪያዎቹ ዘመናት እንደነበር ቅዱስ ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ምዕመናን በፃፈው በመጀመሪያው መልእክቱ ስለትንሳኤ በዓል አከባበር ዕፁል።/1ኛ ቆሮ5፥6-8/ ከዚያ በኋላ የተነሱ አበው ይህችን ዕለት **የዕለት ንግስት**፣ በዓሉንም **የበዓላት በዓል**፣ **የክብራችን ሁሉ ክብር** ሲሉ ያከብሩ ነበር።
- የበዓለ ትንሳኤ አከባበር ስርዓት ሁሉን አቀፍና ተመሳሳይ ሆኖ መከበር የጀመረው በ4ኛው ክ/ዘመን ጀምሮ ነው። በንጉስ ቆስጠንጢኖስ ጊዜ ሕዝቡ ተሰብስቦ በድምቀትና በአንድነት ከዋዜማው ጀምሮ መብራት እያበሩ ማክበር ተጀምሯል። በየዓመቱ ከእሑድ በዓሉ አይዋጣም ወሩና ቀኑ ከፍም ዝቅም ይላል።

፰. በዓለ ዕርገት

- ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በፈቃዱ ሞቶ ከተነሳ በኋላ ለ 40 ቀናት ያህ ደቀመዛሙርቱን ሲያስተምራቸው ቆይቷል። ቅዱስ ሉቃስ እንደተናገረው ከትንሳኤው በኋላ በምድር ላይ የቆየው ለ 40 ቀናት ብቻ ነው።
- ጌታችን ያረገው በደብረ ዘይት ተራራ ነው። /ሐዋ 1፥1/ ሉቃ 24፥50-53/ ዮሐ 6፥62/ 1ኛጢሞ 3፥16/ ዕርገት እንደ ሌሎች በዓላት ዝግጅት ባይደረግበትም በቤተክርስቲያን ግን የተሟላ አግልግሎት የሚሰጥበት ማኅሌቱ፣ ቅዳሴው፣ ይባቤው የሚደረግበት ዕለት ነው።
- ዕርገት በተለየ አካሉ ሰው የሆነው ወልደ እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስ የመጣበትን የድኅነት ስራ ፈፅሞ ወደ አባቱ ቀኝ የተመለሰበት ዕለት በመሆኑ ከጌታ ዓበይት አንዱ ሆኖ ይከበራል።
  /ሐዋ 7፥57/ ዕብ 4፥14/ ዕብ 7፥16/ 1ኛጢሞ 3፥16/ መዝ 8፥4/

፱. በዓለ ጰራቅሊጦስ (ጰንጠቆስጤ)

- ጰንጠቆስጤ ማለት ቃሉ የግሪክ ቃል ሲሆን ትርጉሙም **ሃምሳኛ** ማለት ነው። ጰራቅሊጦስ ማለት ደግሞ **ከጎን የሚቆም፣ የሚረዳ፣ የሚያጽናና** ማለት ነው። በብሉይ ኪዳን ዘመን ከባርነት የወጡበት የቂጣ በዓል (በዓለ ፋሲካን) ካከበሩ በኋላ ሃምሳኛውን ቀን በተለየ ሁኔታ በዓለ ሰዊት ብለው ያከብሩታል። በእነርሱ ከመጋቢት እስከ ግንቦት ያለው ወቅት ፀደይ (የእሸት ወራት) ነውና። ጌታችን ባወቀ ይህን በዓል (በዓለ ሰዊትን) ለሐዲስ ኪዳን መሠረት እንዲሆን አደረገው።
- ይህ በዓል የሚከበርበት ዓቢይ ምክንያት የሆነው ርደተ መንፈስቅዱስ (የመንፈስ ቅዱስ መውረድ) ነው። ይህም ጌታችን በዐረገ በአስረኛው ቀን ከትንሳኤው (ከተነሳ) ደግሞ በ50ኛው ቀን ነው።

ንዑሳን በዓላት

- ቤተክርስቲያን ከምታከብራቸው በዓላት መካከል ዘጠኙ ንዑሳን በዓላት ይገኙበታል። እነዚህም፡-
  ፩. ስብከት ፪.ኖላዊ ፫. ግዝረት ፬. ቃና ዘገሊላ ፭. መስቀል...ናቸው

  ፮. ብርሃን ፯. ጌና ፰. ልደተ ስምዖን ፱. ደብረ ዘይት

፩. <u>ስብከት</u>

- ይህ በዓል የሚገኘው ከበዓለ ልደት በፊት ባለው እሁድ ነው። የሚከበርበትም ምክንያት ነቢያት በትንቢታቸው (በስብከታቸው) **ይወርዳል፣ ይወለዳል፣ ይመጣል፣ ያድነንማል** እያሉ የተናገሩለትን ትንቢት ለማስታወስ ነው።

፪. <u>ብርሃን</u>

- በዓሉ የሚከበርበት ዓቢይ ምክንያት ነቢያት **የዓለም ብርሃን** መሲህ ይመጣል እያሉ ማስተማራቸውን ለማስታወስ ነው።

፫. <u>ኖላዊ</u>

- ይህም የዓለም ጠባቂዋ (እረኛዋ) የአዳም ተስፋን ለመፈፀም ሰው እንደሚሆን እንደሚመጣ ነቢያት የተናገሩለት ትምህርት (ትንቢት) ለማስታወስ ነው።
  - ❖ እነዚህ ሶስት በዓላት የሚከበሩበት ከልደት በፊት በሚገኙት ሶስት ተከታታይ እሑዶች በቅደም ተከተላቸው መሠረት ነው። እነዚህ በዓላት የሚከበሩት በቤተክርስቲያን ቀለም (በስብሐተ እግዚአብሔር) እነዚህ ለማስታወስ የሚረዱ ምንባባትና ቅዳሴ ፀሎት እንጂ የተለየ ስርዓት እንደሌላቸው ተመዝግቧል።

፬. <u>ጌና</u>

- ጌና **በዓለ ልደት** ማለት ነው። ከንዑሳን በዓላት አንዱ አድርጎ የሚቆጥረው ፍትሀ ነገስት ነው። በዓሉ የሚከበረው በየዓመቱ የልደት ዋዜማ ነው። በዚህ መሰረት ይህ ዕለት የጌታ የልደት ዋዜማ በመባል ይጠራል።

፭. <u>ግዝረት</u>

- ይህ በዓል ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መገረዙን በማሰብ የሚከበር በዓል ነው። የሚከበርበትም እለት **ጥር ስድስት (6)** ቀን ነው። ይህ ጌታችን ለተወለደበት ዕለት ለታኅሳስ 29 ቀን ስምንተኛ ቀኑ እንደሆነ እንገነዘባለን። ይህም ጌታችን የሙሴን ሕግ ለመፈፀም እንደሆነ ያስረዳል። /ዘፀ 12፥3/
- ወንጌል እንደገለፀው ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ቤተ ግዝረት ሄዲል እንጂ አልተገረዘም "ቢገርዙት ስምነት ቀን በሞላ ጊዜ በማኅፀን ሳይገረዝ በመልአኩ እንደተባለ ስሙ ኢየሱስ ተብሎ ተጠራ" /ሉቃ 2፥21/ እንደ ብሉይ ስርዓት በስምንተኛው ቀን ወደ ቤተ ግዝረት ቢወስዱትም ከዕለተ ሞቱ በፊት ደሙ በከንቱ ትፈስ ዘንድ አይገባም ነበርና በተአምራት ተገዘረ። ይህ እንደምን ነው? ቢሉ ያለወንድ እንደተፀነሰው ያለስለት፣ ያለደም መፍሰስ ተገዘሯል።

፮. <u>ልደተ ስምዖን</u>

- ይህም በዓል ተዓምራት በተደረገለት ከደጋግ አባቶች አንዱ በሆነው በስምዖን ስም ይጠራ እንጂ በዓልነቱ የጌታ ነው። ታሪኩ /በሉቃ 2፥22-25/ ላይ ይገኛል። /ዘሌ 12፥2-8/
- የመንፃት ወራት ሲያበቃ (ከ40ቀን በኋላ) ወደ ቤተመቅደስ ይዛው ስትሄድ የተደረገ ተዓምር ነው።
- **<u>ስምዖን ማን ነው?</u>** ከክርስቶስ ልደት በፊት 284 ዓመት አስቀድሞ በዘመነ በጥሊሞስ ጊዜ መፃሕፍተ ብሉያትን ከእብራይስጥ ወደ ጽርዕ ከመለሱት ሰባ ሊቃውንት አንዱ ነው። ትርጉም በሚሰራበት ወቅት በኢሳይያስ የተፃፈው ***"እነሆ ድንግል ትፀንሳለች"*** የሚለውን ቃል ግራ አጋብው ድንግል እንዴት ትፀንሳለች ትወልዳለች ብሎ ሴት ትፀንሳለች ትወልዳለች ብሎ በሦስተኛው እፍቃለሁ ሲል መንፈስ እግዚአብሔር "ተው አትፋቀው" ይህ አንተ የተጠራጠርከውን ሳታየው አትሞትም አለው። እርሱም በእግዚአብሔር ረድኤት ተጠብቆ ከኖረ በኋላ ቀኑ ሲደርስ በመንፈስ ተረድቶ ወደ ቤተመቅደስ ይወጣል።



- በዚያም አግኝቶት ከእርጅናው ስለታደሰ በዓሉ የጌታ ሆኖ ሳለ ልደቱ ስምዖን እየተባለ ይጠራል። /ሉቃ 2፥22-25/

፮. ቃና ዘገሊላ

- ቃና ዘገሊላ አውራጃ የምትገኝ መንደር ናት። በዚህች ቦታ ጌታ በሰርግ በዓል ላይ ተገኝቶ ከጥምቀቱ በኋላ የመጀመሪያውን ተዓምር አድርጓል። በዚህ ዕለት ከተደረጉ ነገሮች አራት ዓበይት ትምህርቶችን እንገነዘባለን።

ሀ. ተዓምራቱን

- ውሃውን ወደ ወይን መለወጡ ነው። ይህም በኃይሉ በስልጣኑ ያደረገው ነው።

ለ. ምስጢረ ቁርባን (ትምህርት)

- እመቤታችን ጌታችን የወይን ጠጅ እንዲያደርግላቸው በማለደችው ጊዜ "ጊዜዬ ገና አልደረሰም" ያላት እውነትና ወይን (ደሜን) የምሰጥበት ጊዜ ገና ነው ለማለት እንደሆነ ትርጓሜያችን ያስረዳል። ስለዚህ የዚህ ዕለት ትምህርቱ የምስጢረ ቁርባን ትምህርት አስቀድሞ የተነገረበት ነው።

ሐ. የእመቤታችን አማላጅነት

- በዚህ ዕለት ያደረገችው አማጅነቷን የሚገልፅ ነው። ምክንያቱም የወይን ጠጅ ማለቁን እርሱ ራሱ ጌታችን ያውቃል የባሕሪይ አምላክ ነውና እንደሚያውቅም ደግሞ እመቤታችን ታውቃለች። ስለዚህም እመቤታችን ለባለሰርጎች አማላጅ ሆና ጠየቀች ጌታችንም ከአንቺ ሰው የሆንኩት ፈቃድሽን ላልፈፅም ነውን ይህን ላደርግልሽ ከአንቺ ጋር ምን አለኝ በማለት መለሰላት። እርሷም የአክብሮት መልሱን አይታ "***የሚላችሁን ሁሉ አድርጉ***" ስትል አዘዘቻቸው። ይህም ለአማላጅነቷ አስረጂ ነው።

መ. ምስጢረ ተክሊል

- ጌታችን በቃና ዘገሊላ መገኘቱና በዚያ ተዓምራት ማድረጉን ሰርግን የማክበሩና ጋብቻን ቤተ ክርስቲያን አንድ ምስጢር አድርጋ እንድትይዘው መሰረት የጣለበት ነው። ስለዚህ ጋብቻ ቅዱስና የተባረከ ለሰው ለጆች የተፈቀደ በእግዚአብሔር የተወደደ መሆኑን ያስረዳል። /ማቴ 19፥3-8/
- በአጠቃለይ ይህ ተዓምራት የተደረገው በዓል የሚታሰበው **የካቲት 12** ነው።

፯. ደብረዘይት

- ደብረ ዘይት ከኢየሩሳሌም በስተምስራቅ በኩል የቁድሮንን ሸለቆ ተሻግሮ የሚገኝ ተራራ ነው። ደብረዘይት ስያሜውን ያገኘው በተራራው ላይ በብዛት ከሚገኘው የወይራ ዘይት ዛፍ ይመስላል ደብረ ዘይት ማለት የወይራ ዛፍ የመላበት ተራራ ማለት ነውና።
- ደብረ ዘይት ላይ የተደረጉ ነገሮች፡-
  - ሀ. ዳዊት ከአቤሴሎም በሸሸ ጊዜ ተጠግቶበታል። /2ኛሳሙ 15፥10/
  - ለ. ጌታችን አስተምሮ ውሎ ማታ እየሄደ የሚያድረው በደብረዘይት ነው።
  - ሐ. በዕለተ ሆሳዕና ከኢየሩሳሌም ሲወጣ የገባው ደብረዘይት ነው። /ማር 11፥1/
  - መ. አይሁድ ጌታን የያዙት በዚህ ተራራ ግርጌ በምትገኘው ጌቴሰማኒ ነው። /ማቴ 26፥30/



ሠ. የዚህ ዓለም የድኅነት ስራው ፈጽሞ ያረገው በዚሁ ተራራ ነው።
ረ. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በኋላ ዳግመኛ ይመጣል ተብሎ የሚጠበቀው በዚህ ነው። /ዘካ14፥4/
ሰ. ስለ ዳግም ምፅአቱ ያስተማረው በዚህ ተራራ ነው። /ማቴ 24፥1-15/

- ይህ በዓል የሚታሰበው በዓቢይ ፆም አጋማሽ ላይ ነው። ቅዱስ ያሬድ በድጓው በዚህ ዕለት የምፅአቱ ቃለ እግዚአብሔር ስራ እኛም በዚህ እለት የምንጠየቀውን ጥያቄ በማሰብ እናከብረዋለን።

፱. መስቀል

- በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን የመስቀል በዓል የሚከበረው መጋቢት 10 እና መስከረም 17 ነው። በዓሉ የሚከበረው መስቀሉ ከተቀበረ ከ300 ዓመታት በኋላ መገኘቱን ምክንያት በማድረግ ነው።
- ንግስት ኅሌኒ ኪራኮስ በሚባል ሽማግሌ በተነገራት መሠረት መስከረም 16 ቀን ደመራ አስደምራ ዕጣን አስጭሳ በእግዚአብሔር አመልካችነት የተቀበረበትን ቦታ አገኘች። በዚህ መሰረት መስከረም 17 ቀን ቁፋሮ አስጀምራ መጋቢት 10 ቀን ተገኝቶ ወጥቷል። በኋላም ለመስቀሉ መታሰቢያ አሰርታ ተመርቆ የገባው (ቅዳሴ ቤቱ የተከበረው) መስከረም 17 ቀን ስለሆነ ሁለቱም ዕለታት ተከብረዋል።
- በመስከረም 17 በደማቅና በመጀመሪያ ደረጃ እንዲከበር ያደረገው ምክንያት ግን መጋቢት 10 ቀን ሁል ጊዜ በዓቢይ ፆም ወቅት ላይ የሚውል በመሆኑ በዚህ ወቅት ተድላ ደስታ የሚደረግበት ወቅት ሳይሆን በፆም በፀሎት በሱባዔ የሚገኙበት በመሆኑ በመስከረም እንዲከበር ሆኗል።
- የበዓሉ አከባበር የጥንቱ ስርዓት ሳይለቅ ደመራ ተደምሮ በአባቶች ካህናት ፀሎት ተፀልዮ በዝማሬ በቸብቸቦ ከሕዝቡ ጋር ደመራው የማብራቱ ስርዓት ይከናወናል ደመራ ነዶ ካለቀ በኋላ የተቃጠለውን እምነት እየተቀቡ ለበረከት ይካፈሉታል።

✞ በዓለ ማርያም

❖ የቅድስት ማርያም መታሰቢያ ዕለታት የሆነችን በሚገባ ማክበር ይኖርብናል በነዚህም ዕለታት የእርሷን የሕይወት ታሪኳን በመንገር በመስማት በዝማሬ በፀሎት ማክበር ተገቢ ነው። የእመቤታችን በዓላት ቢቻለን ሰላሣ ሶስቱን በዓላት ማክበር አለብን ባይቻለን ግን አምስቱን በዓላትን ማክበር ተገቢ ነው። እነሱም፡-

፩. ጥር 21 ቀን የዕረፍት በዓሏን
፪. የካቲት 16 ቀን የምህረት ቃል ኪዳን የተቀበለችበትን
፫. ግንቦት 1 ቀን የተወለደችበት ልደታ (ልደቷን)
፬. ሰኔ 21 ቀን በጎልጎታ የፀለየችበትን
፭. ነሐሴ 16 ቀን ስጋዋ ያረገበትን (ፍልሰቷን)

❖ እመቤታችን በቃልኪዳኗ እነዚህ በዓላቴን ያከበሩ ምስጋናዬን የፃፉ የተረጎሙ እቀምላቸዋለሁ በችግራቸው ሁሉ እረዳቸዋለሁ ብላ ለዮሐንስ ወንጌላዊ የነገረችውን እናገኛለን።

✞ የቅዱሳን መላዕክት በዓል

❖ ቅዱሳን መላእክት የአምላክ ባለሟሎች የሰው ባለውለታዎች ስለሆኑ ክብር ይገባቸዋል። ስለዚህም ቃልኪዳን የተቀበሉበት ስለሆኑ ተአምራትም የሰሩበትን ዕለት መታሰቢያ በማድረግ እናከብራለን።
❖ መላእክተኞች የሰው ጠበቂዎች መሆናቸውን እናምናለን። /ማቴ 18፥10/ እንዲሁም የአምላክ መልእክተኞች ናቸው ስለዚህ እንደባለሟልነታቸው እንደአገልግሎታቸው ክብር ይገባቸዋል።

✞ የልዩ ልዩ ቅዱሳን በዓል

❖ አምላክ የቀደሳቸውን ቃል ኪዳን የገባላቸውን ቅዱሳንን ሁሉ ቤተክርስቲያን ታከብራለች ስለዚህም የተወለዱበትን ያረፉበትን አንዳንድ ተአምራትም ያደረጉበትን ዕለት በማክበር እነርሱን በማመስገን ዝናቸውን በመንገር እናሳልፈዋለን። ቅዱሳን የሚባሉ ከሐዋርያት ጀምሮ ፃድቃን ሰማዕታት ደናግል ሌሎችም በፆታ በዕድሜ ሳይወሰኑ የቅድስና የብፅዕና ማዕረግ የተሰጣቸው ሁሉ ናቸው። ስለዚህም የሁሉን መታሰቢያ ማክበር አለብን።



ዋቢ መጻሕፍት

- ሰማንያ አሐዱ (81) መጽሐፍ ቅዱስ
- ፍትሀ ነገስት ንባቡና ትርጓሜው፣ 1990 ዓ.ም
- ሃይማኖተ አበው፣ 1967 ዓ.ም
- መጽሐፈ ቅዳሴ አንድምታ 1988 ዓ.ም
- ስርዓተ ቤተክርስቲያን፣ ሊቀካህናት ክንፈ ገብርኤል አልታዬ፣ 1983 ዓ.ም
- ስርዓተ ቤተክርስቲያን፣ ሊቀካህናት ክንፈ ገብርኤል አልታዬ፣ 1995 ዓ.ም
- የሰዋሰው ቅዱስ ጳውሎስ ወጴጥሮስ መንፈሳዊ ኮሌጅ ለስድስት ወር ትምህርት የተዘጋጀ ያልታተመ
- ኮከሐ ሃይማኖት፣ መልአከ ብርሃን አድማሴ ጀንበሩ፣ 1989 ዓ.ም
- ትምህርትና ክርስትና፣ 1984 ዓ.ም
- የቅዳሴ ስርዓት፣ በመጋቤ ምስጢር ዓምደ ወርቅ ደሴ፣ 1997 ዓ.ም
- ንዋየ ቅዱሳት፣ በሚሊዮን በለጠ አሰፋ፣ 1999 ዓ.ም
- አምደ ሃይማኖት፣ በመምህር ብርሃኑ ጎበና፣ 1986 ዓ.ም
- ስርዓተ ቤተክርስቲያን በካሴት የተቀረፀ፣ መምህር ብርሃኑ ጎበና